## ምዕራፍ ስምንት
## ባልና ሚስት

" . . . ሚስቶች ሆይ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ ። ባሎች ሆይ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፣ መራራም አትሁኑባቸው። "/ቆላ 3፥18-19/ "እንዲሁም እናንተ ሚስቶች ሆይ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ በፍርሃት ያለውን ንፁሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው። ለእናንተም ጠጉርን በመሽረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናፀፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ። እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተስፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፣ እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም ጌታ ብላ እየጠራችው ታዘዘችለት። እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆችዋ ናችሁ።

"እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፣ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ፀጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።" / 1ጴ3፥1-7 /

" ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፣ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና "/ኤፌ 5፥ 22-23/

ባለፈው ትምህርታችን እጮኛን እንዴት እንደምንመርጥ አይተናል። እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት የተዘጋጀው ለወጣት ወንድሞችና እህቶች ነው። ነገር ግን በመካከላችን ያሉት ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ ያገቡም ሰዎች አሉ። ከዚህ በተጨማሪ ብዙ ያገቡ ሰዎች ወደ ፊት የሚድኑም አሉ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ለእነዚህ ላገቡት ሰዎችም በግልፅ እንዴት ባል እንደሚሆንና እንዴትስ ሚስት እንደምትሆን የሚነግሩን ብዙ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። አንድ ሰው ከማግባቱ በፊት ለጋብቻ በጣም የሚስማማውን ሰው መምረጥ አለበት። ነገር ግን ካገባ በኋላ እንዴት ባል እንደሚሆን ወይም እንዴት ሚስት እንደምትሆን በእግዚአብሔር ፊት መማር አለባቸው ። ይህንን በመማር በቤትና በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ችግሮች ይቃለላሉ።

## ለመማር ጊዜ ስጥ

ከሁሉ በፊት ያገቡ ሰዎች ባል ወይም ሚስት መሆን በጣም ጥንቃቄ የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ማወቅ አለባቸው።

### 1. ብርቱ ጉዳይ ስለመሆኑ

አንድ ሰው በአንድ ሙያ ላይ ከመሰማራቱ በፊት በሚገባ መዘጋጀትና የሙያው እውቀት ሊኖረው ይገባል። ሐኪም ለመሆን በኮሌጅ ውስጥ የዓመታት ሥልጠና ያስፈልጋል። አንድ መምህርም ማስተማር ከመጀመሩ በፊት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ገብቶ መማርና የተወሰነ ጊዜ ማጥፋት ያስፈልገዋል። አንድ መሃንዲስም የዓመታት የኮሌጅ ጥናቱን ማጠናቀቅ አለበት። ነርስም እንዲሁ በነርስ ትምሕርት ቤት የህክምና ትምህርት ማጥናት አለባት። ታዲያ አንድ ሰው ባል ወይም ሚስት ለመሆን የአንድ ቀን ሥልጠና እንኳን ለመውሰድ አለመቻሉ አያሳዝንም? ከዚህ የተነሣ ብዙ ምስኪን ባሎችና ሚስቶች መኖራቸው አያስደንቅም። ምክንያቱም ባል ወይም ሚስት እንዴት እንደሚሆንና ትዳር ምን እንደሆነ አልተማሩምና ነው። እኔ ብታመም በሕክምና ሙያ ያልሰለጠኑ ዶክተሮች ወይም ነርሶች ያድኑኛል ብዬ እታመንባቸዋለሁን? አንድ ሰው ሕፃናት እንዲያስተምርልኝ ብፈልግ አንድ ትምርት ቤት የማያውቅ ሰው እንዲረዳልኝ እጠይቀዋለሁኝ? ቤት ብገነባ ብቃት የሌለውን መሐንዲስ እሠማራለሁን? ታዲያ አንድ ሰው ጥሩ ባል ወይም ጥሩ ሚስት እንዴት እንደሚሆን ሣይማር ጥሩ ይሆናል ብዬ አስባለሁን?

ብዙ ጊዜ ወላጆቻችን እንዴት መልካም የትዳር ጓደኛ እንደምንሆን አላስተማሩንም። ለአቅመ አዳም ወይም ሔዋን ስንደርስ ወይም ሥራ ስንይዝ እንዲሁም የትዳር ጓደኛ የሚሆኑን ስናገኝና ቤተሰባችንን ለማስተዳደር የሚበቃ የገንዘብ አቅም ሲኖረን ወደ ትዳሩ ዓለም በቀጥታ እንገባለን። ካለምንም ቅድመ ዝግጅትና በቂ እውቀት የሚደረገው ይህ የጋብቻ መተሳሰር ችግር ላለበት ቤተሰብ መነሻ ነጥብ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ወገኖች ተጋብተው ባልና ሚስት በመሆን መኖር ጀመሩ እንጅ እንዴት መኖር እንዳለባቸውና ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት እንደሚገባቸው ጠንቅቀው አያውቁም። በእንዲህ ዓይነት ጥምረት የተመሠረተ ቤተሰብ እንዴት ስኬታማ ሕይወት ሊኖረው ይችላል? አስቸጋሪ በጣምም አዳጋች ኑሮ ነው።

ስለዚህ አዳዲስ አማኞች ሁሉ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገው ወደ ትዳር ዓለም እንዲገቡ ከሕይወት ልምዳችን በመነሳት በሚገባ መምከርና ማስተማር የእኛ ኃላፊነት ነው ።

ሌላው አዳዲስ አማኞች ሊያውቁት የሚገባቸው ነገር ቢኖር ባል ወይም ሚስት መሆን በጣም ከባድ ነገር መሆኑን ነው። ማንኛውም ሥራ በሰዓት የተወሠነ ሲሆን ይህኛው ግን የማያቋርጥ የሕይወት ዘመን ሥራ ነው። ሌሎች ሥራዎች የጡረታ ዘመን ሲኖራቸው ይህ ግን እስከ ሞት ድረስ ይቀጥላል። በመሆኑም እጅግ በጣም ትኩረት የሚሻና ከሁሉም ሥራዎች የበለጠ ሊታሰብበት የሚገባ ሥራ ነው ።

## 2. እርምጃ ሊወሰድበት የሚገባ ትምህርት

ብዙዎች ያለ ምንም ሥልጠና ወደ ትዳር ዓለም የገቡ ስለሆነ ስላለፈው ከመጨነቅ ይልቅ አሁን ልናተኩርበት የሚገባው ይህን ያለውን ሁኔታ በማሻሻል ላይ ነው። ቤተሰብ እንዴት ከባድ እንደሆነ ብናይ ባሎች እንዴት ባል እንደሚሆኑ ሚስቶችም እንዴት ሚስት እንደሚሆኑ የሚረዱአቸውን እርምጃወች ለመውሰድ ፈቃደኛ ይሆናሉ።

አንድ ሰው ቢሠለጥንና ቤተሰቡን እንደ አንድ ሙያተኛ ቢንከባከብም እንኳ ውድቀት ሊገጥመው ይችላል። ታዲያ የአንድ ሰው አመለካከት ሰልጥኖ እንኳን ችግር የሚገጥመው ከሆነ ያልሰለጠነውማ እንዴት ቤተሰቡን የበለጠ ችግር ላይ አይጥል? አንድ ሰው መላ ኃይሉን በቤተሰቡ ላይ ማዋል አለበት። ከሌላው ነገር ሁሉ ትጋቱ በዚህ ሊያዝ ይገባል። እንደ ቀላል ነገር ከታየ ቤተሰብ ከውድቀት ሊያመልጥ አይችልም። የቤተሰብህ ሕይወት በእግዚአብሔር ፊት ያማረ እንዲሆን በአትኩሮት ልትይዘውና ጊዜ ልትሰጠው ይገባል። ውድቀት ሁሉ ወደ ስኬታማነት መለወጥ ይገባዋል። ጋብቻ ስኬታማ እንዲሆን ጥንቃቄ ያሻዋልና።

ሁሉም ያገቡ ወንድሞችና እህቶች ኃላፊነታቸውን በብቃት ለመወጣት በእግዚአብሔር ፊት ሊማሩ ይገባቸዋል። ጋብቻ ከሌሎች ሙያዎች ይልቅ የበለጠ ከባድ ስለሆነ ማንም ሰው እንዴት እንደሆነ ለመማር መዘግየት የለበትም።

### ዓይንህን ዝጋ

ከጋብቻ በኋላ በመጀመሪያ ልትማረው የሚገባ ነገር ማየት የማይገባህን ነገር ላለማየት ዓይኖችህን መጨፈን ነው።

እንግዲህ ሁለት ሰዎች ከቀን ወደ ቀን ከዓመት እስከ ዓመት ያለ ምንም የዓመት ፈቃድ ወይም የህመም ፈቃድ ባልና ሚስት ሆነው ባንድ ላይ በሚኖሩበት ጊዜ የሌላውን ወገን ድካም ለመፈለግ ሰፊ ጊዜ አላቸው። ነገር ግን አንተ ካገባህ በኋላ ዓይኖችህ ሊሸፈኑ ይገባቸዋል። የጋብቻ ዓላማ የሌላውን ሰው ድካም መፈለግ አይደለም። አስተውል እርሷ ሚስትህ እንጅ ተማሪህ አይደለችም። እርሱም የአንቺ ባል እንጅ የሙያ ተማሪሽ አይደለም። የትዳር ጓደኛን ለመርዳት ወይም ለማረም የእርሱን ችግርና ድካም እንድትፈልጉ አልተጠየቃችሁም። ቤተሰብ በፅኑ መሠረት ላይ መታነፅ አለበት። ስለዚህ ከማግባትህ በፊት ያሉትን ችግሮችና ማናቸውንም ነገሮች ለመረዳት ዓይችህን በስፋት ልትከፍታቸው ይገባል። ካገባህ በኋላ ግን ተጨማሪ ነገር ለማወቅ መፈለግ የለብህም። ፀጉር ለመሰንጠቅ ከፈለግህ ያን ለማድረግ ብዙ እድሎች አሉህ። እግዚአብሔር በአንድ ላይ ሲያስቀምጣችሁ የሌላውን ችግር ለመፈለግ በጣም ብዙ ዘመን ምናልባትም ሃምሳ ዓመት የሚደርስ እድሜ አላችሁ። በዚህ ምክንያት ያገቡ ወንድሞችና እህቶች ሊያደርጉ የሚገባቸው በሌላ ወገን ችግርና ድካም ላይ ዓይናቸውን መጨፈን ነው። ሳትፈልግ እንኳን ብዙ ነገር ታያለህ፣ ታዲያ ሰትፈልግ ብዙ ነገር ካየህ ሆን ብለህ ብትፈልግማ ምን ያህል ችግሮችን ትመለከታለህ ?

ሁለት ሰዎች በባልና ሚስትነት ሲጣመሩ ከእግዚአብሔር መታዘዝና ፍቅር በቤተሰብ እንዲኖር የማድረግን ኃላፊነት ተቀብለዋል። ባልና ሚስት አንዱ የሌላውን ስህተት እየፈለጉ እንዲያርሙ አልተጠየቁም። ባሎች ለሚስቶቻቸው እንደ ዩኒቨርስቲ መምህር እንዲሆኑ ሚስቶችም ለባሎቻቸው አስተማሪ እንዲሆኑ አልተደረገም። ባል ሚስቱን መለወጥ ወይም ሚስት ባልዋን መለወጥ አያስፈልጋቸውም። ዕድሜያቸውን በሙሉ ከትዳር ጓደኛቸው ፀባይ ጋር እንደሚኖሩ ሁሉም ወገኖች ማወቅ ስፈልጋቸዋል። ለመርዳት ብለህ በማሠብ የሌላውን ሰው ችግርና ድካም ሆነ ብለህ አትመልከት። እንደዚህ ዓይነቱ የመርዳት አስተሳሰብ በመሠረቱ ስህተት ነው። ያገቡ ሰዎች ዓይናቸውን መጨፈን መለማመድ አለባቸው። መትጋት ያለባቸው ሌላውን ለማረም ሳይሆን ለማፍቀር ነው።

## መቻቻልን ተለማመድ

መቻቻል ከጋብቻ በኋላ ወዲያውኑ ልንማረው የሚገባ ነገር ነው። ምንም ያህል በባለትዳሮች መካከል ልዩነቶች የሌሉ መስለው ቢታዩም ባይፈጥኑም ዘግይተው የሚከሰቱ ልዩነቶች መኖራቸው ግልፅ ነው። የተለያየ አመለካከት በሚወዱትና በሚጠሉት ነገር ምርጫ፣ በአስተያየትና በዝንባሌ ላይ ልዩነት ይኖራቸዋል። ስለዚህ ከተጋቡ በኋላ ከሌላው ጋር ተቻችሎ መኖርን መለማመድ አለባቸው ።

## 1. ግማሽ መንገድ መሄድ

መቻቻል ማለት ምን ማለት ነው ? መቻቻል ማለት ሌላውን ሰው ግማሽ መንገድ በመሄድ አገኘዋለሁ ማለት ነው። በሁለቱም በኩል እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ካለ መልካም ነው። ነገር ግን ጉዳዩ የተገላቢጦሽ ቢሆን እንኳ አንተ ራስህ ቢያንስ ግማሽ መንገድ መሄድ አለብህ። ደረጃህን ትተህ ሁሉንም መንገድ ብትሄድ ብዙ ችግሮች ይወገዳሉ። ይህ በማይቻልበት ጊዜ ግን ሌላኛው ወገን ቢያንስ በግማሽ መንገድ በመሄድ መገናኘት መልካም ነው። በሌላ አባባል ወንድሞችና እህቶች ተጋብተው ባልና ሚስት ከሆኑ በኋላ በማንኛም ነገር ሁለቱም ማስተካከያዎችን ማድረግ መማር አለባቸው። ሁሉንም መንገድ ማስተካከል ከቻልክ መልካም ነው። ካልቻልክ ግን ቢያንስ ግማሽ መንገድ መሄድን መለማመድ አለብህ። ካንተ ክልል ተራምደህ ሌላውን ማግኘትን ተማር። ባመለካከትህም ቢሆን ግትር አትሁን። ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የአመለካከት ለውጥ ለማድረግ ፈቃደኛ ሁን። በእርግጥ የራስህ የሆነ አስተሳሰብ ሊኖርህ ይችላል። ቢሆንም ግን ከሕይወት ጓደኛህ አስተሳሰብ ጋር መቻቻልን ተማር።

ወጣት ተጋቢዎች ለመጀመሪያው አምስት የጋብቻ ዓመታት እርስ በእርሳቸው መቻቻልን ከተማሩ ከአምስት ዓመት በኋላ ሰላምና ደስታ ያለው ቤት ይኖራቸዋል። በአምስቱ ዓመታት ጊዜ ውስጥ መቻቻል ምን እንደሆነ ካልተማሩ፣ ግማሽ መንገድ እየሄዱም ካልተገናኙ ያ ቤተሰብ ይስተካከላል ለማለት የማይቻል ነው። ጋብቻ ቀላል ጉዳይ አይደለም። ጥሩ ጋብቻ ጊዜና ጥረትን ይጠይቃል።

መቻቻልና መረዳዳት ማለት ሌላውን ወገን የሚያስጨንቀውን መፈለግ ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች ድምፅ /ጫጫታ/ ይጠላሉ። አንዳንዶች ደግሞ ፀጥ ሲል ይጨንቃቸዋል። አንዳንዶች ያለ ብዙ እንቅስቃሴ / ስራ/ መኖር ያቅታቸዋል። ሌሎቹ ደግሞ ብዙ አይፈልጉም። እንግዲህ መቻቻል ሊኖር የሚገባው እዚህ ላይ ነው። ስለዚህ አንደኛው ድምፁን መቀነስ፣ ሌለኛው ደግሞ መጠነኛ ጫጫታ እንዲኖር መፍቀድ ይኖርባቸዋል። በዚህ ጊዜ ግማሽ መንገድ ላይ ይገናኛሉ። ሚስቲቱ ትጉ ባልየው ደግሞ በጣም ዳተኛ ነው እንበል። ስለዚህ ዳተኛው ሰው ትጉዋን ሚስቱን ሙሉ በሙሉ ተከተል ቢባል አንድ ቀን ሁሉን ነገር ወርውሮ ጥሎ ሚስቱ ወደ ወላጆቿ ቤት እንድትሄድ ሊያደርጋት ይችላል። ወይም የባለቤቷ ከባድ ዳተኝነት ሚስትዮዋን ፈቷን ወላጆቿ ቤት እንድታዞር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

2. ራስን መካድ መማር

ክርስቲያን እንደመሆናችን ራስን መካድ መማር አለብን። ራስን መካድ ማለት ለሌላው ሰው ሲባል ያን ሰው መቻል ወይም መሸከም ማለት ነው። ሁለቱም ባልና ሚስት የበለጠ መቻቻልን መማር አለባቸው። እንደዚያ ቢያደርጉ ቢያንስ በቤተሰብ ውስጥ ሰላም ይኖራል። ራስን መካድ ባለበት መቻቻል አለ። ራስን መካድ በሌለበት መቻቻል የለም። ወጣት አማኞች በቤተሰብ ውስጥ መቻቻል ማለት ጥቂት ነገሮችን ሳይሆን በጣም ብዙ ነገሮችን የሚያጠቃልል መሆኑን መገንዘብ አለባቸው። ጆ.ኤች. ፔምበር የቤተሰብ ዲሲፕሊን ወይም መመሪያ እያሉ የሚጠሩት ይህንን ነው። በቤተሰብ ውስጥ ለመቻቻል ብዙ ሁኔታዎች ካሉ በዚያ ቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ጥሩ ሥነ ሥርዓት አለ ማለት ትችላለህ። የራስህን አመለካከት ትተህ የሌሎችን አስተያየት መቀበልን ተማር።

## አድናቂና ንቁ ሁን

ካገባህ በኋላ የትዳር ጓደኛህን ጠንካራ ጎን ማድነቅን ተማር፦

1. የሌሎችን ጥንካሬ ፈልግ

የሌሎችን ድካም መቻልና ጓይናችንን መሸፈን ብቻ ሳይሆን ጥንካሬአቸውንም ማድነቅ መማር አለብን። በመልካም ሁኔታ በተሠሩ ነገሮች ላይ ንቁ መሆን አለብን። የቤተሰብ ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ የሚሻከረው ባል ሚስቱን እንዴት እንደሚያደንቅ ካላወቀና ሚስትም ለባሏ ተገቢውን ክብርና ቦታ ሳትሰጠው ስትቀር ነው። አስተውል፣ ሚስቶቻችንን መጣልና የባሎቻችንን ጥማት አለማርካት ትክክል አይደለም። የሚያስፈልገን እርስ በእርሳችን አድናቆትን መግለፅ ነው። የሌላውን ጥንካሬና መልካም ምግባር እንዲሁም ውበትን ማየት መማር አለብን።

በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ኃላፊነት ያለው ወንድም በሁሉ ሰው ዘንድ መልካም ይነገርለታል። ነገር ግን ስለዚህ ሰው ሚስቱን ብትጠይቋት ሁል ጊዜ የመጨረሻው ከፋ ሰው እንደሆነ ትናገራለች። ለኃላፊነት ብቁ የሆነ ሰው ብቁ እንዳልሆነ ባሏን እየነቀፈች ሁልጊዜ ትናገራለች። ይህ ለምን ሆነ ምናልባት ባለቤቷን ልትመራ ስለምትፈልግ ሊሆን ይችላል። ይህን በመቃወሙም ለኃላፊነት ብቁ እንዳልሆነ አድርጋ ትከሰዋለች። ይሁን እንጂ ሁሉም ወንድሞችና እህቶች በማንኛውም ጊዜ ይህን ሰው ያከብሩታል። ይህን የማትቀበል ሚስቱ ብቻ ነች። ታዲያ እንደዚህ ዓይነት ቤተሰብ እንዴት ሆኖ ውብ ህይወት ሊኖረው ይችላል?

በሌላ መንገድ ደግሞ በባልዮው አድናቆት ብቻ ብዙ ሰዎች ሴትዮዋ ጥሩ ሚስት እንደሆነች ሊረዱ ይችላሉ። በፔኪንግ በነበርኩበት ጊዜ አንድ ነገር አስታውሣለሁ። ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው ሲያወሩ አንዲት እህት በጣም ያደንቋታል። በንግግራቸው መካከል ባለቤቷ መጣና ተጨመረ። እነርሱም ያችን እህት ማድነቃቸውን ቀጠሉ። ነገር ግን ባለቤቷ ምንም ቃል አልተነፈሠም። የእርሱ ፀጥታ እንዲህ የሚል ይመስል ነበር። "ትክክል ያልሆነች ሴት ማግባቴን ማን በነገራቸው" እንደዚህ ዓይነቱ አስተሣሠብ ቤተሰብን ያፈርሣል። የትዳር ጓደኛችንን ጠንካራ ጎን ከእኛ ቀድመው ሌሎች ሲያውቁ መስማት እንዴት ሚያሳፍር ነገር ነው። ዓይናችን ካልታወረ በስተቀር እኛ መቅደም አልነበረብንም?

## 2. <u>አድናቆትህ እንዲታወቅ አድርግ</u>

ባል ለሚስቱ ያለው አድናቆት ከሌሎች ሰዎች ያነሰ ሊሆን አይገባውም። ከሌሎች ሰዎች ባይበልጥም እንኳን ማነስ ግን የለበትም። የእርሷን ጠቀሜታ ዋጋ የማትሰጠውና በትንሹ የምታደንቀው ከሆነ ለምን አገባሃት? ያን ጊዜ የነበረህ እይታ ወይም አሁን ያለህ እይታ ስሕተት ነው ማለት ነው። በሚስቲቱም በኩል እንዲሁ ሊሆን ይገባል። ይህ ሰው ትክክለኛ ሰው እንዳልሆነ የሚሠማሽ ከሆነ ለምን አገባሽው? ካገባሽው ስህተት የፈፀምሽው አንቺ ራስሽ መሆንሽን ማወቅ አለብሽ። ደስተኛ ቤተሰብ እንዲኖር የጋራ አድናቆት ያስፈልጋል። አንተ እየነቀፍክ ሌሎች ሰዎች ሚስትህን እንዲያደንቁ አታድርግ። ያገባኻትን ሴት ጠንካራ ጎን እያየህ የእርሷን መልካም ነገር ተረዳ። ሁኔታዎች ሲመቻቹልህም ያየኸውንና የሚሰማህን ጥሩ ነገር በይፋ ተናገር። ይህ የምትናገረው ደግሞ እውነት እንጂ ግምት መሆን የለበትም። ባልና ሚስት በዚህ ዓይነት መንገድ አንድ ለአንድ አድናቆታቸውን ቢገልፁ የቤተሰብ ትስስራቸው ይጠነክራል።

እንደዚህ ዓይነት የአድናቆት መግለጫ ከሌለ ብዙ አለመግባባትና ችግሮች ይመነጫሉ። በእንግሊዝ አገር የሚኖር አንድ ያገባ ወንድም አንድ ቀንም እንኳ ሚስቱ መልካም ነገር እንዳደረገች ተናግሮ አያውቅም። በዚህም የተነሣ ይህች እህት እንደ ክርስቲያን ሚስት መሆን አልቻልኩም በማለት ሁልጊዜ ትጨነቅ ነበር። ጭንቀቷም በሳንባ ነቀርሣ እንድትጠቃና ለሞት እንድትቃረብ አደረጋት። በሞት አፋፍ ላይ እያለችም ባለቤቷ "ከሞትሽ ምን እንደማደርግ አላውቅም፣ በዘመንሽ ሁሉ እጅግ መልካም ነገሮችን አድርገሻል፣ ከሞትሽ ግን ይህ ቤተሰብ ምን ሊሆን ነው?" አላት።እርሷም ስትመልስ "ይህን አሁን የተናገርከውን ለምን ቀደም ሲል አልገለጽክልኝም ነበር" አለችው። በመቀጠልም "እኔ ሁል ጊዜ መ ነገር ይሰማኝ ስለነበረ ራሴን ስወቅሰው ኖርሁ። አንድ ቀንም እንኳን መልካምን ነገር አድርገሻል ብለኸኝ አታውቅም። በዚህም

የተነሳ ታመምኩ። አሁንም ይኸው ለሞት ተቃረብኩ" አለችው። አስተውል ቤተሰብ መልካም ቃሎትን ይፈልጋል። እነዚህ መልካም ቃላት በተደጋጋሚ ከተነገሩ መልካም ይሆናል። ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው ሊደናነቁ ይገባል። አንዱ ለአንዱም ጥሩ ነገር መናገሩ ያንፀዋል፣ ያበረታታዋልም።

ሚስቶቻቸው ስለማያደንቋቸው ብቻ መልካም መስራት እየቻሉ መልካም ማድረግ ያቃታቸውን ጥቂት ወንድሞች አውቃለሁ ሚስቶቻቸው ሁልጊዜ ጥሩ እንዳልሆኑ ይነግሩአቸዋል። ከዚህም የተነሣ እነዚህ ባሎች ራሣቸውን መከሰስና መውቀስ ይጀምራሉ። ሚስቶቻቸው ህሊናቸው ሆነው ይሠራሉ። እንግዲህ እነዚህ በደንብ የሚያውቋቸው ሚስቶቻቸው ምንም መልካም ነገር እንደሌላቸው ሲፈርዱባቸው ባሎችም መልካም ነገር የለኝም ብለው ይደመድማሉ። በዚህም ብዙ ውድቀት ይደርስባቸዋል። አስተውሉ የአንድ ቤተሰብ ሕይወት ውድቀት የሚደርስበት በቤት ውስጥ ባለው የአድናቆት መጠንና የሌላውን ሰው ጥንካሬና መልካም ጎን በመቀበልና እንዲሁም የሌላውን ሰው ድካምና ችግር ከማየት በመቆጠብ ነው።

## አክባሪ ሁን

ቤተሰብ እርስ በእርሱ ሊከባበር ይገባል። አለመከባበር ፀያፍ ነገር ነው።

እኛ ሁላችን ማንኛውንም ሰው ማክበር አለብን። ነገር ግን ከሰውየው ጋር ስለተላመድህ ብቻ ካላከበርከውና ትህትና ከጎደለህ ይህን ወዳጅህን ታጣዋለህ። ሐዋርያው ጳውሎስም ስለፍቅር ሲናገር "የማይገባውን አያደርግም" (1ቆሮ 13፥5) ይላል። ብዙ ጊዜ የቤተሰብ ችግር የሚመጣው በትንሽ ነገር ነው። አንድ ሰው ጥቂት ቸርነት ወይም ክብር ብቻ የሚኖረው ከሆነ ያ ቤት ችግር ይገጥመዋል። ያገባሽው ሰው በጣም የሚቀርብሽ ስለሆነ ስለ እርሱ ጥቂት የምታስቢ ይሆናል። ነገር ግን አስተውይ መከባበር የሰውን ግንኙነት ያዳብራል። ይህ ከሌለ ግን አስቀያሚው የሕይወት ገፅታ ሁሉ ይገለፃል። ምንም እንኳን የለመድካቸው ሰዎች ቢሆኑም መከባበር የግድ መኖር አለበት። አንድ ወንድም ይህን ነገር በሚገባ ሲገልፀው "መከባበር የአንድ ማሽን ማንቀሣቀሻ ቅባትን ይመስላል " ብሏል። ትሕትና ከሌለ ግጭቶችና የማያስደስቱ ስሜቶች ይከሰታሉ።

## 1. በንግግርህ ውስጥ ትሕትናህ ይገለፅ

"አመሰግናለሁ" ወይም "ይቅርታ አድርግልኝ" የሚሉትን ቃላት ተማር። "እችላለሁን?" ወይም "እባክህ " የሚሉት የትህትና አነጋግሮች በተደጋጋሚ ልትቀጠምባቸው ይገባል። እነዚህ ቃላት ከሌሉህ ወዳጆችን ለማፍራት አትችልም። ታዲያ በእነዚህ ቃላት ምክንያት ወዳጆችን ማፍራት ካልቻልክ እንዴት በቤተሰብማ የበለጠ አያስፈልጉም? ክርስቲያን "ፍቅር የማይገባውን አያደርግም " የሚለውን ማስተዋል አለበት። ይህም የፀጋ ቃል በቤታችን ውስጥ መናገር መለማመድ እንዳለብን ይመክረናል።

## 2. በአለባበስ ንፁህ መሆን

የአንተ ቃላት ትሁትና ሰው አክባሪ ባህርይህ ብቻ በቂ ስላልሆነ አለባበስህም እንደዚሁ ንፁህ መሆን አለበት። በጓደኞችህ ፊት ንፁህ ሆነህ መቅረብ እንደምትወደው ሁሉ በቤትህም ንፁህ ልብስን ልበስ። በአለባበስ ጉዳይ የማይገባን ነገር አታድርግ። ቅርበት ስላላችሁና ስለተላመዳችሁ ብቻ ግዴለሽ አትሁን። መላመድ ንቀትንም ሊያመጣ ይችላል። እንደባልና ሚስት ማን የሚቀራረብ አለ ? ስለዚህ መከባበር ቸል መባል የለበትም። ስትለብስም ንፁህ ነገር ልበስ። ቤትም ስትሆን የማያስከብርህን አትልበስ።

## 3. በባህሪህ ውስጥ ባለ ፀግነትን አሳይ

በባህርይ ውስጥ ባለፀግነት ሊኖር ይገባል። አንድን እቃ ስትሠጥ ከእቅም በላይ ካልሆነብህ በስተቀር በሁለት እጅህ ብታቀብል መልካም ነው። ቢላ ወይም መቀስ ለሰው ስታቀብል ጫፉን ወይም ስለቱን ወደ እርሱ አታዙር። በተለይም በቤት ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ፀጋ ሊኖር ይገባዋል። አንድን እቃ ወስዶ በእጅ በመስጠት ፋንታ መወርወር ሶስት ሰኮንዶች ሊቆጥብ ይችላል። ከዚያ በኋላ ያለው ውጤት ግን ፍፁም ከባድ ነው። ስለዚህ ትሁት ወይንም ሰው አክባሪ መሆንን ተለማመድ።

አንድ ሰው ትሁት መሆኑን ለማወቅ የሚረዱ ከብዙ ቤተሰብ ጋር በቂ የሆነ ግንኙነት አድርጌአለሁ። እርሷ ወይም እርሱ ጥቂት ችግሮች ሊኖሩባቸው ይችላሉ። ይሁን እንጅ አንድ እንደ ህግ ያለ ነገር እናያለን፣ ከባልና ከሚስት አንዱ ትሁት ወይንም አክባሪ ከሆነ ያ ቤተሰብ ቢያንስ ፀጥታ ይኖረዋል። የሳህንና የማንኪያ ድምፅ ይቀንሣል።መከባበርን ወይም ትህትናን ያጣ ቤተሰብ ግን በግጭት ይሞላል። አንዲት ሴት ጓደኞቿን ሚስት በሆነችበት ደረጃ ሆና የምታስተናግዳቸው ከሆነና ባልም ጓደኞቹን

ባል በሆነበት ደረጃ ዓይነት ጓደኞቹን የሚያይ ከሆነ የእነዚህን ሰዎች ቤት ማንም ዘወር ብሎ አያየውም። ከዚያ የምንረዳው ወንድሞችን ልንነግራቸው የሚገባ ነገር ባልንጀሮቻቸው ሊሸከሙት የማይችሉትን ሚስቶቻቸው ታግሰው የቻሉ መሆናቸውን ነው። እህቶችንም ልንነግራቸው የሚገባ ባሎቻቸው ለእነርሱ ታጋሽ መሆናቸውን ነው። ማለትም ጓደኞቻቸው ሊቋቋሙት የማይችሉትን ድርጊት በባሎቻቸው ላይ እየፈፀሙ ባሎቻቸው የታገሱአቸው መሆኑን ነው። ስለዚህ ለትዳር ጓደኛ ትሁት አለመሆን ጨካኝነት ነው። ክርስቲያን ደግሞ ጨካኝ መሆን የለበትም። ክርስቶስን ያወቀ ሰው ከትህትና ሊወጣ አይገባውም / ኤር 4፥20/

## 4. በድምፅ ውስጥ የፍቅር ቃላጼ ይኑርህ

ድምፃችንም ደግነትን የተሞላ ወይም ከልባችን የሆነ ፍቅርን መግለፅ አለበት። አንድን ቃል በተለያየ መንገድና ቃላጼ መናገር ይቻላል። አንድ አለቃ ሠራተኞቹን በሆነ ቃላጼ ሊናገራቸው ይችላል። ጓደኛሞች እርስ በእርሳቸው በጓደኝነት ቃላጼ ሊነጋገሩ ይችላሉ። ፍቅር በፍቅር ድምፅ ይናገራል። የጥላቻ ቃልም ጥላቻ በሚገልፅ ድምፅ ይነገራል። የብዙ ሰዎች ችግር አስደሳች ድምጾችን ከቤታቸው ውጭ ስለሚጨርሱ ቤት ውስጥ የማያስደስቱ ድምፆችን መጠቀማቸው ነው። በስራ ቦታቸው ለስራ ባልደረቦቻቸው ትሁት ናቸው። በሆስፒታል ላሉ ሕመምተኞችም ታጋሾች ናቸው። በትምሕርት ቤት ላሉ ተማሪዎችም ሲናገሩ ይጠነቀቃሉ። ነገር ግን ቤታቸው ውስጥ ስለሚጠቀሙበት ጽምፅ ግድ የላቸውም። በቤት ውስጥ የሚናገሩትን ዓይነት ድምፅ ቢሮ ውስጥ ቢያስተጋቡና ቢጠቀሙ በሁለት ቀን ውስጥ ከስራ ይባረራሉ። ታዲያ ሁልጊዜ ይህን ጭካኔ ቤት ውስጥ የሚጠቀሙ ከሆነ እንዴት የቤቱ ሕልውናው ሊጠበቅ ይችላል?

ድምፁ ትክክል ካልሆነ ቤተሰቡ ሰላም አይኖረውም። አስተውል በቤት ውስጥ የግዴለሽ ቃላት፣ ከባድ ድምጾችን፣ የትዕቢት ቃላጼዎችና የራስ ወዳድነት አመሎችን የሚገልፁ ቃላትን መጠቀም የለብህም። ፍቅር በድምፅ እንኳን ቢሆን "የማይገባውን አያደርግም "

## ፍቅር እንዲያድግ አድርገው

አንድ ቤተሰብ ውጤታማ እንዲሆን ፍቅር ያለማቋረጥ ማደግ አለበት። እንዲሞት ግን መፍቀድ የለብንም።

## 1. ፍቅርን መግበው

ወጣቶች ፍቅር ሊሞት እንደሚችል ሁል ጊዜ ማወቅ አለባቸው። ፍቅር ሊሞት እንደሚችልና በቀላሉም እንደሚሞት አስባለሁ። ሕይወት እንዳላቸው ነገሮች ሁሉ ፍቅርም ምግብ ይፈልጋል። ምግብ ካጣ ይራባል፣ በመጨረሻም ይሞታል። ስለዚህ መግበው፣ ያድጋል።

ፍቅር የቤተሰብና የጋብቻ መሠረት ነው። ፍቅር ሁለት ሰዎችን ወደ ጋብቻ ይመራል። ፍቅር በቤተሰብ ውስጥ ባንድ ላይ እንዲኖሩ ያደርጋል። በሚገባ ከተመገበ በቀላሉ ያድጋል፣ ከተራበ ግን ይሞታል፡ ብዙዎች ከመጋባታቸው በፊት ፍቅር አላቸው። ከተጋቡ በኋላ ግን መራብ ይጀምራሉ። ስለዚህ ፍቅራቸው ቀስ በቀስ ቢሞት አያስደንቅም። ፍቅር ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነገሮች ለመመገብ ይፈልጋል። እነዚህም መቻቻል፣ መስዋዕትነት፣ ራስን መካድ ፣ መግባባት ፣ ርሕራኄና ይቅር መባባል ናቸው። እነዚህ ነገሮች ተደጋግመው መደረግ ያለባቸው ናቸው። ፍቅር እነዚህን ነገሮች ከተመገበ በጥሩ ሁኔታ ሊያድግ ይችላል። ነገር ግን ሰዎች የሌላውን ደስታ የማይፈልጉ ከሆነና የራሣቸውን ምኞት ብቻ የሚያስቡ ከሆነ ፍቅራቸው ወዲያውኑ በርሃብ ይሞታል።

ያለ ፍቅር ማግባት የሚያም ነው። ያለፍቅር ቤተሰብ እንዲኖር ማድረግ በጣም አሣዛኝ ነው። አንድ ሰው በወጣትነቱ ወይም በጉልምስናው ዘመን ፍቅር ባይኖርም ቤተሰቡን ታግሶ ሊይዝ ይችላል። ነገር ግን በእድሜ ሲሸመግል በቤተሰቡ ውስጥ ፍቅሩ በከባድ ሁኔታ ሊመታ ይችላል። ዘመን በጨመረ ቁጥር ልዩነት እየሰፋ ይሄዳል። ስለዚህ ገና ወጣትና ጎልማሳ ሳለህ ቤተሰብህን ፍቅር መግበው። ይህንም ተለማመድ። ፍቅርህን ለመመገብ ሞክር እንዲያ ብታደርግ ቤትህ በፍቅር ይሞላል።

## 2. ሌላውን የማያስደስቱ ነገሮችን ተው

ሁሉም ያገቡ ሰዎች ሌላው ወገን በጣም የሚፈራቸውንና በጣም የሚጠላቸውን ወይም የማይፈልጋቸውን ነገሮች ለማወቅና ለማግኘት መጣር በጣም ጠቃሚ ስለሆነ የግዴለሽነት ሕይወት አትኑር። ሁሉም ሰው የሚጠላውና የሚፈራው ነገር አለ። ያገባሽው ሰው የምግባር ድክመት ካለበት ሁኔታውን ለማስተካከል የጋራ መቻቻል እንደሚኖር ተስፋ አደርጋለሁ። የምግባር ድክመት ካልሆነ ግን ግማሽ መንገድ ሄዶ በማግኘት ፋንታ ሁሉንም መንገድ እንድትሄዱ እመክራችኋለሁ።

ከብዙ ዓመታት በፊት በዩናይትድስቴትስ የጭካኔ ተግባር ፈፅማብኛለች ብሎ ሚስቱን ስለከሰሰ የአንድ ሰው ታሪክ ሰምቻለሁ:: ታሪኩ አስከቂኝ ቢመስልም የሚያስፈራ ነው:: ባልየው አስልቺ ድምፅ መታገስ አልቻለም:: በመጀመሪያ ጊዜ ባልና ሚስት በጣም ይፈቃቀሩ ነበር :: ነገር ግን ከተጋቡ ሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ የቤተሰቡ ግንኙነት እየቀዘቀዘና እየሻከረ መጣ:: ሚስቱ ሹራብ መስራት ትወዳለች ሹራብ ስትሠራ የሚሠማውን የማሽን ድምፅ ይጠላዋል:: ለ 7 አመት ያህል በዚህ ድምፅ ተሰቃየ:: በመጨረሻም ባለቤቱ በአዕምሮው ላይ ጭካኔ የፈፀመችበት መሆኑን ለመከሰስ ወደ ፍርድ ቤት ሄደ:: ፍርድ ቤቱም ሹራብ መስራቷ ወንጀል ስላልሆነ ለፍቺ በቂ ምክንያት እንዳልሆነ በመግለፅ ፍርድ ቤቱ በጣም ያፈቅራት እንደነበርና እንደ በግ ግልገልም እንደሚጠነቀቅላተ ተናግሯል:: ነገር ግን ከተጋቡ ከአንድ አመት በኋላ ሹራብ መስራቷን በመቀጠሏ ግንኙነታቸው ሻከረ:: ይህም ሰው እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ታግሶ መቆየቱን ተናግሯል:: ዛሬ ግን ይህን የሹራብ ማሽን ድምፅ ታግሶ መሸከም እንዳልቻለና ከዚህም በላይ በፊት እንደሚስቱ ይወዳቸው የነበሩትን የበግ ግልገሎች ሳይቀር የመግደል ስሜት እንዳሣደረበት ገልፆአል:: ለፍርድ ቤቱም ፍቺው ካልተፈቀደለት በመንገድ ላይ ለሚገድላቸው የበግ ግልገሎች በኃላፊነት ሊጠየቅ እንደማይችል ተናግሯል:: ይህ ታሪክ እውነት ነው:: ሚስት ሹራብ መስራቷ ስህተት የለውም ብላ ነበር፥ ነገር ግን ባል የበግ ግልገሎችን እስከ መግደል የሚያደርስ ችግር አመጣበት::

ስለዚህ አስተውል፣ ማንኛውም ሰው የሚጠላውና የሚፈራው ነገር አለ:: ይህ ደግሞ የምግባር ችግር ላይሆን ይችላል:: ይህ የሰውየው ፀባይ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ ቤተሰብ ስኬታማ እንዲሆን ባልም ሆነ ሚስት ለእኛ ምንም የማይመስለን በሌሎች ዘንድ ግን ጉልህ ስፍራ ሊሰጠው ስለሚችል አስተውለን እናድርግ::

በሻንጋይ ከሚኖሩ ብዙ ቤተሰቦች ጋር ተደጋጋሚ ግንኙነት አድርጌአለሁ:: በሌሎች ቦታዎችም እንዳየሁት የቤተሰብ ችግር ሆኖ ያገኘሁት ብዙዎቹ ጉልህ ስፍራ የማይሰጧቸው ነገሮች ናቸው:: በውጭ ላሉና ለጎደኞቻችን እነዚህ ነገሮች በጣም ትንሽ መስለው ሊታዩ ይችላሉ ነገር ግን ያለማቋረጥ በተደጋጋሚ በቤተሰብ ውስጥ ከተከናወኑ አንድ ሰው ያለውን ትዕግስት አሟጠው ሊጨርሱት ይችላሉ::

ሁለት ሰዎች በአንድ ላይ መኖር በጣም እንክብካቤና ጥንቃቄ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን አማኞች ሁሉ ሊያውቁ ይገባል:: ስለዚህ ነገሩ ቀላል ስለሆነ እንደ ትንሽ ነገር መወሰድ የለበትም:: አንተ ጉልህ ነው የማትለው ነገር በትዳር ጓደኛህ ላይ ተፅዕኖ ሊያመጣበት ስለሚችል የአዕምሮ ጭንቀት ሊፈጥርበት ይችላልና አስተውል ::

## ራስ ወዳድ አትሁን

በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ሌላው ጠቃሚ ነገር ራስ ወዳድ አለመሆን ነው።

### 1. ሌላው የሚደሰትበትን ፈልግ

ካገባህ እንዳገባህ ሰው ኑር እንጂ እንዳላገባ ሰው አትሁን። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል "ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፤ልቡም ተከፍሎአል። . . . የተጋባች ግን ባልዋን እንዴት ደስ እንድታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች "/ 1ቆሮ 7÷33-34 /። ቤተሰብን የሚያጋጥመው ትልቁ ችግር ምን አልባት ራስ ወዳድነት ነው።

በዩናይትድ ስቴትስ የሚኖር አንድ ፓስተር አስታውሳለሁ። በሕይወት ዘመኑ 750 ጋብቻዎችን አስፈፅሟል። በእያንዳንዱ የጋብቻ ስነስርዓት ላይ ለእነዚህ አዲስ ተጋቢዎች ራስ ወዳድ እንዳይሆኑ ይመክራቸዋል። በጋብቻ ሕይወት ፍቅር እንጂ ራስ ወዳድነት መኖር የለበትም። ይህ ፓስተር የሕይወት ዘመኑ ሲገባደድ ለእነዚህ ላጋባቸው ሰዎች አንድ የቃለ መጠይቅ ደብዳቤ አሁን ስላሉበት ሁኔታ እንዲገልጹለት ላከ። የሚገርመው ከ 700 በላይ የሚሆኑ ተጋቢዎች አሁንም በትዳራቸው ፀንተው የተገኙ ሲሆን ለዚህም ለቤተሰባቸው ደስተኛ ሕይወት ምክንያቱ ራስ ወዳድ ባለመሆናቸው እንደሆነ ገለፁለት። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በዩናይትድ ስቴትስ የተለመደ አይደለም ምክንያቱም በዚያች አገር ከአራት ጋብቻዎች አንዱ በፍች ይደመደማል።

ስለዚህ ለሌሎች እንዴት እንዲሠማን ልናውቅ ይገባል። የሌሎችን ህመም ወይም ደስታ፣ ፍርሃት ወይንም ጥላቻ፣ ችግር ወይንም ዝንባሌ እንረዳላቸው። እነዚህን ነገሮች የማይረዱ ከሆነ ጥሩ ባል ወይም ጥሩ ሚስት ሊሆኑ አይችሉም። የሌሎችን ሁኔታ የማይረዱ ሰዎች ራስ ወዳዶች ናቸው።

### 2. የምትወደውን መስዋዕት አድርግ

ጋብቻ የሚፈልገው አንዱ መሠረታዊ ነገር መስዋዕትነት ነው። አንዱ ሰው ሌላውን ማስደሰት መቻል አለበት። ይህን ብታደርግ ራስ ወዳድ አትሆንም። እዚህ ላይ ትድሚያ ሊሠጠው የሚገባ ጉዳይ የአንተ መውደድና አለመውደድ ሳይሆን የሌላው ሰው መውደድና አለመውደድ

ነው። ያ ሰው የሚወደውንና የሚጠላውን ሀሳብ ወይም አመለካከቱን ለማወቅ ተግተህ ተከታተል። በሌላው ወገን በኩል ቆመህ የትዳር ጓደኛህንና የራስህን ሁኔታ ተረዳ። በተቻለ መጠን የአንተን ስሜት አመለካከትና አስተያየት ወይም የራስህ የሆነውን ነገር መስዋዕት አድርግ። ሌላውን ለመረዳትና ለማፍቀር ራስህን ተግተህ ተከታተል። በዚህ ዓይነት መንገድ የቤተሰብ ችግሮች በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳሉ።

ብዙ ትዳሮች የሚከተሉት ችግሮች አሏቸው። የቤቱ አባወራ ስለምንም ነገር የማያስብ ነገር ግን ሁሉ ነገር በዙሪያው የሚሽከረከርበት የህዋው አስኳል አድርጎ ራሱን ይቆጥራል። ሚስትም የሚያገባው ሕይወቱንና ምቾቱን እንድትጠብቅለት ብቻ ነው። እንደዚህ ዓይነቱ ቤተሰብ ችግር ይገጥመዋል። ምክንያቱም ጋብቻው የተመሠረተው በራስ ወዳድነት ላይ ነው። እንደዚሁም ሁሉ ሚስትም ራስዋ ሁሉም ሰው የሚኖርበት የሕዋው ማዕከል አድርጋ ራሷን ታስባለች። ስለዚህ ለዓላማዋ መሣካት እንዲያገለግላት ባል ታገባለች። እንደዚህ ዓይነቱ ጋብቻ ተሰባብሮ ይጠፋል፥ ምክያቱም ጋብቻው በራስ ትርፍ ላይ ተመስርቶ የሚንቀሣቀስ ነውና።

## የግል ነፃነትንና የግል ንብረትን ፍቀድ

በቤተሰብ ውስጥ አንዱ ለሌላው የተወሰነ የግል ነፃነትንና የግል ንብረትን መፍቀድ አለበት።

## ቤታችሁ ወህኒ ቤት አይሁን

በአንዳንድ ቤተሰቦች ውስጥ ሚስት በማንኛውም ነገር መብት የላትም። በሌላ በኩል ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ ዘመናዊ ቤተሰቦች ውስጥ ባል መብት የለውም። እንደዚህ ዓይነቱ ቤተሰብ ያለጥርጥር ችግር አለበት። ስለዚህ ባልም ሆነ ሚስት ከወህኒ ቤት በስተቀር ሰውን እንደማይጠሉ ልታውቁ ይገባል።ስለዚህ ለትዳር ጓደኞቻችሁ ወህኒ ቤት ከሆናችሁ ፍቅር አትጠብቁ። ማንም ወህኒ ቤትን ሊወድ አይችልም። ማንም ደግሞ እስረኛ መሆን አይፈልግም። የወህኒ ቤት በር የሚጠብቀውን ዘበኛ ልታፈቅረው አትችልም። ታዲያ አንተ ነፃነት የነፈገህን ሰው እንዴት ልትወደው ትችላለህ? ብዙዎች ባል በሚስቱ ላይ እንደ እስር ቤት ጠባቂ መምሰል እንዳለበት ያስባሉ። እንደዚያ ዓይነቱ ባል ከሚስቱ ፍቅር ቢጠብቅ የእስር ቤት ዘበኛ ከእስረኞቹ ፍቅር እንደመጠበቅ ያህል ነው። ብዙ ትጠብቃለህ እድሉና መንገዱ ግን የለም። በባሏ ላይም ጠባቂ ዘበኛ የሆነች ሚስት የሚገጥማት ነገር ይኸው ነው። ቁጥጥር ፍርሃትን እንጂ ፍቅርን አያመጣም። ሰው ነፃነቱ ሁሉ ተወስዶበት ፍቅር ሊሰጥ አይችልም። ጋብቻ የባልና የሚስትን ነፃነት ያሳጣል ማለት አይደለም። ባል ሁሉንም ነፃነቱን ለሚስቱ መስጠት

የለበትም። ሚስትም እንደዚሁ። ባል ሚስቱ ሁሉንም ነፃነቷን እንድትሰጠው የሚጠብቅ ከሆነ ሊያውቀው የሚገባ ነገር ሚስቱ ከዚያ በኋላ የምትፈራውና የምትጠላው መሆኑን ነው።

## 2. እግዚአብሔር ነፃነት ሰጥቶናል

ማንም ሰው ሙሉ በሙሉ ነፃነቱን ማጣት አይፈልግም። ነፃነት ከሰው ልጆች ባሕርይ አንዱ ነው። እግዚአብሔር ራሱ ነፃነትን ሰጥቶናል። ይህንንም በገነም ደጆች ዙሪያ አጥር እንኳ እንደሌለ ማየት እንችላለን። ይህም ነፃነት ከፋና ደጉን በምታሳውቀው ዛፍ ዙሪያ የኪሩቤል የሚንበለበል ሰይፍ አለመኖሩ ያረጋግጣል። እግዚአብሔር የሰውን ነፃነት ባይፈልግ ኖሮ መልካምንና ክፋን በምታሳውቀው ዛፉ ዙሪያ የኪሩቤልን የሚንበለበል ሰይፍ ባስቀመጠና ሰውም ያን ፍሬ መብላት ባልቻለ ነበር። ነገር ግን እግዚአብር የሰውን ነፃነት አልጣሰውም፣ አልቀማውም። እንደዚሁም ሁሉ ማናቸውም ባሎች ለሚስቶቻቸው አንዳንድ የተወሰነ የምርጫ ነፃነት ሊሰጧቸው ይገባል። ሚስቶችም እንደዚሁ ለባሎቻቸው ሊሰጧቸው ይገባል። ነገር ግን ነፃነቱን ቀምተህ ለእርሱ አንተ የምትወስንለት ከሆነ በምላሹ ከእርሱ የምታገኘው ፍርሃት ወይም ጥላቻ ይሆናል። ነፃነት በሚጠፋበት ጊዜ ጥላቻ ይመጣል። አለዚያም ቢያንስ ፍርሃት ያቆጠቁጣል።

በቤተሰብ ውስጥ ባልም ሆነ ሚስት አንዱ ለሌላው ነፃነት መስጠት አለባቸው። እያንዳንዳቸው የራሣቸው የሆነ ጊዜ፣ ገንዘብና ቁሣቁስ ሊኖራቸው ይገባል። የባልና የሚስት ግንኙነት ስላለ ብቻ እነዚህ ነገሮች ሊነፈጉ አይገባም። ወሰንን ማወቅም ያስፈልጋል። በሌላው ነፃነት ላይ ተፅእኖ ማድረግም ሆነ ወሰንን አልፎ የመሄዱም ችግር ለጊዜው ትንሽ ነገር ቢመስልም የከፋ ውድቀትን ሊያስከትል ይችላል።

## 3. የግል ነፃነትን አክብር

እያንዳንዱ ባልና ሚስት ላገባው ሰው የግል ነፃነት ያለው መሆኑን ተረድቶ ሊፈቅድለትና ሊያከብርለት ይገባል። ይህ ፍፁም መብት ነው። ባል ወይም ሚስት ጣልቃ የማይገቡበት ነፃነት ነው። ይህን ግራ እጅ የቀኝ እጅ ሳያሳውቅ እንዲያደርግ እንደተፈቀደው ማለት ነው። የግለሰቡን መብት መጠበቅን ተለማመድ። ይህም ቤተሰቡ ብዙ ችግሮችን እንዲያስወግድ ይረዳዋል።

## ችግሮችን ማቃለልን ተማር

ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከታቸው ደግሞ የቤተሰብ ችግሮችን እንዴት እንደምናቃልልና እንደምናስወግድ ነው። ባልና ሚስት አንዳንድ

ባል ሚስቱን ቢሰማ ሚስትም ባሏን ብትሰማ ብዙ ችግሮች ሊቃለሉ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ግን ችግሩ ሚስት ለማለት የፈለገችውን ሁሉ ትላለች። ነገር ግን ባሏን አትሰማም። ባልም እንደዚሁ ነው። ነገር ግን ሚስቱን ቢሰማት ይህን በማድረግ ብቻ ችግሩ በቀላሉ እልባት ያገኛል።

ለውይይት በምትቀመጥበት ጊዜ ግንኙነቻችሁን በተጨባጭ ተወያዩባቸው። ከተሸፋፈኑ ግን ስብሰባችሁ ውጤታማ አይሆንም። የንግግራችሁ ዓላማ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለመፈለግ ይሁን፡ትክክለኛው ነገር ምን እንደሆነ ሁለታችሁም ላታውቁ ስለምትችሉ ሁላችሁም እውነቱን ለማግኘት መጣር አለባችሁ። ሁላችሁም መነጋገርና ከዚያም በኋላ መፀለይ አለባችሁ። በፀሎት መፍትሔውን ለማግኘት እሹ። ችግሩ የት ላይ እንደሆነ እንድትረዱ ጌታን ለምኑት። ሁለተኛ በምትፀልዩበት ጊዜ ብዙ ጉዳዮች መፍትሄ ያገኛሉ። የብዙዎች ችግር ተቀምጠው በተጨባጭ አለመደማመጣቸው ነው። ያን ቢያደርጉ ግን ግማሹ ችግራቸው ይቃለላል። ወዲያውኑ የችግራቸውን ትክክለኛ ነጥብ ማግኘት ይችላሉ።

በመጀመሪያዎቹ የጋብቻ ወራት እንደዚህ ዓይነት የቤተሰብ ውይይት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ መካሄድ አለበት። ከዚያ በኋላ ግን አልፎ አልፎ ነው የሚያስፈልገው። ይህም የብዙ ቤተሰቦችን ችግሮች እንድንረዳና መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል። ብዙ ቤተሰቦችም በተሳካ ሁኔታ እንዲጓዙ ይረዳል። በውጤቱም ብዙ ችግሮች መፍትሄ ያገኛሉ።

## ስህተትን አምኖ ይቅርታን መጠየቅ

በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ባልና ሚስት አንዱ ለሌላው ስህተትን በግልፅ መናገርና መጠየቅ ሁል ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ጥፋታቸውን ዝም ብለው ማለፍ የለባቸውም። አንደኛው ወገን ጥፋቱን አምኖ ይቅርታን ሲጠይቅ ሌላኛው ወገን ደግሞ ይቅር ማለት አለበት።

### 1. ኃጢአትን ተናዘዝ

ክርስቲያን ኃጢአት ሲያደርግ መሠረታዊ መመሪያው ኃጢአቱን መሸፈን ወይም ንስሃ መግባት ብቻ አይደለም። ጥፋት ለሰራበት ሰውም መናዘዝ አለበት። ኃጢአትን መሸፈንና አለመናገር ጥሩ አይደለም። ክርስቲያን ኃጢአቱን ለሌላው ይናዘዛል። ይህንና ያን ነገር አድርጌአለሁ ይላል። ለሁሉም ጥፋቶች ኑዛዜ መደረግ አለበት። በቤተሰብ ውስጥ ጥፋት ሲፈፀም ሁል ጊዜ ንስሃና ኑዛዜ መደረግ አለበት።

## 2. ሌላውን ይቅር በል

አንተ ስህተቶችን ስትሠራ ተናዘዝ፣ ይቅርታንም ጠይቅ። ልክ እንደ አንተ ሌላኛው ወገን ስህተት ሰርቶ ይቅርታ ቢጠይቅህ ምን ታደርጋለህ? የአንተ የቤተሰብ ግንኙነት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለህን ዓይነት ግንኙነት እንደሚመስል አስተውል። የትዳር ጓደኛህ ጥፋት ቢሠራ ከመመርመር ይልቅ ይቅር በለው "...ፍቅር በደልን አይቆጥርም "/1ቆሮ 13 ፥5/።

ፍቅር ማንኛውንም ስህተት አይመዘግብም። በዚህ ፋንታ ፍቅር ይቅር ማለትን ይወዳል ። ኃጢአት ይቅር እንደተባለ ወዲያውኑ ይረሳል። ፍቅር በማቴ 18 ላይ ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዳደረገው አያደርግም። ኃጢአትን አይቆጥርም ፣ የይቅርታን መስፈሪያም አይወስንም። እውነተኛ ይቅርታ ጊዜ አይወስድም። ወዲያው ኃጢአት ይቅር እንደተባለ ይረሳል፥ ደስተኛ ቤተሰብ እንዲኖርህ ከፈለግህ የይቅርታ ሕይወትን ተለማመድ።

## የቤተክርስቲያንን ርዳታ አግኝ

ቤተሰብ ችግር ሲገጥመው በቤተሰብ ውስጥ ለችግሩ መፍትሄ ለመፈለግ መሞከር መልካም ነው። ከሁሉ በፊት በቤተሰብ ውስጥ ምክክር፣ ውይይት፣ ኑዛዜና ይቅርታ መኖር አለበት። ወደ ሶስተኛ ወገን ማምጣት ግን ችግሩን ሊያባብሰው ይችላል። ስለዚህ በቀላሉ መፍትሄ ለመፈለግ የተቻለህን ሁሉ አድርግ እንጅ እንዲባባስ አታድርገው ።

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ጉዳዮችን ወደ ቤተክርስቲያን ለማምጣት አትፈልግ ይሆናል። ነገር ግን ይህን ዝም ብለህ በችኮላና በስሜት ብቻ አታድርገው። ባል የሚስትን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልገዋል፣ ሚስትም እንደዚሁ። ሁለታችሁም የችግሩን መፍትሄ ማግኘት ካልቻላችሁ ቤተክርስቲያን እንድትረዳችሁ ልትወስኑት ትችላላችሁ። ዓላማው በቤተክርስቲያን ፊት ለመካሰስ ወይም ለመጣላት ሣይሆን ቤተክርስቲያን ለችግራችሁ መፍትሔ በመስጠት እንድትረዳችሁ ለመጠየቅ ነው። ወደ ቤተክርስቲያን እንድትረዳችሁ ለመጠየቅ ነው። በዚህ ጊዜ ሁለታችሁም ችግራችሁን መናገር አለባችሁ። ሁለታችሁም በፈቃዳችሁ እንዲህ ማለት አለባችሁ " እኛ ክርስቲያኖች የት ላይ እንደተሳሳትን ቤተክርስቲያን እንድትረዳን እንፈልጋለን፣ እኛም እንዴት እንደሚሰማን ለቤተክርስቲያን እንነግራታለን። " ሁለቱም ወገኖች ቤተክርስቲያን እንድትረዳቸው ደስተኛ እስከሆኑ ድረስ ችግራቸው በቀላሉ መፍትሄ ያገኛል። የዚህ ዓይነት ውይይት ዓላማው ብቀላ ወይም የሌላውን ስህተት ለማጋለጥ አይደለም። ነገር ግን ችግሩ የት ላይ እንዳለ በእውነት ለማወቅ ከመፈለግ ላይ ነው።

## በእግዚአብሔር ፊት አብሮ መሆን

የቤተሰብን ችግር ለማቃለልና በአንድ ላይ በደስታ ለመኖር ባልና ሚስት ሁለቱም በአንድ ላይ በእግዚአብሔር ፊት ጥሩ ሕይወት ሊኖራቸው ይገባል። ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በመሆን በአንድ ላይ መፀለይ ያስፈልጋቸዋል። ባለ ትዳሮች በእግዚአብሔር ፊት ለመቆየትና መንፈሳዊ ነገራቸውን ለመወያየት እንደዚህ ዓይነት ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ባልም ሆነ ሚስት የእግዚአብሔርን የብርሃን ፍርድ በደስታ ሊቀበሉ ይገባቸዋል ባል ፊቱን ሊያጠቁር፣ ሚስትም እንደዚሁ ልታደርግ አይገባቸውም። በአንድነት ሕብረት ሊኖራቸው ይገባል። ለፀሎትና በአንድ ላይ ለመወያየት ጊዜ መውሰድ ያስፈልጋል። ጥሩ ቤተሰብ እንዲኖር ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት መኖር አለባቸው።

## ጥሩ ቤተክርስቲያን ከጥሩ ቤተሰብ ይመጣል

እነዚህን ሁኔታዎች የጠቀስነው ወጣት ወንድሞችና እህቶች በቤተሰብ ሕይወታቸው በአንድነት እንዴት መኖር እንዳለባቸው መማር እንዲችሉ ነው። ለኑሮአችሁ ቸልተኞችና ዳተኞች አትሁኑ። እነዚህ ሁኔታዎች ለቤተሰብና ለቤተክርስቲያን ችግር ያመጣሉና እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን አንድ ሰው ከቤተሰቡ ጋር በአንድነትና በፍቅር መኖር ካልቻለ በቤተክርስቲያን ካሉ ወንድሞችና እህቶችም ጋር ተስማምቶ ለመኖር ያስቸግረዋል። ከትዳር ጓደኛው ጋር በቤት ውስጥ ሰላም የሌለው ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዴት ብሎ ሃሌሉያ እያለ ለመዘመር ይችላል ? በጥሩ መንገድ በቤቱ የሚኖር ሰው በቤተክርስቲያንም በጥሩ ሁኔታ ለመኖር ይችላል። በጥሩ ሁኔታ በአንድነት የሚኖሩ ከሆነ ቤተክርስቲያን የሚኖርባት ችግር በጣም አነስተኛ ይሆናል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## ወላጆች

"ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና። መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ናት። እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣፅ አሣድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው። "/ኤፌ 6÷1-4/" ልጆች ሆይ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ። አባቶች ሆይ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው።" /ቆላ 3÷20-21/

### ትልቅ ኃላፊነት

በብሉይ ኪዳን ከመጽሐፈ ምሳሌ በስተቀር ብዙ ስለወላጅነት የሚያስተምር መጽሐፍ ያለ አይመስልም። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ሐዋርያው ጳውሎስ ወላጅ እንዴት ኃላፊነቱን እንደሚወጣ ግልፅ የሆነ ትዕዛዝ ሰጥቷል። ወላጅነት በአዲስ ኪዳን ትኩረት የተሰጠው ነገር ነው። አዲስ ኪዳን እንዴት ልጅ እንደሚሆን ጥቂት ትምህርቶች ቢኖሩትም ስለወላጅነት ከሚያስተምረው ጋር ሲነፃፀር ጠንካራ አይመስልም። በኤፌሶን ምዕራፍ ስድስትና በቆላስያስ ምዕራፍ ሦስት የተፃፈው ቃል ከልጆች ይልቅ በወላጆች ላይ የጠነከረ ነው። እግዚአብሔር ከልጆች ይልቅ በወላጆች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶበታል። ስለሆነም ሰው እንዴት ወላጅ መሆን እንደሚቻል መማር ያስፈልገዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለወላጆች የሚናገረው ቃል ሲጠቃለል የሚከተለውን ይመስላል። ይህም ልጆቻችሁን በምክርና በጌታ ቃል አሳድጉአቸው እንጅ ልባቸው እንዳይዝል አታስቆጡአቸው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ወላጆች ራሳቸውን መግዛትን መለማመድ አለባቸው። ወላጆች ራሳቸው የጌታን ስርዓትና ትምህርት ማወቅ ይገባቸዋል። ሐዋርያው ጳውሎስም የሚናገረው ስለዚሁ እዉነት ነው።

ስለዚህ አማኞች በተለይም ደግሞ ወላጆች ባል ወይም ሚስት መሆን ቀላል እንዳልሆነ ሁሉ አባት ወይም እናት መሆን ደግሞ የበለጠ ክባድ እንደሆነ ሊያውቁ ይገባል። ባል ወይም ሚስት መሆን በአብዛኛው ጉዳዩ የራስ ነው። ወላጅ መሆን ግን በሌሎችም ሕይወት ላይ ተፅዕኖ አለው። ባል ወይም ሚስት መሆን ያገቡትን ወገን የግል ደስታ ብቻ የሚነካ ነው። ነገር ግን ወላጅ መሆን በሚመጣው ትውልድ ደስታ ላይ ተፅዕኖ አለው። የልጆች የወደፊት ሁኔታ በወላጆቻቸው ላይ የተመሠረተ ነው። ስለዚህ የወላጆች ኃላፊነት ትልቅ ነው። እግዚአብሔር የልጆቻችንን አካል፣ ነፍስ፣ ሀሳብ፣ ኑሮና የወደፊት ሁኔታ በእጃችን ሰጥቶናል። ወላጅ

በልጆቹ የወደፊት ሁኔታ ላይ ተፅዕኖ የሚያሣድረውን ያህል ማንም ሰው የሌላን ሰው የወደፊት ሕይወት መወሰን አይችልም። ወላጆች አብዛኛው ልጆቻቸውን በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማያት ወይም ወደ ሲኦል መንዳት ይችላሉ። ስለዚህ የወላጆች ኃላፊነት በጣም ታላቅ ነው። ስለሆነም ወገኖች ጥሩ ወላጆች ለመሆን ጥሩ ባልና ሚስቶች መሆንን መማር አለባቸው። የወላጅነት ኃላፊነታቸው ከባልና ከሚስት ኃላፊነታቸው ይከብዳል።

እንዴት ክርስቲያን ወላጅ እንደሚሆን የሚረዱ ጥቂት ነጥቦችን ከዚህ ቀጥለን እናያለን።

## <u>ራስህን ቀድስ</u>

ወላጅ የሆኑ ሁሉ ለልጆቻቸው ሲሉ ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት መቀደስ አለባቸው።

### 1. <u>ጌታ ራሱን ቀድሷል</u>

በጌታ ፊት መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው? ጌታ ኢየሱስ ለእኛ ሲል ራሱን ቀድሷል። ይህ ግን የሚያመለክተው ቅዱስነትን ሳይሆን መለየትን ነው። ጌታ ኢየሱስ በባህርይው ቅዱስ ነው። ነገር ግን ለቤተክርስቲያን ሲል ራሱን የበለጠ ቀደሰ፣ ለየ። ይህም ማለት በእርሱ በራሱ ቅዱስ ባህርይ ያለምንም ጥያቄና ድርድር ብዙ ነገሮችን ማድረግ ሲችል ለደካሞች ደቀመዛሙርቱ ሲል ከማድረግ ተቆጥቧል። የደቀ መዛሙርቱ ድካም ጌታ ኢየሱስ በብዙ መንገድ የሚኖረውን ነፃነቱን አግዶታል፣ ወስኖታልም። ብዙ ነገሮችን ለማድረግ በራሱ ነፃ ቢሆንም እንኳ ደቀ መዛሙርቱ ሊረዱ ስለማይችሉ እንዳይደናቀፉ ስጋት ስለአደረበት ብዙ ነገሮችን ከማድረግ ራሱን ገትቷል። ባሕርይውን በተመለከተ በነፃነት ሁሉን ማድረግ ይችላል፣ ነገር ግን ለደቀመዛሙርቱ ሲል አላደረገም።

### 2. <u>ራስህን ቀድስ</u>

በተመሣሣይ ሁኔታ ሁሉም ወላጆች ለልጆቻቸው ሲሉ ራሳቸውን መቀደስ አለባቸው። ይህም ማለት ብዙ ነገሮች ሊያደርጉ ነፃነት አላቸው። ነገር ግን ለልጆቻቸው ሲሉ ማድረግ የለባቸውም። ለልጆቻቸው ሲሉ ብዙ ቃላትን አይናገሩም። ሕፃን ልጅ ወደ ቤተሰብ ከመጣበት ቀን ጀምሮ ወላጆች ራሳቸውን መቀደስ ያስፈልጋቸዋል።

ራስህን መቆጣጠር ካልቻልህ እንዴት ልጆችህን ልትቆጣጠር ትችላለህ? ራስህን መግዛት ካልቻልህስ እንዴት ልጆችህን ማስተዳደር ትችላለህ? ልጅ የሌለው ሰው ራሱን መቆጣጠር ባይችል የሚጎዳው ራሱን ብቻ ነው። ልጅ ያለው ሰው ግን ልጆቹንም ራሱንም ይጎዳል። ስለዚህ ክርስቲያን የልጅ አደራ እንደተሰጠው ወዲያውኑ ራሱን መቀደስ አለበት። በቀረው የሕይወት ዘመኑ ሁለት ወይም አራት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ጥንድ አይኖች ይከታተሉታል፣ ይመለከቱታል። ይህን ዓለም ከለቀቀ በኋላ እንኳ እነዚያ ዓይኖች ያዩትን ነገር ያለማቋረጥ ያስታውሳሉ።

## 3. በትልቁ ደረጃ መሠረት ኑር

ልጅህ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ ራስህን ለጌታ ቀድስ። ለራስህም የምግባር ደረጃ ማስቀመጥ ይኖርብሃል። ይህም ደረጃ በቤትህ ውስጥ የምትተዳደርበት ነው። ማለትም የአንተን ባሕርይ፣ የአንተን ውሳኔ፣ የአንተን ሀሳብና መንፈሣዊ ሕይወትህን የምትመራበት ነውና። ከዚህ ደረጃ ሳትወርድ በጥንቃቄ ልትኖር ይገባል። አለበለዚያ ግን ልጅህንም ራስህንም ታጠፋለህ። ብዙ ልጆች በወላጆቻቸው ጠፍተዋል። ምክንያቱም ወላጆቻቸውም ስለአስተሳሰባቸው ወይንም ስለ መንፈሳዊ ነገራቸው መመዘኛ የሚሆን የምግባር ደረጃ ይጎድላቸዋልና ነው።

የልጆች የወደፊት ግምገማና ነገሮችን የመመዘን መንገድ የሚማሩት ከወላጆቻቸው ነው። ልጆች የምትነግሯቸውን አይሰሙም፣ ያዩትን ግን አይረሱም። ከእናንተ በማየት ይማራሉ።

ወላጆች መንገዳቸውን ልጆቻቸው እንደሚከተሉት ሊያስተውሉ ይገባል። ከማግባታችሁ በፊት ስሜታችሁ በሚነዳችሁ መሠረት ትመሩ ይሆናል። ልጅ ከመጣ በኋላ ግን ትወሰናላችሁ። ነፍሳችሁ አዘነም፣ ተደሰተም ትልቁን ደረጃ መከተል አለባችሁ። ምክንያቱም የልጆቻችሁ የወደፊት ሁኔታ በክርስቲያን ወላጆች ይመሠረታልና ነው።

በአንድ ወቅት አንድ ወንድም የተናገረውን አስታውሳለሁ። ልጁ ችግር ውስጥ ነበር። ስለሆነም ይህ ወላጅ "እሱ ማለት እኔ ነኝ፣ እኔም ማለት እሱ ነው" ብሏል። ይህ አባባል ፍፁም ትክክል ነው። ብዙ ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸው ችግር ውስጥ ሲሆኑ ራሳቸውን በልጆቻቸው ማየት ይችላሉ። ልጆች የወላጆቻቸው ነፀብራቅ ናቸው።

አማኞች ልጆች በሚኖሩአቸው ጊዜ ራሳቸውን ለጌታ እንደገና እንዲቀድሱ ለመናገር እፈልጋለሁ። ነፍሳቸውን፣ ሕይወታቸውንና የወደፊት ልጆቻቸውን ለጌታ እንዲሰጡ በዚህም አቋማቸው የወለዷቸው ታማኞች እንዲሆኑ ያስፈልጋል። ብዙ ዓይነት ሰራዎች ባንድ ወይም

በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊከናወኑ ይችላሉ፣ የወላጅነት ሥራ ግን የጊዜ ገደብ የሌለው የዕድሜ ልክ ሥራ ነው።

4. በልጆችህ ላይ የባለአደራ ስሜትን አዳብር

የሥራ ወይም የጋብቻ ውድቀት ከወላጅነት ውድቀት ጋር በፍፁም ሊወዳደሩ አይችሉም። ለምን? ምክንያቱም አንድ ሰው ካደገ ራሱን በሚገባ መከላከል ይችላል፡ ነገር ግን ለአንተ የተሰጡ ልጆች ራሳቸውን መከላከል አይችሉም። ወደ ጌታ ሄደህ እንዲህ ማለት ትችላለህን? "ጌታ ሆይ አምስት ልጆች ባደራ ሰጥተኸኝ ነበር፣ ነገር ግን ሶስቱ ጠፍተዋል። "ወይም "አሥር ልጆች ታምነህብኝ ሰጥተኸኝ ነበር፣ ነገር ግን ስምንቱ ጠፋብኝ "እንዲህ ዓይነቱ የባለ አደራነት ስሜት ከጠፋ ቤተክርስቲያን ጠንካራ ልትሆን አትችልም። ላንተ የተሰጡህ ወይም የተወለዱልህ ልጆች ከጠፉ ወንጌል እንዴት ለዓለም ሊሠራጭ ይችላል? በሌሎች አለማውያን ለመተካት ታስባለህ ? ስለዚህ ቢያንስ የራስህን ልጆች ወደ ጌታ አምጣ። በጌታ ምክርና ተግሣፅ አለማሳደግ ስህተት ነው። አስተውል ልጆችን ወደ ጌታ ማምጣት የወላጆች ኃላፊነት ነው።

ለቤተክርስቲያን መጥፎ ውድቀት ተጠያቂዎች ወላጆች ናቸው። ማንም ወላጆችን የመቆጣጠር ስልጣን የለውም፣ ልጆች ሊቆጣጠሩአቸው አይችሉም። ራስህን በግዴለሽነት የምትመራ ከሆነ ልጆችህንም ልቅና ስድ ታደርጋቸዋልህ። ለወላጆች ራሣቸውን መቆጣጠር በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። የራሣቸውን ነፃነት መተውም ያስፈልጋቸዋል። አለበለዚያ ግን እንዴት በእግዚአብሔር ፊት መቆምና በእጃቸው የተሰጧቸውን ነፍሳት ማቅረብ ይችላሉ?

## አካሄድህን ከእግዚአብሔር ጋር አድርግ

ሁሉም ወላጆች ኃላፊነታቸውን ማወቅና ለልጆቻቸው ሲሉ ራሳቸውን መቀደስ ብቻ ሳይሆን አካሄዳቸውንም ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ አለባቸው።

1. በሕይወትህ ቅዱስ ሁን

አንድ ሰው ለልጆቹ ሲል ራሱን መቀደሱ ትክክል ነው። ነገር ግን ይህ ሰው ያደረገው ለልጆቹ ሲል ብቻ እንደሆነ አያመለክትም። ጌታ ኢየሱስ ቅዱስ ነው፣ ለደቀመዛሙርቱ ሲል ግን ራሱን ቀደሰ። ለደቀመዛሙርቶቹ ሲል ራሱን ከመቀደሱ በፊት ቅዱስም ነበር። እንደዚሁም ሁሉ ለልጆቻቸው ሲሉ ራሳቸውን የቀደሱ ወላጆች

በማናቸውም ጊዜ አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ አለባቸው።

ነገር ግን አዳንዳድ ጊዜ ሞቅ ሲልህ ወይም በስሜት ተገፋፍተህ የእግዚአብሔር ሰው መስለህ ልትታይ ትችል ይሆናል። ነገር ግን ልጆችህ በትክክል አለመሆንህን በአንተ ውስጥ ፈጥነው ያውቃሉ ፥ ያያሉም። ስለዚህ የምታታልለው ራስህን እንጅ እነርሱን አይደለም። በእነርሱ ፊት ጠንቃቃ እየሆንክ ብቻህን ስትሆን ግን ዘልዛላ ከሆንህ ልጆች በቀላሉ ዘልቀው በመግባት የአንተን ሁኔታ ያውቁታል። በዚህ ምክንያት ራስህ መቀደስ ያለብህ በእነሱ ፊትና ለእነርሱ ስትል ብቻ ሳይሆን በፊተኛውም በእግዚአብሔር ፊት በእውነት ቅዱስና ከዓለም የተለየህ ልትሆን ይገባሃል። ሄኖክ እንዳደረገው አንተም አካሄድህን ከእግዚአብሔር ጋር አድርግ።

## 2. ሄኖክ ልጅ ከወለደ በኋላ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ

"ሄኖክም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ኖረ፣ ማቱሳላንም ወለደ። ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣ ማቱሣላንም ከወለደ በኋላ የኖረው ሁለት መቶ አመት ሆነ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ "/ዘፍ 5፥21-22/ ሄኖክ ከአንድ መቶ ስድሳ አምስት ዓመት በፊት ስለነበረው ሁኔታ የምናውቀው ነገር የለም። ነገር ግን ማቱሣላን ከወለደ በኋላ እስኪወሰድ ድረስ ሁለት መቶ አመት አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳደረገ እናውቃለን።

ይህ በብሉይ ኪዳን ፍፁም የተለየ ነው። የቤተሰብ ሸክም በሄኖክ ላይ በመጣ ጊዜ ራሱ ብቃት እንደሌለው እያየ መጣ። ኃላፊነቱ ከባድ እንደሆነ ተሰማው። ስለዚህ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ። መጽሐፍ ቅዱስ ሄኖክ በልጁ ፊት ብቻ አካሄዱን ከእግዚአብሔርጋር አደረገ አይልም። እርሱ ራሱ ብቻውን ሳለም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ነበር። አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ካላደረገ ልጁን መምራት እንደማይችል የተረዳ ሰው ነበር። ሄኖክ በእነዚህ ሁለት መቶ ዓመታት ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አግኝቷል። ይሁን እንጅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረጉን አላቋረጠም። ወላጅነት አንድን ሰው አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳያደርግ አያግደውም። እንዲያውም የበለጠ እስኪነጠቁ ድረስ አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያደርጉ ያበረታቸዋል እንጂ። አስተውል በመጀመሪያ የተነጠቀው አባትዮው ነበር። ይህም የተነጠቀ ሰው ብዙ ልጆች ነበሩት። ይሁን እንጂ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያደርግ አይከለክሉትም ። የቤተሰብ ኃላፊነትን

መሸከም ያንድን ሰው መንፈሳዊ ሁኔታ በእግዚአብሔር ፊት የበለጠ ይገልጠዋል።

## 3. ሁለት ዓይነት ደረጃዎች አይኑሩህ

ልጆችን ወደ እግዚአብሔር ለመምራት አንተ ራስህ አካሄድህን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ አለብህ። ልጆችህን ወደ መንግስተ ሰማያት መምራት የቻልህ መስሎህ የማታምንበትን ጣቶችህን ወደ መንግስተ ሰማያት አትቀስር። አንተ ራስህ አስቀድመህ ሂድ። እነርሱም ይከተሉሃል። የብዙ ክርስቲያን ቤተሰቦች ውድቀት ምክንያት ወላጆች ልጆቻቸውን ከእነሱ የተሻሉ እንዲሆኑ መፈለጋቸው ነው። እነርሱ ራሳቸው ከዓለም ጋር ተጣብቀው ልጆቻቸው ዓለምን እንዳይወዱና ጌታን ተከትለው እንዲሄዱ ይሻሉ፣ ይጠብቃሉ። እንደዚህ ዓይነቱ መሻት ዋጋ የሌለው ነው። ስለዚህ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር አንድ ዓይነት ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል። አንተ የማትኖርበት ደረጃ ለልጆችህ ማውጣት አትችልም። በመንፈሣዊ ነገር የምትከተለው ደረጃ የልጆችህም ደረጃ እየሆነ ይመጣልና። አንድ ወቅት አንድ ቤተሰብ ጎብኝቸ ነበር። ለዚህም ምስክር ነኝ። እናት ልጇ ስለዋሸ ደበደበችው። ነገር ግን የዚህ ቤተሰብ እናትና አባት የሚገርመው ነገር ውሸት የሚናገሩ ናቸው። ብዙ ጊዜ ሲዋሹ አግኝቻቸዋለሁ። ልጃቸው በዚህ ነገር ተደበደበ። ልጁ የተደበደበው ውሸት በመናገሩ አይደለም። በወላጆቹ አቋም ልጁ የተጠቀመበት የውሸት ዘዴ አለመሣካቱ ነው። በሌላ አባባል ልጁን ያስገረፈው ነገር መዋሸቱ ሳይሆን ውሸቱ መገለጡ ብቻ ነው። በዚያ ቤት ሕይወት ውሸት ከተደረሰበት ወይም ከተረጋገጠ ልጁ ይቀጣል። እንደዚህ ዓይነት ሁለት የኑሮ ደረጃ እየተለማመድህ እንዴት ልጆችህን ልትረዳ ትችላለህ ? አንተ ራስህ እየዋሸህ ልጆችህን አትዋሽ ማለት ትችላለህን? እነሱን መከልከሉ ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው ?አንተ በአንድ ደረጃ እየኖርህ ለልጆችህ ደግሞ ሌላ ደረጃ ከሰጠህ ምንም ነገር ሊከናወን አይችልም። ልጆች የሚቀበሉት ካንተ የሚያዩትን ብቻ ነው። ውሸትና አለመታመንን ካዩብህ የፈለገውን ያህል ብትገርፋቸውም ታባብሣቸዋለህ እንጅ ከዚያ ፈቀቅ አይሉም። ይህም አንድ አባት ልጆቹ እራሳቸውን ችለው መኖር ሲጀምሩ ሲጋራ ማጨስ እንደሚፈቀድላቸው የመናገርን ያህል ነው። ውሸት በሚነገርበት ቤት ውስጥ ያሉ ልጆች ራሳቸውን ችለው ከወላጆቻቸው ሲለዩ መዋሸት እንደፈቀድላቸው ያስባሉ። አሁን ውሸት መናገር ስለማይችሉ ከወላጆቻቸው ቤት እስኪወጡ ይጠብቃሉ ። ያን ጊዜ ግን ለመዋሸት ነፃ ናቸው።በዚህ ዓይነት መንገድ መራመድ ልጆችህን ወደ ዓለም መገፍተር ነው። ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳደረገ አንተም አካሄድህን ከእግዚአብሔር ጋር ብታደርግ ሄኖክ ልጁን እንደ መራው አንተም መምራት ትችላለህ። አንተ በዚያ መንገድ ካልሄድህ ልጆችህን መምራት አትችልም።

አስተውል ልጆች በተፈጥሯቸው አንተ የምታፈቅረውን ያፈቅራሉ። አንተ የምትጠላውን ይጠላሉ። አንተ ዋጋ የምትሠጠውን ዋጋ ይሠጡታል፣ አንተ የምትኮንነውን ይኮንኑታል። ስለዚህ አንድ የምግባር ደረጃ ላንተም ለልጆችህም ይኑርህ። ያንተ የምግባር ደረጃ ምንም ይሁን ምን የልጆችህም ነው። እግዚአብሔርን ስለመውደድ ያወጣሃው ደረጃ እነርሱም እግዚአብሔርን የሚወዱበት ደረጃ ነው። አንተ ለእግዚአብሔር በሆንከው መጠን እነርሱም ይሆናሉ። በቤተሰብ ውስጥ አንድ ደረጃ ብቻ ነው ሊኖርህ የሚችለው፥ሁለት ደረጃ ሊኖር አይችልም ።

አባትየው የይስሙላ ክርስቲያን የሆነበት አንድ ቤተሰብ አውቃለሁ። እርሱ ቤተክርስቲያን አይሄድም።ነገር ግን ልጆቹ ሁል ጊዜ እሁድ ጠዋት ለመባ የሚሆን ገንዘብ ይዘው እንዲሄዱ ይሰጣቸዋል። ከዚያም እርሱ ከሶስት ጓደኞቹ ጋር በመሆን ቁማር ይጫወታል። መጨረሻም ልጆቹ የሚሰጣቸውን ገንዘብ ኬክ ቤት ያጠፉት ጀመር። የቤተክርስቲያኗ ፖስተር ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ያንቀላፋሉ፣ ትምህርት አቋርጠውም ለጨዋታ ይወጣሉ። ስለሆነም እነዚህ ልጆች ማድረግ የሚችሉት መብላት፣ መጫወትና ቤተክርስቲያን የሄዱ መሆናቸውን ሪፖርት ማድረግ ብቻ ነው። በእርግጥ ይህ ከባድ ችግር ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለአንተ ልጆች ሲሰጥህ በቤተሰብ ውስጥ አንድ ደረጃ ብቻ ሊኖርህ ይገባል። አንድ ጊዜ ደረጃ ከወጣ ሁል ጊዜ ያን ደረጃ መጠበቅ አለብህ። አስተውል ልጆች ሁል ጊዜ የምታደርገውን ያያሉ እንጂ የምትነግራቸውን አይሰሙም። የምታደርገውን ስለሚያዩ የት ላይ ትክክል እንዳልሆንህ ያውቃሉ። እነርሱን ማታለል አትችልም። ምክንያቱም የአንተ ሀሳብና እውነተኛው ማንነትህ ምን እንደሆነ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው።

ሄኖክ ማቱሣላን ከወለደ በኋላ ለሁለት መቶ ዓመታት አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረጉ እንዴት በጣም ደስ የሚል ምሳሌ ነው። ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አግኝቷል። በዘመኑ ሁሉ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አድርጎ ነበር። ምንም ነገር የማይሸቃቅጥ እውነተኛ አባት በእግዚአብሔርም ፊት ፍፁም ነበር።

## ወላጆች አንድ አቋምና ሀሳብ ሊኖራቸው ይገባል

አንድ ቤተሰብ ፅኑ እንዲሆን ክርስቲያን አባትና እናት አንድ ሀሳብና አቋም ሊኖራቸው ይገባል። ለጊታ ሲሉ የራሳቸውን ነፃነት መስዋዕት ለማድረግና የማይጣስ የምግባር ደረጃ ለማውጣት መስማማት

አለባቸው። ከዚያ በኋላ ግን አባትም ይሁን እናት የተለየ አቋም ሊኖራቸው አይችልም።

ብዙ ጊዜ እናትና አባት ባንድ ላይ ካለመቆማቸው የተነሳ ልጆቻቸው ኃጢአትን እንዲያደርጉ ክፍተት ይፈጥራሉ። ወላጆች ካልተስማሙ ለልጆቹ አንድ ግልፅ አቋም ለመከተል አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። አባት "ይሁን" ሲል እናት "አይሆንም" የምትል ከሆነ ልጆች የሚመርጡት የሚመቻቸውን ነው። ይህም በአባትና በእናት መካከል ያለውን ልዩነት ያጎላዋል።

ሁለት የሸመገሉ ክርስቲያን ባልና ሚስት አውቃለሁ። ሁለቱም የየራሳቸው ኃሳብ አላቸው። በዚህ ምክንያት ጥሩ ባልና ሚስት ወይም ወላጅ ሊሆኑ አልቻሉም። ልጆቻቸውያባንድ ጉዳይ ላይ በእውቀታቸው መሠረት ጥሩ የመሠላቸውን ያፀድቅልኛል የሚሉትን ወላጅ ይጠይቃሉ። እናት ወደ ቤት መጥታ ለምን ይህን ነገር አደረጋችሁ ብላ ስትጠይቃቸው ቀደም ሲል አባታቸውን ጠይቀው እንደነበር መልስ ይሰጣሉ። አንዳንድ ጊዜም ነገሩን ያዟዙሩታል፣ በእናትና በአባት የውጊያ ሜዳ ላይ ልጆች የራሳቸውን ጨዋታ ይጫወታሉ። እንዲህ በማድረግም ብዙ ነፃነት ስለሚያገኙ ይደሰቱበታል። ከሃያ ዓመት በፊት ይህ ዓይነት ሁኔታ አጋጥሞኝ ነበር ። እኔም እናትና አባት በዚሁ ሁኔታ ከቀጠሉ ልጆች በጌታ ሊያምኑ እንደማይችሉ እነዚህን ወላጆች ነግሬያቸው ነበር። ነገር ግን በወቅቱ በቀረበው ሀሳብ ላይ አልተስማሙም። ዛሬ ልጆቻቸው በሙሉ አድገዋል። አንዳንዶች ኮሌጅ ገብተዋል ፣ ሌሎች ደግሞ ውጭ እየተማሩ ናቸው። ነገር ግን አንዳቸውም በጌታ አያምኑም። በልጆች መካከል ችግር ሲፈጠር ወላጆች አንድ አይነት ስምምነትና ሀሳብ ቢኖራቸው በጣም ይጠቅማል። ለልጆቻቸው አንድ ሀሳብ ወይም አቋም ሊያቀርቡላቸው ይገባል። ሁኔታዎች ምንም አስቸጋሪ ቢሆኑ አንድ ነገር ለማድረግ ወደ አንተ የመጣውን ልጅ እናቱን ጠይቆና አልጠየቀ እንደሆነ በመጀመሪያ አነጋግረው። ጠይቆ ከሆነ እናቱ ምን እንዳለችው አረጋግጥ። እናትም ከሆነች ቀደም ሲል አባቱን ጠይቆ እንደሆነ ታረጋግጥ። ጠይቆም ከሆነ አባቱ ምን እንዳለ ትወቅ። ከዚያም አባትም ይሁን እናት ለጥያቄው የሰጡት መልስ ትክክልም ይሁን ስህተት ይሆኛው ወገን ግን አንድነትን መጠበቅ አለበት። መነጋገር የሚያስፈልገው ከሆነ ባልና ሚስት ብቻቸውን ሆነው በመነጋገር መፍትሄ ይፈልጉለት። ለልጆች ክፍተት አትፍጠርላቸው። ክፍተት ካገኙ የሚያስደስታቸውን ስለሚያደርጉ ሁል ጊዜ ክፍተትን ይፈልጋሉ። ልዩነታችሁን በግል ልታስወግዱ ትችላላችሁ። ልታስወግዱም ይገባል። ነገር ግን ልጆች በመካከላችሁ ክፍተት እንዲያገኙ አትፍቀዱላቸው። እንደዚያ ብታደርጉ ልጆቻችሁን በቀላሉ ወደ ጌታ ማምጣት ትችላላችሁ።

## የልጆችን መብት አክብር

ልጆችን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ የተባለ ነገር አለ ። ይህም ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ናቸው የሚልነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ንብረቶች ናቸው። አንድ ቀን እነዚህን ንብረቶች እንድትመልስ ትጠየቃለህ። በዚህ ጊዜ "የእኔ ናቸው " ማለት አትችልም። ልጆች ሙሉ በሙሉ የአንተ እንደሆኑና ትልቅ ሰው እስኪሆኑ ድረስ በእነርሱ ላይ ያልተወሰነ ስልጣን እንዳለህ አድርገህ አታስብ። እንደዚያ ዓይነቱ አስተሳሰብ የአህዛብ እንጂ የክርስቲያን አይደለም። ክርስትና ልጆች የአንድ ሰው የግል ንብረቶቹ እንደሆኑ አድርጎ አይቀበልም። ይልቁንም ክርስትና ልጆች የመለኮታዊ አምላክ ርስት እንደሆኑ ያረጋግጣል። እስከሚፈለገው የዕድሜ ደረጃ አድገው በራሳቸው መኖር እስከሚችሉ ድረስም ቢሆን ተቀናቃኝ የሌለውን ፅኑ የወላጅ ሕግ በእነርሱ ላይ አይጭንም።

### 1. የወላጅ ስልጣን ያልተወሰነ አይደለም

አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያን ከሆኑ በኋላም ወላጆች ሊሳሳቱ አይችሉም የሚል ሀሳብ አላቸው። ይህንንም ግትር ሀሳብ ይዘው ያሉ አሉ። ነገር ግን ዓለም ብዙ የተሳሳቱ ወላጆች ይዛ ትታያለች። ይህን ስናገር አዝናለሁ። በተደጋጋሚ ወላጆች ስህተት ውስጥ ይወድቃሉ። በልጆቻቸው ላይ ያልተወሠነ ስልጣን እንዳላቸው አድርገው የሚፈፅሙት ድርጊት ትክክል አይደለም። በዚህ ጉዳይ ላይ የተሳሳተ ኃሳብ ሊኖረን አይገባም።

አስተውል ገደብ የለሽ ስልጣን አልተሰጠህም። ፍፁም ልትቆጣጠረው የማትችል ነፍስ ለልጆች ተሰጥቷል። ይህም ነፍስ የልጆች ነው። ለእነርሱም ይገባል። በመጨረሻም ወደ መንግስተ ሰማያት ወይም ወደ ገሃነም ሊሄድ ይችላል። ይህ በእግዚአብሔር ፊት የልጁ ኃላፊነት ነው። ልጅህን እንደ እቃ ወይም እንደ ቁሣቁስ አድርገህ ልታየው አትችልም። እግዚአብሔር በልጆችህ ላይ ገደብየለሽ ስልጣንን አልሰጠህም። እግዚአብሔር ያልተወሰነ ሥልጣን የሰጠህ በግኡዝ ነገሮች ላይ ነው። በነፍሣት ላይ ግን አይደለም። ማንም በሌላ ነፍስ ላይ ፍፁም ስልጣን የለውምና።

### 2. ልጆችህን አታስፈራራ

ከማንኛውም ሰው ጋር በጥሩ ሁኔታ ትግባባለህ። ከወዳጆችህ፣ ከዘመዶችህ ጋር ሚዛናዊ ነህ በተለይም ለአለቃህ ትሁትና አክባሪ ነህ። ነገር ግን ልጆችህን እንደግል ንብረት ታያቸዋለህ። ከእግዚአብሔር የተሰጡህ ነፍሳት መሆናቸውን ትረሳለህ። የአንተን መጥፎ ዐመል

በእነርሱ ላይ ታወርድባቸዋልህ። ደስ የሚያሰኝህንም ታደርግባቸዋለህ። ከልጆችህ በስተቀር ለማንኛውም ሰው ትሁት ትመስላለህ። ቁጣህን የምታወርድባቸው ሰዎች ሆነዋል። እንዲህ ዓይነት ብዙ ወላጆች አውቃለሁ። አንዳንድ ሰዎች ሁል ጊዜ ትሁትና ጨዋ የማይቆጡ ከሆኑ ደስተኛ አይሆኑም፣ ከሰውነት ደረጃ የወረዱ የሚመስላቸው አሉ። ስለሆነም የእነሱን መጥፎ አመል የሚገልጡባቸውን ሰዎች ይፈልጋሉ። ይሁንም እንጂ ወደ ስራ ባልደረቦቻቸው ቢያዞሩ ባልደረቦቻቸው ይሸሿቸል፣ ባለቆቻቸው ላይ ቢያደርጉ ከስራ ያባርሯቸዋል፣ በወዳጆቻቸው ላይ ቢያደርጉ ይነቅፏቸዋል። ስለዚህ ያለምንም ፍርሃት ቁጣቸውን ሊያሣርፉበት የሚችሉበት የተመቸ ቦታ ሆኖ የሚያገኙት ልጆቻቸውን ብቻ ነው። ስለሆነም ብዙ ወላጆች ክፉ አመላቸውን በልጆቻቸው ላይ ይገልጣሉ።

ጠንከር ያለ ነገር በመናገሬ ይቅርታ አድርጉልኝ። ምክንያቱም በልጆቻቸው ላይ የሚጨክኑና በሌላ በኩል ደግሞ ወደ እኔ ዘወር ብለው "ሚስተር ኒ ይህ ምግብ ግሩም ነው፣ እባክህ ብላለን " የሚሉ ብዙ ሰዎች ስላየሁና ስላጋጠሙኝ ነው። እንዴት በዚህ ሁኔታ ልመገብ እችላለሁ? እነዚህ ወላጆች ልጆቻቸውን የሚያዩት ቁጣቸውን የሚገልፁባቸው የመብት እቃቸው አድርገው ነው። እግዚአብሔር ልጆችን ለምንድን ነው የሰጠው? ቁጣችንን እንድናሣርፍባቸው ነውን? እግዚአብሔር ይማረን።

እግዚአብሔር የልጆችን መብት ሁሉ ባዶ አላደረገውም ክብራቸውንና ነፃነታቸውን አላጠፋም። የግል ማንነታቸውን አላጠፋም ለእናንተ በእጃችሁ ሲሰጣችሁ የሚያስደስታችሁን ነገር እንድታደርጉባቸው ወይም እንድትደበድቧቸው አይደለም። በዚህ በኩል ነፃነት የላችሁም። ይህን የምታስቡ ከሆነ እንደዚህ ዓይነቱ ሀሣብ የክርስቲያን አይደለም። በእግዚአብሔር ፊት ላንተም ሆነ ለልጅህ ተግባራዊ የሆነው አንድ ዓይነትና ትክክል ወይም ስህተት የሚል ደረጃ ነው። ላንተ ሌላ ለልጅህ ደግሞ ሌላ የሚል ደረጃ የለም። አሁን አስተዋልህ፥ አማኞች ለልጆቻቸው ትሁትና ጨዋ እንዲሆኑ ልነግራቸው እወዳለሁ። ልጆቻቸውን ሲያስተዳድሩ ነውረኛና ግዴለሽ እንዲሆኑ አያስፈልግም ።

ነውረኛና ግዴለሽ መሆን የአንድን ሰው ልጅ ጋጠወጥ ያደርገዋል። በክርስትና ሕይወት ያደገ ማንኛውም ሰው ራሱን መግዛት መቻል አለበት። በተለይም ልጆቹን በተመለከተ ራሱን መግዛት መጀመር አለበት። ይህም የልጆቹን ነፍስ በማክበር ነው። ልጆች ምንም ትንሽና ደካማ ቢሆኑ የግል ነፃነት አላቸው። ይህን እግዚአብሔር ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ ማንም መብታቸውን ሊነፍጋቸው አይገባም።

ልጆች ባደራ የተሰጡ ወራሾች ናቸው። የእነርሱ የምግባር ደረጃ የሚመጣው ካንተ የምግባር ደረጃ ነው። ወላጆች ቁጣቸውን በልጆቻቸው ላይ የማፍሰስ መብት የላቸውም። ቁጣም በልጆች ላይ ማውረድና መጥፎ አመልን ማሣየት ለክርስቲያን ስህተት ነው። ለልጆችህም ቢሆን ሚዛናዊ መሆን አለብህ። ስትናገር "አይደለም" ከሆነ "አይደለም "አዎ "ከሆነ "አዎ" ይሁን። በዓለም ላይ የመጨረሻ ደካማ ሰው ደካሞችንና ትንሾችን የሚጨቁን ነው።

## 3. ለልጆችህ መስቀል አትሁን

ሁለት ልጃገረዶች በአንድ ትምህርት ቤት ይማሩ ነበር። አንደኛዋ አንድ ቀን ለትምህርት ቤት ጓደኛዋ እንዲህ አለቻት " አስፈላጊ ከሆነ አባቴ ለእኔ ሲል እንደሚሞት አውቃለሁ። " ይህች ልጃገረድ ስላባቷ የሰጠችውን አስተያየት በማየት ምን ዓይነት ክርስቲያን አባት እንደሆነ ማወቅ ይቻላል። ሌላኛዋም ልጃገረድ ከክርስቲያን ቤተሰብ የመጣች ነች የዚህች አባት ደግሞ በጣም ኃይለኛና ሁል ጊዜ በዚህች ልጅ ላይ የሚቆጣ ሐሣብ የለሽ ሰው ነው። አንድ ቀን ይህች ልጅ ትምህርት ቤት የክርስቲያን መልዕክት ሰማች። ከት/ቤት ከተመለሰች በኋላ አባቷ ምን እንደተማረች ጠየቃት። ስትመልስም "ዛሬ ጌታ አንተን ለእኔ መስቀል አድርጎ እንደሰጠኝ አውቂያለሁ" አለች። ታዲያ ይህ ለብዙ ሕፃናት ችግር አይደለምን? አባቶቻቸውን ወይም ሹናቶቻቸውን ጌታ መስቀል አድርጎ እንዲሰጣቸው የሚቆጥሩ ብዙ አይደሉምን? የእነዚህ ሁለት ልጃገረዶች አባቶች ሁለቱም ክርስቲያኖች ናቸው፣ ልዩነት ግን አላቸው። አንዱ እስከ ሞት የሚታመንበት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መስቀል ሆኖ ተገኘ። ታዲያ ክርስቲያን ለልጆቹ መስቀል መሆኑ አያሳዝንም!

ወላጆች ልጆቻቸውን ማዘዝ ሲፈልጉ ረጋ ማለት አለባቸው። በቅድሚያ በጌታ ፊት ጥሩ ወላጅ እንዲሆኑ ይጸልዩ። አንድ ሰው ጥሩ ወላጅ ካልሆነ እንዴት ጥሩ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር ለወላጆች ልጆችን ሰጥቷል እንጅ ወላጆች ለልጆች መስቀል እንዲሆኑ አልተሠጡም። ስለዚህ ወላጆች የልጆቻቸውን ነፃነት፣ ግላዊ ጉዳይና ነፍስ ማክበር አለባቸው።

### ልጆቻችሁን አታስቆጡ

ሐዋርያው ጳውሎስል ጆቻቸውን እንዳያስቆጡና እንዳያስመርሯቸው ወላጆችን ይመክራል።

## 1. ስልጣንህን በተወሠነ ደረጃ ብቻ ተጠቀም

ልጆችን ማስቆጣት ማለት ምን ማለት ነው ? ይህ ማለት ከመጠን በላይ ስልጣንን መጠቀም፣ እንዲሁም በኃይልና በጉልበት ወይም በገንዘብና በመሳሰሉት ልጆችን መጫን ማለት ነው ። እርግጥ ነው በማንኛውም መንገድ አንተ ከልጆችህ ትበረታለህ፥ ለማስፈራራትና በገንዘብ አቅምህ ልታሸንፋቸው ትችላለህ። እንዲህ በማለትም "የማትሰሙኝ ከሆነ ገንዘብ አልሠጣችሁም " ወይም " የማትሰሙኝ ከሆነ ምግብና ልብስ አልገዛላችሁም" በማለት ታስፈራራቸዋለህ። የምትረዳቸው አንተ እስከሆንክ ድረስ የገንዘብ ርዳታህን በማቆም ልትጨቁናቸው ትችላለህ። በቀላሉ በብርቱ ጉልበትህ ወይም ሊሸከሙት በማይችሉት ፈቃድህ ልታሸንፋቸው ትችላለህ። በዚህም ታስቆጣቸዋልህ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የምትጨቁናቸው ከሆነ ነፃነት የሚያዩበትን ቀን ይናፍቃሉ። ያቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉንም ማዕቀቦች ወርውረው በመጣል በማንኛውም ነገር ነፃነታቸውን ያውጃሉ። እንዲህ ከሆነ ደግሞ አደገኛ ነው።

አንድ አባቱ ቁማር የሚጫወት፣ ሲጋራ የሚያጤስና የሕዝብ ገንዘብ የሚዘርፍ ነገር ግን ሁል ጊዜ እሁድ ቤተክርስቲያን የሚሄድ አባት ያለው ሰው የመሰከረልኝን አስታውሳለሁ። ይህ አባት ልጆቹ ሁሉ ቤተክርስቲያን እንዲሄዱ፣ ባይሄዱ ግን ከባድ ቅጣት እንደሚደርስባቸው የሚያስገድድ ሰው ነው። ይህ ሰውም ስለ አባቱ ሲመሠክርልኝ በዚያ ወቅት ራሱን መርዳት ከሚችልበት ደረጃ ሲደርስ ቤተክርስቲያን ላለመሄድ ወስኖ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን ይህ ሰው ዳነ። የእግዚአብሔር ምህረት በዛለት እንጅ የክርስቶስ ተቃዋሚም ሆኖ በተነሣ ነበር። እንደዚህ አይነት ነገሮች በጣም ከባድ ናቸው። ራሱ የማይማርክና የማይሰብ ሰው ልጆቹን ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሄዱ ማስገደድ የለበትም። ይህ ልጆችን ያበሳጫቸዋል። ወላጆች ስልጣናቸውን ከመጠን በላይ ከተጠቀሙ ልጆችን ያበሳጫቸዋል። ወላጆች ስልጣናቸውን ከመጠን በላይ በመጠቀም ልጆች እንዲበሣጩ ማድረግ የለባቸውም።

አንድ ያልዳነ የማውቀው ሰው ነበር። ነገር ግን ልጆቹ መጽሐፍ ቅዱስ በቤታቸውና በትምህርት ቤት እንዲያነቡ ያስገድዳቸዋል። ትምህርት ቤታቸው የሚሽን ትምህርት ቤት ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያነቡ አያድርጉ ማለቴ አይደለም። ነገር ግን ወላጆች ራሳቸው በድርጊት ልጆቻቸውን መሳብ አለባቸው። የምታደርገው ሁሉ እነርሱን ለማስገደድ ከሆነ እንዴት አድርገህ የጌታን ውበት ታሳያቸዋለህ? የዚህ ልጅ እናት ሥጋዊ ክርስቲያን ነች። አስደንጋጭ ቁጣ ነበረባት። ነገር ግን ልጇን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያነብና ሚሽን ትምህርት ቤት እንዲከታተል ታስገድደዋለች። አንድ ቀንም ልጇ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ሙቼ እንደሚያቆም ጠየቃት። እርሷም

ስትመልስለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ ሊያቆም እንደሚችል መለሰችለት። እርሱም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ዲፕሎማ እንደተቀበለ ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂወችን ወደ ቆሻሻ ማቃጠያ ቦታ ወስዶ አቃጠላቸው።

ስለዚህ ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው። ፍቅርና ጨዋነትን ማሳየትን ተለማመዱ። በእነርሱ ፊት መልካም ምስክርነት ይኑራችሁ። ማራኪም ሁኑ፣ ስልጣናችሁን በገደብ ተጠቀሙ። ገደብ የለሽ ስልጣን አጠቃቀም ሊቋቋሙት ከማይችሉት ደረጃ ሊያደርሳቸው ይችላል።

## 2. ለልጆችህ አድናቆትህን ግለፅላቸው

ልጆች መልካም ሲሠሩ አግባብ ያለው አድናቆትን ልትቸሯቸው ይገባል። አንዳንድ ወላጆች የሚያውቁት መግረፍና መሣደብ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ልጆችን በቀላሉ ያስቆጣቸዋል። ጥሩ የመሆን ፍላጎት ያላቸውን ልጆች እንኳ ተስፋ ያስቆርጣቸዋል። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው " ያለው። ልጆች መልካም ሲሠሩ ሊበረታቱ ይገባል፣ እንዲሸለሙም፣ ስርዓት ይዘው እንዲያድጉም መደረግ ያስፈልጋቸዋል። አለበለዚያ ግን ልባቸው ይዝላል።

መሳደብ ብቻ የምታውቅ እናት ስላለቻት አንዲት ትንሽ ልጅ ታሪክ በአንድ ወቅት አንብቤአለው። ይህች ሕፃን ጥሩ ባህርይ ያላት ነች። እናትዋ ግን ለእርሷ ጥሩ እንዳልሆነች ታውቃለች። ሁል ጊዜም ይሰማታል። በተለይ አንድ ቀን የእናትዋን እርዳታ ለማግኘት ሞክራ ሳይሳካላት ቀርቷል። ምሽት ላይ እናትዋ የሌሊት ልብስ ሳታለብሳት ትታት ትሄዳለች። ተመልሳ እንድታለብሳ እናትዋን ጠራቻት። ነገር ግን እናትዋ ይህችን ልጅ ለምን እንደጠራቻት ስትጠይቃት በፍርሃት መልስ አልሠጠቻትም። ስለዚህ እናትዋ እንዴገና ትታት ሄደች። አሁንም እንደገና ጠራቻት። ከዚያም እናትዋ ለምን ጠራሽኝ በማለት በድጋሚ በቁጣ ጠየቀቻት። ሕፃንዋም "እናቴ የምታደርጊልኝ ነገር የለምን?" አለቻት። እናትዋም ምንም ነገር ሳትናገር ትታት ሄደች። ልጅቱም ለሁለት ሰዓት ያህል እንዳለቀሰች አንብቤያለሁ። እናትዋ ምንም የሚሠማት አልነበረችም። ከመደባደብና ከመሣደብ በስተቀር ሌላ ስለማታውቅ ምንም ስሜት አልነበራትም።

ከልጆች ይልቅ ለወላጆች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ምንባብ አለ። ይህም የሆነው ወላጆች ሲሳሳቱ ጌታ ብቻ ስለሚያስተምራቸው ነው። ነገር ግን ልጆች ሲያጠፉ መላው ዓለም ይፈርድባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ የሚነግረን ወላጆች ልጆቻቸውን ሊያስቆጡና ልባቸውን ሊያዝሉ የሚችሉት ርህራሄ ስለሚጎድላቸው ነው። የወላጅ ተግባር ከማንኛውም

ሌላ ተግባር የበለጠ ከባድ ነው። ብዙ ትኩረትን የሚጠይቅም ስለሆነ ልበ ደንዳና አትሁኑ።

## ትክክለኛውን ተናገር

የወላጆች ቃል ለልጆቻቸው ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው። ቃላቸውም እንደምሣሌነታቸው ጠቃሚ ነው።

### 1. ባዶ ተስፋ አትስጥ

ልታሟላ የማትችለውን ነገር ለልጆች አትናገር። ተግባራዊ የማይሆን ተስፋ አትስጥ። ተስፋውን ተግባራዊ የማድረግ አቅም ከሌለህ ፈፅሞ ተስፋ አትስጥ። ልጆቻችሁ አንድ ነገር እንድትገዙላቸው ከጠየቁአችሁ ቃል ከመግባታችሁ በፊት በጥንቃቄ አስቡበት። የምትናገሩት ማንኛውም ቃል ተግባራዊ መሆን አለበት። ይህንም እውነተኛነት እንደትንሽ ነገር አትዩት። ልጆቻችሁ ቃላችሁን የሚጠራጠሩ አይሁኑ። ቃላችሁ የሚታመን መሆኑን ማመን አለባቸው ። ልጆች የወላጆቻቸው ቃል እምነት የሚጣልበት አለመሆኑን ከደረሱበት ትልቅ ሰው ሲሆኑ ለማንኛውም ነገር ግዴለሽ ይሆናሉ። ማንኛውንም ነገር ሳያስቡ ይናገራሉ። ወላጆች ቃላቸው ተግባራዊ ካልሆነ ለምን ተግባራዊ እንዳላደረጉ በውሸትና በማታለል ለማምለጥ መሞከር የለባቸውም። ተግባራዊ የማይሆን ነገርንም መናገር አልነበረባቸውም። ብዙ ወላጆች ደግነትን በቃላቸው ያበዛሉ። ልጆቻቸው ለጠየቁአቸው ማናቸውም ነገር ለመፈፀም ቃል ይገባሉ። ተግባራዊ የሚያርጉት ግን ጥቂቱን ብቻ ነው። እንደዚህ ዓይነቱ ባዶ ቃል ልጆቹን ተስፋ ያስቆርጣል። ልታደርገው ለምትችለው ነገር " እሺ " ልታደርገው ለማትችለው ነገር ደግሞ " አይሆንም" ፣ እንዲሁም እርግጠኛ ላልሆንከበት ነገር " ምን አልባት "በማለት ተናገር። ቃሎችህም ትክክለኛ ይሁኑ።

### 2. ትዕዛዝህን ለማስፈፀም ትጋ

ልጆችህ አንድ ነገር እንዲያደርጉ በምትጠይቅበት ጊዜ የጠየቅሃቸው ነገር ተግባራዊ መሆኑን አረጋግጥ። አለበለዚያ ግን ምንም አትናገር። አንዴ ትዕዛዝ ከሰጠሃቸው ያን ትዛዝ አትርሳ ወይንም ለሚቀጥለው ጊዜ ለማስተላለፍ አትደራደር። ትዕዛዝም ይሁን የተስፋ ቃሎች የተቀደሱ መሆናቸውን ለልጆችህ አሳያቸው። ለምሣሌ ልጆችህ ሁል ጊዜ ጠዋት መኝታ ቤታቸውን እንዲያፀዱ ከነገርካቸው የአንተ ትጋት መሆን ያለበት ይህ መፈፀሙን መቆጣጠር ነው። ዛሬ ሳያደርጉት ቀርተው ብታገኝ በሚቀጥለው ጠዋት የግድ እንዲፈፅሙ እዘዛቸው።

በዚህ ዓመት ካላደረጉት በሚቀጥለው ዓመት እንዲያደርጉት አሁንም መጠየቅ አለባቸው። አባት ዝም ብሎ ሳያስብ እንደማይናገርና የሚናገረውም ነገር መፈፀም ያለበት መሆኑን ልጆችህ እንዲያምኑበት አድርግ። ቃሎችህን እንደማትሽቃቅጥ እንዲያውቁ አድርግ። አለበለዚያ ግን የምትናገረው ነገር ዋጋ ያጣል። ስለዚህ የምትናገረው ነገር ሁሉ መፈፀም ስለ አለበት ለማስፈፀም ግፊት አድርግ።

## 3. ትክክል ያልሆነ ነገርህን አርም

አጋነህ ተናግረህ ከሆነ በልጆችህ ፊት ይህን ለማረም አጋጣሚውን ፈልግ። ቃሎች ትክክል መሆን ያስፈልጋቸዋል፥ምን አልባት ሁለት ላሞችን ሦስት ወይም አምስት ወፎችን ስምንት ብለህ አጋነህ ተናግረህ ይሆናል። እነዚህን ቁጥሮች በልጆችህ ፊት ማስተካከልን ተለማመድ። የቃልን ቅድስና አሳያቸው። በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ያለ ማንኛውም ነገር ጥሩ የክርስቲያን ፀባይን መፍጠር አለበት። ስለዚህ የቃልን ቅድስና ማረጋገጥ ይኖርብሃል። ይህንን ቅድስና ልጆችህ እንዲረዱት ልትመራቸው ያስፈልግሃል። ትክክል ያልሆነ ነገር ተናግረህ ከሆነ መጥፎና አደገኛ መሆኑን ተናዘዝ፣ በቤትህ ውስጥ መልካም ምሳሌነትን አስቀምጥ። በዚህም ልጆችህ የቃሉን ቅድስና ያውቃሉ።

ስለ ትክክለኛ ቃሎች ችግር የሚመጣው የጌታ ተግሳፅ ሲጎድል ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው መስጠት ያለባቸው የጌታን ተግሳፅ ብቻ ሳይሆን እንደዚያ አይነቱን ሕግ የሚያዝዘውን ትምህርት ጭምር ነው። ቃሎች እንዴት ቅዱስ እንደሆኑ ልጆቻችሁን ማሳየት አለባችሁ። ቃል ኪዳን መጠበቅ፣ትዕዛዝም ተግባራዊ መሆን አለበት። ቃሎችም ትክክል መሆን አለባቸው። በዚህ መልክ ቢያድጉ ልጆቻችሁ መንፈሣዊ ትምህርቶችን ለመቀበል አይከብዳቸውም።

## በጌታ ምክርና ተግሣፅ ልጆችህን አሳድግ

የጌታ ተግሳፅ ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት አንድ ሰው እንዴት መመላለስ እንዳለበት የሚገልፅ ትዕዛዝ ነው። ልጆችን ስታዝ ወይም መመሪያ ስትሠጥ እንደ ዓለማዊ ሳይሆን እንደ ክርስቲያን ይሁን። በመልካም የክርስቲያን ወግ መሠረት መመሪያ ልትሠጣቸውና ልታስተምራቸው ይገባሃል።

## 1. የልጆችህን ምኞት አስተካክል

በልጆች ላይ ያለ ታላቅ ችግር ምኞት ነው። እያንዳንዱ ልጅ የራሱ ምኞት አለው። ብዙ ልጆች ስማቸውን ሲፅፉ እንዲህ ብለው ያስቀምጣሉ

"የወደፊቱ ፕሬዚዳንት፣ የወደፊቷ ንግስት ወ.ዘ.ተ." እንግዲህ አንተ በዓለማዊ ምኞት የተሞላህ ከሆነ ልጆችህ የሚያስቡት ፕሬዚዳንት፣ ሚሊየነር ... ወዘተ ለመሆን ነው። አንተ የምትኖርበት አለም ያ የልጆችህ ምኞት ይሆናል። በዚህ ምክንያት ወላጆች የልጆቻቸውን ምኞት ማስተካከልና መቅረጽ አለባቸው። ስለዚህ አንተ ራስህ ዓለምን ሳይሆን ጌታን የምትወድ መሆን አለብህ። በትንሿ ልባቸውም ቢሆን ለጌታ መሰቃየት እና ሰማዕት መሆን መልካምና የከበረ ነገር እንደሆነ ሊረዱ ይችላሉ። ስለዚህ አንተ ራስህ ምሣሌ መሆን ያስፈልግሃል። የአንተ ምኞት ምን እንደሆነና ምን ዓይነት ክርስቲያንም ለመሆን እንደምትፈልግ ንግራቸው። በዚህ አይነት መንገድ ወደ መልካሙና ወደ ከበረው አቅጣጫ ምኞታቸውን ማስተካከል ትችላለህ።

## 2. የልጆችን ትዕቢት አታበረታታ

ልጆች ከውጫዊ ምኞት በተጨማሪ የውስጥ ትዕቢት ችግር አለባቸው። በጉብዝናቸው፣ በችሎታቸው ወይም በአንደበተ ርዕቱነታቸው በትዕቢት ሊወጠሩ ይችላሉ። ልጆች ብዙ ጊዜ የሚፎክሩትና ራሣቸውን በጣም ልዩ እንዲሆኑ አድርገው የሚያስቡበት ብዙ ነገር ማግኘት ይችላሉ። ስለዚህ ወላጆች ልጆቻቸው በትዕቢት እንዳያድጉ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። እንዲሁም ልጆቻቸውን ማፈን የለባቸውም። ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ምንም የሌላቸውን ነገር በመካብ ስህተት የሆነ መንገድ ያስተምሩአቸዋል። ሰዎች ልጆቻችሁን ቢያመሰግኑአቸው እንኳ እናንተም መልሳችሁ እነርሱን የሚመስሉ ሌሎች ብዙ ልጆች እንዳሉ ንገሯቸው እንጂ ትዕቢታቸውን አታበረታቱ። ይልቁንስ በጌታ ምክርና ተግሣፅ መሠረት ምሩአቸው። የራሳቸውን ክብር እንዲጥሉም አታድርጉ። ትዕቢትም አትፍቀዱላቸው። ክብራቸውን አትጣሉባቸው። ስለራሳቸው ያላቸውን የተጋነነውን ግምት የት ጋ እንደሆን አሳዩአቸው። ብዙ ጊዜ ወጣቶች በማህበረሰብ ውስጥ ገብተው መልካም ነገር ማድረግ ከመጀመራቸው በፊት በማሕበረሰቡ ወፍጮ ገብተው ለመስተካከል ከአሥር እስከ ሃያ ዓመት ይፈጅባቸዋል። ይህ ደግሞ ውድ የሆነውን ጊዜ ማባከን ነው። የዚህ ምክንያቱ በቤት ውስጥ በጣም ስለሚተብቱና ከመጠን በላይ ስለሚገንኑ አንድን ስራ በጥሩ ሁኔታ ለመሥራት ራሳቸውን ትሁት አድርገው ማቅረብ ስለማይችሉ ነው።

## 3. ልጆች ሽንፈትን እንዲቀበሉና ትህትናን እንዲለማመዱ አስተምሯቸው

ክርስቲያን ቢሸነፍ እንኳ ያሸነፋቸውን ሰዎች እንዴት ማድነቅ እንዳለበት መማር ያስፈልገዋል። በድል ጊዜ ራስን መግዛት ቀላል ነው፣ በሽንፈት ጊዜ ግን ከባድ ነው። በድል ጊዜ ብዙ ሰዎች ትሁት ናቸው። በሽንፈት ጊዜ ግን ስለ ሌሎች ሰዎች በትሕትና የሚናገሩ በጣም ጥቂት

ናቸው:: ክርስቲያን በተረታ ጊዜ ትሁት መሆንና ሽንፈትን በመልካም ፈቃድ መቀበል መቻል አለበት:: ልጆች ማሸነፍ ደስ ይላቸዋል ፣ ይፈልጋሉም:: እንደዚህ ዓይነት ምኞት መልካም ነው:: በተለይ ለስፖርትና ለጥናት ይረዳቸዋል :: ልጆችህ ትሁት እንዲሆኑ አስተምራቸው፣ አበረታታቸው:: ነገር ግን ከእነርሱም የተሻሉ ሌሎች ብዙ ተማሪዎችም እንዳሉ ንገሩፋቸው:: ሽንፈትን እንዴት በመልካም መንፈስ እንደሚቀበሉ አስተምራቸው:: ይህ ለልጆች አስቸጋሪ ነገር ነው:: ለምሣሌ ሁለት ልጆች ኳስ ቢጫወቱ አሸናፊው በኩራት ሲወጣጠር ተሸናፊው ደግሞ ዳኛው ጥሩ እንዳልሆነ ወይም የፀሀዩ ጨረር ለዓይኑ እንዳስቸገረው ያማርራል:: በአጠቃላይ ለሽንፈቱ ምክንያት ይደረድራል:: ስለዚህ ልጅህ ትሁት እንዲሆንና ቀና አመለካከት እንዲኖረው አበረታታ:: የልጆችን ፀባይ ለማዳበር አስልጥናቸው:: እንዴት እንደሚያሸንፉ መማር አለባቸው:: በሽንፈታቸው ጊዜ ደግሞ ሌሎችን እንዴት ማስቀደም እንዳለባቸው መለማመድ አለባቸው:: በጊታ ስርዓትና ትዕዛዝም እናሣድጋቸው::

ብዙ ጊዜ ልጆች ሚዛን የጎደለው ነገር ሊናገሩ ይችላሉ:: በፈተና ላይ ጥሩ የሰራን ተማሪ አስተማሪው እንዳገዘው፣ የእነርሱ ውድቀት ደግሞ አስተማሪው ስለሚጠላቸው እንደሆነ ሊናገሩ ይችላሉ:: እዚህ ላይ ግን አንተ የምታየው ትህትና የሚጎድላቸው መሆኑን ነው:: ስለዚህ ክርስቲያን ሽንፈትን መቀበል ጥሩ ምግባር እንደሆነ መረዳት ይገባዋል:: ሌሎች ሰዎች ሲገስፁን ሽንፈታችንን በግልፅ መቀበል ያስፈልገናል :: ሽንፈትን እንዲህ በማለት መቀበል እንችላለን "ሌሎች ድልን ያገኙት ከእኛ የበለጠና የተሻለ ትጋትና ብልሃት ያላቸው ሆነው ስለ ተገኙ መሆኑን መናገር አስፈላጊ ነው:: ድል ሲያገኙ በትዕቢት መወጣጠር የክርስቲያን ባሕርይ አይደለም:: ሽንፈትን በጥሩ መንፈስ መቀበል የክርስቲያን ጥሩ ምግባር ነው:: በቤተሰብ ውስጥ ልጆች ከእነርሱ የተሻሉትን እንዲቀበሉ ወይም እንዲረዱ ሊማሩ ይገባቸዋል:: ይህም ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ራሳቸውን በደንብ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል:: ክርስቲያን ከእርሱ የተሻሉትን ሰዎች ማድነቅና እርሱ ራሱ ምን እንደሆነ ማወቅ ይገባዋል:: በዚህ ዓይነት መንገድ የተቀረፁ ልጆች ለመንፈሣዊ ነገር የበለጠ ክፍት ናቸው ::

## 4. ልጆች እንዴት መምረጥ እንዳለባቸው አስተምር

ልጆች ገና ሕፃን ሳሉ ጀምሮ ምርጫ ማድረግ እንዲለማመዱ ምቹ ሁኔታዎች ሊፈጠሩላቸው ይገባል:: ራሳቸውን ችለው ከወላጆች እስኪለዩ ድረስ ማንኛውንም ነገር ሁል ጊዜ አትወስኑላቸው:: ድንገት ወደ ዓለም ሲገቡ ይቸገራሉና:: እንደዚያ ካደረግህ ለራሳቸው እንዴት እንደሚመርጡ አያውቁም:: ስለዚህ ልጆችህን ስታሳድግ ለመምረጥ ስፊ አጋጣሚወች አመቻችላቸው:: ምን እንደሚወዱና ምን እንደሚጠሉ

እንዲገልፁ አድርጓቸው:: የወደዱት ነገርም ትክክል ወይም ትክክል እንዳልሆነ አሳዩአቸው:: በትክክል እንዲመርጡም እርዱአቸው:: አንዳንድ ልጆች ባለ አንድ ቀለም ልብስ መልበስ ይወዳሉ:: ሌሎች ደግሞ ሌላ ይመርጣሉ:: ስለዚህ ልጆቻችሁ መምረጥ እንዲችሉ የተቻላችሁን አጋጣሚ ሁሉ አመቻቹላቸው:: ስለ ምርጫቸውም አስተምሩአቸው::

## 5. ልጆች ለነገሮች እንዴት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው አስተምር

ልጆቻችሁ ለነገሮች እንዴት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ማስተማር አለባችሁ:: ልጆች የራሳቸውን ጫማ፣ ካልሲ፣ መኝታ ቤት ወ.ዘ.ተ. እንዲያስተዳድሩ እድሉን ስጡአቸው:: ትንሽ መመሪያ ስጡአቸውና ራሳቸው እንዲሠሩ አድርጉ:: ስለዚህ ገና በልጅነታቸው ለነገሮች እንዴት እንደሚጠነቀቁ ይማራሉ:: ብዙ ልጆች ገና ከልጅነታቸው የራሳቸውን ኑሮ እንዲጀምሩ ሁኔታዎች አይፈጠሩላቸውም:: ምክንያቱም ወላጆቻቸው ጭፍን በሆነ ሁኔታ ስለሚወዱአቸው ልጆቹ ለእንዲህ ዓይነቱ ኃላፊነት ዕድል አይሰጣቸውም:: ነገር ግን ክርስቲያኖች ልጆቻቸው የራሳቸውን ጉዳይ ራሣቸው እንዲያስተዳድሩ መርዳት ይኖርባቸዋል:: የእግዚአብሔር ፀጋ ለቤተክርስቲያን በዝቶ ሰዎች ወደ ለቤተክርስቲያን ቢጨምሩ ግማሾቹ ከቤተክርስቲያን ወላጆች የመጡ እንደሆኑና ግማሾችም ከዓለም የዳኑ እንደሚሆኑ እምናለሁ:: ነገር ግን በየጊዜው የሚጨመረው ሰው ከክርስቲያን ወላጆች ካልሆነና ከዓለም ብቻ የሚመጡ ከሆነ ቤተክርስቲያን ጠንካራ ልትሆን አትችልም:: በነጳውሎስ ዘመን ቤተክርስቲያን ስትጀመር የነበሩት አባላት በቀጥታ ከዓለም የመጡ ብቻ ነበሩ:: ነገር ግን ቀጣዩ ትውልድ ብዙ ጊዜ ከክርስቲያን ቤተሰብም ይመጣ ነበር:: ለዚህም ማስረጃ ጢሞቲዎስን መጥቀስ ይቻላል:: ሰዎች ሁል ጊዜ ለቤተክርስቲያን በቀጥታ ከአለም ይመጣሉ ብለን መጠበቅ የለብንም:: ከክርስቲያን ቤተሰብም እንዲመጡ ተስፋ ማድረግ አለብን:: እርግጥ ነው ወንጌል ሰዎችን ከዓለም ያድናል፥ከዚህ በተጨማሪ እንደ ጢሞቲዎስ ያሉት ሰዎችም በጌታ ምክርና ተግሣፅ ተኮትኩተው ከአያቱ ብሎም ከእናቱ ከአውንቄ መጥተዋል:: ይህ ነው ቤተክርስቲያንን የሚያበለፅጋት:: ስለዚህ ልጆችህ ለራሳቸው በቤተሰብ ስብሰባ ጊዜ ለነገሮች እንዴት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ይማሩ:: ወንዶችና ሴቶች ልጆች መማር ያስፈልጋቸዋል:: ይህም ጥሩ ባሎችና ጥሩ ሚስቶች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል::

የዛሬው ዘመን ሁኔታ እንዴት ነው? ብዙ ወላጆች ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን በጌታ ስርዓትና ትእዛዝ ሊያሣድጉአቸው ሲገባ ቤተክርስቲያን እንድትጠነቀቅላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ያመጣሉ:: ምክንያቱም ወላጆቻቸው ጥሩ ክርስቲያን ሆነው ስለማይኖሩ ነው::

ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ልጆች ከዓለም ለማዳን ወንጌልን ልትሰብክላቸው ትገደዳለች። ነገር ግን ክርስቲያን ወላጆች ኃላፊነታቸውን ተወጥተው ቢሆን ኖሮ እነዚህ ልጆች ለቤተክርስቲያን ምንም ችግር ሣይፈጥሩ በመጡ ነበር፣ ቤተክርስቲያንም ግማሽ ችግሯና ሸክሟ በተቃለለ ነበር።

## ልጆችህን ወደ ጌታ ምራቸው

ልጆችን ወደ ጌታ የምትመራበት አንዱ መንገድ ውጤታማ የቤተሰብ መስዋዕት ነው። በብሉይ ኪዳን ድንኳኑና መስዋዕቱ በአንድ ላይ የተጣመሩ ነበሩ። በሌላ አባባል ቤተሰብና ቅድስና የተያያዙ ናቸው። የቤተሰብ የአንድነት ፀሎትና በአንድነት መጽሀፍ ቅዱስን ማንበብ የማይለያዩ ናቸው።

### 1. በልጆች ደረጃ የቤተሰብ አምልኮ ይኑርህ

የብዙዎች የቤተሰብ አምልኮ የሚዳከመው ፕሮግራሙ በመርዘሙ አለበለዚያም መልዕክቱ ጥልቅ በመሆኑ ምክንያት ነው። ልጆች ምን እንደሆነ ሳያውቁ አብረው ይቀመጣሉ። አብረው ለተቀመጡት ልጆች ጥልቅ ስብከትን የሚጋብዝ ቤተሰብን አልደገፍም። የአንዳንድ ቤተሰብ ስብሰባ ደግሞ ለአንድና ለሁለት ሰዓት ይራዘማል። ከዚህ በተጨማሪ የሚያተኩረው ጥልቅ በሆኑ እውነቶች ላይ ነው። ይህ ደግሞ ለልጆች ከባድ ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወላጆች ይህ ላይሰማቸውና ላያስቡበት ይችላሉ። በቤተሰብ ስብሰባ በመጀመሪያ ሊታዩ የሚገባቸው ልጆች ናቸው። ስብሰባው ለእናንተ አይደለም። እናንተ ቤተክርስቲያንም ማምለክ ትችላላችሁ። ስብሰባው በእናንተ ደረጃ እንዲሆን አታድርጉ። በቤተሰብ የምታደርጉት ሁሉ በልጆች ደረጃና እነርሱን የሚመጥን ይሁን፤

### 2. ልጆችን በፍቅር ማርካቸው

ሌላው የቤተሰብ ስብሰባ ችግር ፍቅር ማጣት ነው። ልጆች ወደ ቤተሰብ ስብሰባ እንዲቀላቀሉ የሚደረጉት በፍቅር ሳይሆን በአለንጋ ነው። ከዚህ የተነሳ ብዙዎች መካፈል አይፈልጉም። የሚመጡትም ዱላውን ስለሚፈሩ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ አይሠራም። በመልካም ሕይወትህ ሳባቸውና ማርካቸው እንጂ አትግረፋቸው። ለአንድ ጊዜ ልትገርፋቸው ትችል ይሆናል፣ የሚያመጣው ችግር ግን የዕድሜ ልክ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በቤተሰብ ስብሰባ እናንተ ወላጆች ልጆቻችሁን ለመሣብ መሞከር አለባችሁ እንጂ በግድና በኃይል እንዲገኙ አታስገድአቸው።

## 3. በቀን ሁለት ጊዜ የቤተሰብ ስብሰባ አድርጉ

በቀን ሁለት ጊዜ የቤተሰብ ስብሰባ እንዲኖር እንመክራለን። ይህም አንዱ ጠዋት ሌላኛው ደግሞ ማታ ነው። በዚህም ጠዋት አባትየው እንዲመራ፣ ማታ ደግሞ እናትየዋ እንድትመራ ነው። ወላጆች በጠዋት እንዲነሱ ያስፈልጋቸዋል። ምክንያቱም ልጆች ቁርስ ከበሉ በኋላ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት የአምልኮና የፀሎት ጊዜ እንዲኖራቸው ነው። ሰዓቱ መርዘም የለበትም። ከአሥራ አምስት ደቂቃ መብለጥ የለበትም። እያንዳንዳቸው ጥቅስ እንዲያነቡ ጠይቁአቸው። አባትም ጥቂት ቃሎችን ወስዶ ያብራራላቸው። ከተቻለ ልጆች የጥቅሱን ክፍል እንዲያስታውሱት ይደረግ። ፕሮግራሙ በእናት ወይም በአባት ፀሎት ይዘጋ። እግዚአብሔር እንዲባርካቸው ፀልዩላቸው። ፀሎቱም ሊረዱት ከሚችሉት በላይ ጥልቅ አይሁን። ፀሎቱ አይርዘም። ልጆች በሚረዱት መልክ ቀላል ይሁን።

የማታው ጊዜ ጥቂተ ረዘም ሊል ይችላል። ይህንንም እናት ትምራ። መጽሐፍ ቅዱስ ላያስፈልግ ይችላል። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ፀሎት በጣም አስፈላጊ ነው። በተለይም እናት ልጆቿን በዙሪያዋ ሰብስባ የምታካፍላቸውን ሀሳብ ትንገራቸው። አባትም ከጎኗ ሊቀመጥ ይችላል። እናት የልጆቿን ትኩረት በመሣብ ታነጋግራቸው። በቀን የገጠማቸው ችግር ካለም እንዲናገሩ ታድርግ። ተጣልተውም ከሆነ ወይንም ሌላ ልባቸውን ያከበደባቸው ነገር ካለ እንዲናገሩ ማድረግ ካልቻለች አንድ ችግር አለ ማለት ነው። በእናትና በልጅ መካከል መራራቅ ካለ በእናት በኩል የመጣ ድክመት ነው። እናት የልጆቿ እምነት መጣያ መሆን አለባት። ጥቂት እንዲፀልዩ ይሁን። ጥቂት ቃሎች አስተምሯቸው። እንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ ሕያው ጊዜ መሆን አለበት። እንዲናዘዙ አደፋፍሩአቸው። ነገር ግን አታስገድዷቸው። የሆንከውን ሁን፣ ነገር ግን አታስመስል። ልጆች ድንገታዊ እንዲሆኑ አድርግ። የሚናዘዙት ነገር ካለ ይናዘዙ ከሌለ ግን ተዋቸው። የልጆች ግብዝነት የሚመጣው ከባድ ወላጆች ካሉአቸው ነው። ልጆች መዋሸት አይፈልጉም ፣ ነገር ግን በወላጆቻቸው ይገደዳሉ። የማታውን ጊዜ በአጭር ፀሎት ደምድም ልጆች እንዳይደክሙ አድርግ።

ወላጆች ልጆቻቸውን ቀለል ባለ ሁኔታ ይምሩአቸው። ልጆች እንዴት መፀለይ እስከሚያውቁ ድረስ ሁል ጊዜ ይፀልዩላቸው።

## 4. ልጆችን ንስሃ እንዲገቡ እርዷቸው

ልጆቻችሁን ኃጢአት ምን እንደሆነ ልታሳዩአቸው ይገባል። ንስሃ የሚገቡ ከሆነ ተከታተሉአቸው። ወደጌታም አምጡአቸው። .ጊዜው

ሲደርስ በግልፅ መንገድ ጌታን እንዲቀበሉ እርዷቸው። በቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው ወደ ቤተክርስቲያን ውሰዷቸው። በዚህ ዓይነት መንገድ ወደ ትክክለኛ የእግዚአብሔር እውቀት ልጆቻችሁን ልትመሯቸው ይገባል።

## የቤተሰብ ፍቅርን አበረታቱ

የቤተሰብ ግንኙነት የፍቅር ግንኙነት ነው። የቤተሰብ ግንኙነት የሚሻከረው በፍቅር እጦት ምክንያት ነው።

የልጆች የወደፊት ሁኔታ በአብዛኛው የሚመሠረተው በቤተሰብ ግንኙነት ነው። ልጆች ገና ሕፃን ሳሉ ፍቅርን ካልተመገቡ ወዲያው እስቸጋሪ፣ ብቸኛና አመፀኛ እስተሣሠብን ያዳብራሉ፣ ብዙ ሰዎች ከሌሎች ጋር መቀራረብ የማይችሉበት ምክንያት ልጅ ሳሉ ከቤተሠባቸው ፍቅር ስላላገኙ ነው። በቤተሰብ ውስጥ በተደጋጋሚ ሁከትና ፀብ ካለ ልጆች በጥሩና በትክክለኛው ሁኔታ አያድጉም። ወደ ኋላ ይጎተታሉ። የዝቅተኛነት ስሜት ስለሚኖራቸው ሰውን ይንቃሉ። የዝቅተኛነት ስሜት ያለባቸው ሰዎች ከሌሎች ጋር እኩል ለመሆን ሲሉ ራሳቸውን ከፍ ለማድረግ ይጥራሉ።

በህብረተሰቡ ውስጥ ሽፍታና ወንበዴ የሚበዛበት ምክንያት ግለሰቦቹ የቤተሰብ ፍቅርን ስላልተለማመዱ ነው። በዚህ ምክንያት የሰው ባህርያቸው ተለውጦ የአውሬነት ባህርይ ይወርሳቸዋል። ከዚህ የተነሣ ከሰው የተለዩ ይሆናሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ ብዙ ማስተካከያወች ያስፈልጋቸዋል። ከግማሽ በላይ የሚሆነው የቤተክርስቲያን ስራ የሚከናወነው በጥሩ ወላጆች ነው። በወላጆች ድክመት ምክንያት ከባድ ችግሮች በቤተክርስቲያን ላይ ይወድቃሉ። እንዲህ ዓይነቱን ችግር ለማስወገድ አማኞች ልጆቻቸውን በጥሩ ሁኔታ እንዲንከባከቡና እንዲያሳድጉ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። በቤተሰብ ውስጥ ደስታ፣ ጨዋነትና ፍቅር ሊኖር ይገባል። እንደዚህ ዓይነቱ ቤተሰብ ጥሩ ልጆችን ያፈራል። ወላጆች ለልጆቻቸው ወዳጆች መሆን አለባቸው። ልጆቻችሁ ለእናንተ እንግዶች እንዲሆኑ አትፍቀዱላቸው። እስተውሉ ወዳጅነት ይበቅላል እንጅ አይወረስም። ለልጆቻችሁ ቅርብ መሆንን ተማሩ። ለመርዳት ሁል ጊዜ ደስተኛ ሁኑ። እንደዚያ ብታደርጉ ችግር ሲገጥማቸው ይነግሩአችኋል። ሲደክሙ ርዳታችሁን ይፈልጋሉ። ርዳታ ሲያስፈልጋቸው ከውጭ ወዳሉ ወደ ሌሎች ሰዎች እንዲሄዱ አታድርጉ። በስኬታማነታቸውም ሆኑ በውድቀታቸው ወደ እናንተ በተቻለ መጠን እንዲመጡ አድርጉ። ወዳጅ ማለት በቀላሉ ቀርቦ የሚያነጋግር ሰው ነው። ለልጆቻችሁ እንደ ጓደኛ ሁኑ። ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ አትፍረዱ። ነገር ግን በድክመታቸው ልትረዱአቸው ሞክሩ። ከእነርሱ ጋር ተቀምጣችሁ በአንድ ላይ ችግራቸውን ተነጋገሩ፣

ልክ ወዳጆቻቸውን እንደሚፈልጉ እናንተን እንዲፈልጓችሁ አድርጉ። ለልጆቻቸው ጓደኛ መሆን የቻሉ ወላጆች እነርሱ ጥሩ ወላጆች ናቸው።

ይህ ዓይነቱን ጓደኝነት ልጆች ገና ሕፃን ሳሉ አዳብሩት። ከልጆቻችሁ ጋር የሚኖራችሁ ቅርበትና ወዳጅነት የሚመሠረተው በመጀሪያዎቹ ሃያ ዓመታት ውስጥ ለእነርሱ ባደረጋችሁት የእንክብካቤ መንገድ ነው። በመጀመሪያዎቹ ሃያ ዓመታት ከእናንተ የራቁትን ልጆች ከዚያ በኋላ እንዲቀርቡአችሁ ማድረግ አይቻልም። በእናንተና በልጆቻችሁ መካከል እርቀት ካለ ዓመታት ባለፉ ቁጥር ርቀቱ እየሰፋ ይሄዳል። ብዙ ልጆች ወላጆቻቸውን የማያደንቁት በሁለቱ መካከል ወዳጅነት ስለሌለ ነው። በችግር ውስጥ ሆነው እንኳ ወደ ወላጆቻቸው ሲሄዱ ፍርድ ቤት የመሄድ ያህል የቆጥሩታል። ይህ የአንተ ጉዳይ መሆን የለበትም። ልጆችህ ችግር ሲገጥማቸው ሸክማቸውን ለማውረድ ከሚፈልጉት ሰው የመጀመሪያው መሆን አለብህ። እንዲህ ዓይነት ቤተሰብ ሊኖረው የሚችል ሰው የሚገጥመው ችግር በጣም ጥቂት ነው። አብዛኛው መፍትሄ ያገኛል።

## ልጆችህን በጥበብ ቅጣ

ልጆች ሲያጠፉ መቀጣት አለባቸው። ልጅን አለመምከርና አለመቅጣት ትክክል አይደለም።

### 1. ያለ ጥበብ መቅጣትን ፍራ

መምከር ወይም መቅጣት በጣም ከባድና አስቸጋሪ ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን ከመግረፍ መቆጠብና መፍራት አለባቸው። ልክ የራሳቸውን ወላጆች ለመግረፍ እንደሚፈሩ ሁሉ ማለት ነው። ወላጆቹን የሚማታ ልጅ እንደሌለ ሁሉ ወላጅም እንደዚህ ዓይነቱን ቅጣት በልጆቹ ላይ ማድረግ የለበትም ። ወላጅ አጥፍቶ ልጆቹ ይቅር ከሚሉት ይልቅ ራሱ አስቀድሞ ይቅርታ ቢጠይቅ ይሻላል። ስለዚህ ልጆችን መግረፍን ፍራ። ይህንንም ተለማመድ።

### 2. አስፈላጊ ሲሆን ዱላን ተጠቀም

ነገር ግን ልጆች መገረፍ አለባቸው "በበትር ከመምታት የሚራራው ሰው ልጁን ይጠላል። ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥፀዋል " /ምሣ 13፥24/

ይህ የሰሎሞን ጥበብ ነው። አስፈላጊ ሲሆን ወላጆች በትር መጠቀምን መልመድ አለባቸው።

### 3. በልክ ቅጣ

ነገር ግን ቅጣት በልክ መሆን አለበት። ስትናደድ ወይም ከቁጥጥር ውጭ ስትሆን ልጅህን አትማታ። በተናደድክ ጊዜ ከተማታህ አንተ ራስህ ተሳስተሃል። ልጅህን ለመቅጣት ብቁ አይደለህም። በመጀመሪያ ቁጣህን በእግዚአብሔር ፊት ማስወገድ ያስፈልግሃል።

### 4. ጥፋታቸውን አሳያቸው

በአንዳንድ ጉዳዮች መግረፍ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ልጅህ ይህ ቅጣት ለምን እንደተገባው ማሳየት አለብህ። መቀጣት እንደሚያስፈልገው ሁሉ ጥፋቱንም ማወቅ ያስፈልገዋል። ሁል ጊዜ ልጅህን ስትቀጣ ጥፋቱ የት ላይ እንደሆነ ንገረው።

### 5. መግረፍ ከባድ ነገር እንደሆነ ተገንዘብ

መግረፍን የተለመደ ነገር አታድርገው። ለትልቅ ጉዳይ ተጠቀምበት። ሁሉንም ቤተሰብ በአንድነት ጥራና ስለዚሁ ጉዳይ ሁሉም እንዲያውቁት አድርግ። የሚጋረፈው ወላጅ አንድን በሽተኛ ቀዶ ጥገና እንደሚያደርግ ሀኪም መሆን አለበት። ይህ ርምጃ የሚወሰደው ለማስቀጣትና ለማበሣጨት እንዳልሆነና ነገር ግን ችግሩን ለማስወገድ አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ መታወቅ አለበት። እንደዚሁ ሁሉ በቅጣት ጊዜ ወላጆች ፍፁም ያልተናደዱ መሆን ይገባቸዋል። ራሱ የተናደደ ወላጅ ልጁን መምታት የለበትም።

ቅጣቱ እንዴት ነው የሚከናወነው? የራሴን ምክር ልስጥ። ልጁ ዱላን የሚጠይቅ ከባድ ጥፋት ከፈፀመ ወንድምየው ቀዝቃዛ ውሃ እንዲያዘጋጅና እህቱ ደግሞ ፎጣ እንድታቀርብ ማድረግ ትችላለህ ከዚያም የልጁ ጥፋት የት ላይ እንደሆነ አሳየው። ይህም ጥፋት ቅጣት እንደሚያስፈልገው ንገረው። በጥፋትህ ምክንያት ከጥፋት መሸሽም ትክክል እንዳልሆነ ንገረው። ኃጢአትም ለማድረግ የተደፋፈሩ ሰዎች ቅጣትንም ለመቀበል ጉብዝና ሊኖራቸው እንደሚገባ ንገረው። ይህን ከገለፅክለት በኋላ እጁን ይዘህ ሁለት ሦስት ጊዜ ልትመታው ትችላለህ ይህም ምን አልባት የተመታው ምልክት እንዲኖረው ወይም እንዲያብጥ ሊያደርገው ይችል ይሆናል። እንዲህ ከሆነ ወንድሙን ጥራና ያበጠውን ቦታ በቀዝቃዛ ውሃ እያሸ እንዲረዳው አድርግ። እህቱንም ጥራና በያዘችው ፎጣ እንድታደርቅለት አድርግ። የሚደረገው ሁሉ ስርዓት መልካምና ጥሩ ነገር እንጅ ጥላቻ እንደሌለው ያሳያቸዋል። ይህም ፍቅርን ያመለክታል።

ዛሬ ግን ብዙ ቅጣቶች ፍቅርን ሣይሆን ጥላቻን የሚያመለክቱ ናቸው። ልጆችህን እንደምትወድ ትናገራለህ፣ ነገር ግን ማን ሊያምንህ ይችላል? እኔ እንደዚህ ዓይነቱን ሰው ላምን አልችልም። ስለዚህ ልጆችህ የት ላይ እንዳጠፉ ልታሳያቸው ይገባሃል። ስትማታም በማስታመም ጥላቻ እንደሌለህ እንዲያውቁ አድርግ። ጉዳዩ በጣም ከባድ ከሆነ አባት ወይም እናት ጥቂት ዱላዎችን መጠቀም አለባቸው። ይህም ጉዳዩ ከባድ እንደሆነ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል። ይህም ቅጣት በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ባለማስተዋል ኃጢአት እንዳያደርጉና እንዲያስተውሉ ይረዳቸዋል።

እንግዲህ ያ ያንተ ሳይሆን የጌታ ተግሣፅ ይሆናል። ይህም የአንተ የቁጣ ቅጣት ሣይሆን የጌታ ቅጣት ነው። ቁጣቸውን የማይቆጣጠሩ ወላጆችን ግን እቃወማለሁ። መጥፎ የሆነ የወላጆች ቁጣ የልጆችን የወደፊት ሁኔታ ሊያበላሽ ይችላል። የክርስቲያን ቤተሰብ ወላጆች ማፍቀርንና መቅጣትን መለማመድ አለባቸው።

## ታላላቅ ሰዎች ከታላላቅ ቤተሰብ ተገኝተዋል ፣ ይገኛሉም

በመጨረሻም ብዙዎቹ ታላላቅ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የተገኙት ከታላላቅ ወላጆች እንደሆነ መናገር እፈልጋለሁ። ከጢሞቴዎስ ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ብዙዎቹ የመጡት ከታላላቅ ወላጆች ነው። አንዱ ጆን ሆፕኪንስ ነው። ሌላው ጆንኒውተን ነው። ሶስተኛው ደግሞ በዓለም የታወቀው ሚሽነሪ ጆን ፓተን ነው። እንደ ጆን ፓተን ያለ አባት ያላቸው ልጆች በጣም ጥቂት ናቸው። ጆን በእድሜ ሽምግሎም አድጎም በኃጢአት ሲፈተን አባቱንና አባቱ ለእርሱ ያደርገው የነበረውን ፀሎት ያስታውሣል። ጆን ከድሃ ቤተሰብ የመጣ ነው። ቤታቸው አንድ መኝታ ክፍል፣ አንድ ማድቤትና አንዲት ጠባብ የፀሎት ክፍል ብቻ ነበራቸው። በዚያች ጠባብ ክፍል አባቱ ሲፀልይና ሲቃትት ሲሰማ እርሱም ይጨነቃል። አባቱ ለልጆቹ ነፍስ እንደሚቃትት ያውቃል። ዛሬም እንኳ አድጎ የአባቱን መቃተት ያስታውሣል። እንደዚያ ዓይነት ኃጢአትን የማያደርግና ኃጢአትን ላለማድረግ የሚጠነቀቅ አባት እግዚአብሔር ስለሰጠው ያመሰግናል። ጆን ኃጢአትም ቢያደርግ በሰማይ ያለውን እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን በምድር ይኖር የነበረ አባቱንም እንደበደለ ይሠማዋል። እንደዚህ ያሉ አባቶች በጣም ጥቂቶች ናቸው። እንደ ጆን ያሉ ታላቅ ልጆችም በጣም ጥቂቶች ናቸው።

እኛ ባለንበት ትውልድ ወላጆች ጥሩ ወላጆች ለመሆን ቢማሩ እንዴት ዓይነት ጠንካራና ብርቱ ወንድሞችና እህቶች በሚቀጥለው ትውልድ ይኖሩ ነበር። የወደፊቷ ቤተክርስቲያን ሁኔታ የሚወስነው በአሁኑ ወላጆች እንደሆነ የሚሠማኝን ለመናገር እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ለመባረክ ሊያስነሣቸው የሚችል ሰዎች ካሁኑ ያስፈልጉታል። እንዲያ ቢሆን እግዚአብሔር አገልጋዮቹን ከዓለም ሳይሆን ከክርስቲያን ቤተሰብ የሆኑትን ልጆች በማስነሣት ለሥራው መጠቀም ይችል ነበር።

# ምዕራፍ አሥር
# የገንዘብ አስተዳደር

## ያለህን ሸጠህ ተከተለኝ

ባለፉት ትምህርቶች ጌታን ለመከተል ሁሉን መሸጥ እንደሚያስፈልግ አይተናል። አንድ ሰው ጥሪውን ተቀብሎ ለምላሹ ያለውን ሁሉ ቢሰጥ በመንገዱ ቀስ በቀስ ብዙ ገንዘብና ሀብት ይመጣለታል። እንግዲህ ይህ ከሆነ ሀብቱን እንዴት ያስተዳድር? ሁሉንም መሸጥ ለሰው ባይቻልም ለእግዚአብሔር ግን ይቻላል ። አንድ ጊዜ የተበተነን ገንዘብ መልሶ ለመሰብሰብ አይቻልም ብለህ አታስብ። የተበተነ ገንዘብ ተመልሶ ይሰበሰባል።ይህን ያልተረዳው ግን የያዘው ገንዘብ የራሱ እንደሆነ አድርጎ እንዲመለከትና ወደ ቀደሞ ልማዱ ሊመለስ ይችላል። ነገር ግን አማኝ ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ገንዘብ መስጠትን መለማመድ ያስፈልገዋል ።

ክርስቲያኖች ገንዘባቸውን የሚያስተዳድሩበት መንገድ ፈፅሞ ከማያምኑ ሰዎች መንገድ የተለየ ነው። የክርስቲያኖች መንገድ መስጠት ሲሆን የማያምኑት ግን ማከማቸት ነው ። ስለዚህ የእኛ ትኩረት ክርስቲያን ሁሉ በዚህች ዓለም ሲኖር የሚጎድለው ነገር እንዳይኖር እንዴት መኖር እንዳለበት እንዲያውቅ ለማድረግ ነው ። እግዚአብሔር ይህን ተስፋ አልገባልንምን? የሰማይ ወፎች ምግብ እንደማይጎድልባቸው ወይንም የመስክ አበቦች ያማረ ልብስ እንደማይጎድልባቸው ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆችም ምንም ነገር ሊጎድልባቸው አይችልም ።የጎደለባቸው ነገር ካለ ግን አንድ ቦታ ላይ ክፍተት አለ ማለት ነው ።የገቢ ችግር ያለባቸው ወገኖች ገንዘባቸውን በእግዚአብሔር መመሪያ መሠረት የማያስተዳድሩ ናቸው ።

አንድ ጊዜ ሁሉንም ሸጠህ ጌታን ከተከተልህ ይህንን መመሪያ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ልትይዘው ይገባል። ገንዘብህን በእግዚአብሔር መንገድ ማስተዳደር ይገባሀል። አለበለዚያ ግን ችግር ውስጥ ትወድቃለህ ወይም ችግር ይገጥምሃል ። በእግዚአብሔር መመሪያ መሠረት መኖር እንዴት እንዳለብን ማወቅ ይጠቅመናል ።

# የክርስቲያን የገንዘብ አስተዳደር መመሪያ

## ክርስቲያን እንዴት ነው ገንዘቡን ማስተዳደር ያለበት

" ስጡ ይሰጣችሁማል በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል ።" ( ሉቃ 6፥38)

እኛ አማኞች ለሚያስፈልገን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ማየትና መመልከት አለብን። የምንኖረው በእርሱ ምህረት ብቻ ነው። ባለ ፀጋች በሀብታቸው ማለትም በሚበሉትና በሚለብሱት ሊመኩ አይችሉም። በጦርነት ጊዜ ብዙ ሀብታሞች ሁሉንም እንዳጡ አይተናል። በመሆኑም ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ በማያስተማምን ሀብት ተስፋ እንዳናደርግና ሀብታም ለመሆን እንዳንመኝ ይመክረናል። ይህን ማድረግ ግን በብዙ መከራ ወይም ጥፋት ይወጋናል (1ጢሞ 6፥7፤10፥17-19)። እምነታቸውን በጌታ ላይ ያደረጉ ምንም እንኳ ያስቀመጡት ገንዘብ ባይኖራቸውም የሚጎድላቸው ነገር አይኖርም። እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ በሚገባ መሙላት ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር የሚሞላው አንድ ነገር ሲሟላ መሆኑን ሊያውቁ ይገባል ።

እግዚአብሔር የሰማይ ወፎችን መመገብ ከቻለ እኛን መርዳት እንደሚችል የተረጋገጠ ነው ። የሰማይ ወፎችን ሁሉ ሰው መመገብ አይችልም። እግዚአብሔር ግን ይችላል። የመስክ አበቦችንም ማሳመር ይችላል። ለሰማይ ወፎች፣ ለመስክ አበቦችና ለራሱ ልጆች የሚበቃ የተትረፈረፈ ሀብት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ ልንኖርበት የምንችል ቀጥተኛ የሆነ ሁኔታ እንደዚህ በግልፅ የተቀመጠ የለም ። በድህነት የወደቀ ሰው ገንዘቡን በእግዚአብሔር መመሪያ መሠረት ማስተዳደር ያልቻለ ነው። እግዚአብሔር ገንዘባችንን እንዴት መጠቀም እንዳለብን መንገዱን አሳይቶናል። ይህንን የመዝራት ሕግ ካልተከተልን ወደ ድህነት እንደምንወድቅ ግልፅ ነው። ከጎደሉ ነገር የምናመልጠው ይህንን የእግዚአብሔርን ሕግ በመከተል ብቻ ነው ።

የሚያስፈልገን ነገር ካለ እግዚአብሔር ሁሉንም አትረፍርፎ ሊሰጠን ፈቃደኛ ነው ። እግዚአብሔር ድሃ አይደለም፣ በተራሮች ሁሉ ላይ ያሉ ንብረቶች በሙሉ የእርሱ ናቸው ። ሁሉ ነገር የእርሱ ነው። ታዲያ ለምንድን ነው የእግዚአብሔር ልጆች ድሃ የሚሆኑት ?ለምንድን ነው የሚጎድላቸውስ ነገር ያለ? እግዚአብሔር መሙላት የማይችል አምላክ አይደለም። በእርግጥም ሊሞላብን ይችላል። ነገር ግን እኛ የግድ ልናደርግ የሚገባን አንድ ነገር አለ። ይህም እርሱ ሊሞላብን ከመቻሉ

በፊት እንድናሟላ የሚያስፈልገውን ነገር ማሟላት አለብን። ታዲያ የእርሱ ጥያቄ ምንድን ነው? ስጡ ይሰጣችሁማል የሚል ነው ።

በገንዘብ ችግር ውስጥ ያሉ ወንድሞች አጋጥመውኛል። የእነርሱ ችግር ሳይኖራቸው ቀርቶ ሳይሆን በሚገባ አለመስጠታቸው ነው። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሳየን መመሪያ መስጠት ያበለፅጋል ማከማቸት ግን ያደኸያል የሚል ነው። ድሃ ነኝ ብሎ ራሱን የሚቆጥር ነገር ግን የሚሰጥ ሰው ሃብታም ነው ።እግዚአብሔር ተናግሯል፣ ይሆናልም። ድህነትን ለማስወገድ መስጠት አለብህ። ሁል ጊዜ ስጥ ። ብዙ ስትሰጥ እግዚአብሔር ደግሞ አብዝቶ ይሰጥሃል። ከሚያስፈልግህ በላይ የሆነውን ነገር ሁሉ ለመስጠት ፈቃደኛ ብትሆን አንድ ቀን ለሌሎች ከሚያስፈልጋቸው በላይ ያለውን ለአንተ ይሰጥሃል ። አንድ ሃያኛውን ለሌሎች ብትሰጥ አንድ ሃያኛው ሰላሳ፣ ስድሳና መቶ እጥፍ ሆኖ ይሰጥሃል። አንድ ሺህኛውን ብትሰጥ አንድ ሺህኛውም በዚያው ስሌት ይሰጥሃል ።

ብዙ በማከማቸትህ ምክንያት ምንም እንደማያስፈልግህ አውቀህ ባትሰጥ ማን ያውቃል ነገ ምን እንደሚሆን ያለኝ በቂ ነው ብለህ አትዘናጋ። ለሌሎች በሰፈርክበት መስፈሪያ ላንተም ይሰፈርልሃል። ወንድሞችንና እህቶችን ባስተናገድክበት መንገድ እግዚአብሔር ይንከባከብሃል። ያለህን ሁሉ ለሌሎች ብትሰጥ ሌሎችም ለአንተ ይሰጡሃል። ነገር ግን ለአንተ የማይጠቅምህን ነገር ብትሰጥ ሌሎችም እንዲህ ያደርጉብሃል። የማይበቃ ገቢ ሁል ጊዜ ምክንያቱ በቂ ያልሆነ አሠጣጥ ነው። ትክክለኛ አሰጣጥ በቂ የሆነ ገቢን ለማግኘት ዋስትና ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግልጽ ነው " ስጡ ይሰጣችሁማል።" ለሌሎች ስጡ ጌታም ለእናንተ ይሰጣችኋል። የማትሰጡ ከሆነ ግን እግዚአብሔርም ለእናንተ ለመስጠት ግዴታ አይለውም። ብዙዎች ገንዘብ እንዲሠጣቸው ለመለመን እምነት አላቸው፣ ነገር ግን ለመስጠት እምነት የላቸውም። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ቢደኸዩ አያስደንቅም። ከእግዚአብሔር ለመቀበል እንኳ የእምነት ደሃ ቢሆኑም አያስደንቅም ።

አማኞች ይህን መሰረታዊ ትምህርት ወደ ጌታ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ መለማመድ አለባቸው። አለበለዚያ ግን ርቀው መጓዝ አይችሉም። ክርስቲያኖች ገንዘባቸውን የሚያስተዳድሩበት የተለየ መንገድ አላቸው። ይህም ለመቀበል እንደምትፈልገው ስጥ፣ በሌላ አባባል በመስጠት ገቢህን ለካ። የማያምኑ ሰዎች የሚሰጡትን የሚለኩት በገቢያቸው ነው። ነገር ግን እኛ ክርስቲያኖች ገቢያችንን በመስጠት እንለካለን። እኛ በመስጠት የምንለካው የምንቀበለውን ነው። ስለዚህ ገንዘብን የሚወዱና ለመስጠት የሚደራደሩ ሰዎች የእግዘአብሔርን ገንዘብ ሊያገኙ አይችሉም፣ የእግዚአብሔርንም መሞላት አያገኙም ። ማንኛውም ሰው

የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘትና ለማሟላት እግዚአብሔርን ማየት እንዳለበት ለእህቶችና ለወንድሞች መንገር እፈልጋለሁ። በእርግጥም እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ለመሙላት ቃል የገባው ለመስጠት ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ብቻ ነው ። ሉቃስ ላይ ያለው በእውነት የሚያስደንቀው ቃል "በመልካም መስፈሪያ" ይላል። በሚሰጥበት ጊዜ እግዚአብሔር ሂሳብ ውስጥ አይገባም። ሁል ጊዜ አትረፍርፎ ይሰጣል። እግዚአብሔር በጣም ለጋስ ነው ። እስኪፈስ ድረስ ሁል ጊዜ ሞልቶ ይሰጣል። ስስታም አይደለም። በመልካም መስፈሪያ እንደሚሰጥ ይናገራል። "የተጨቆነና የተነቀነቀ፣ የተትረፈረፈም" ይሰጣል። የተትረፈረፈ "ሩዝ" ወይም "ስንዴ" ገዝተሃልን ? አንዳንድ ነጋዴዎች ከመስፈሪያው ውጭ እህሉ እንዲፈስ ያደርጉ ይሆናል። ነገር ግን እህሉ እንዲነቀነቅ አይፈቅዱልህም። እግዚአብሔር ግን እንደነርሱ አይደለም። እግዚአብሔር የሚሰጠው በመልካም መስፈሪያ የተጨቆነና የተነቀነቀም ብቻ ሳይሆን የተትረፈረፈም ጭምር ነው ። በእውነት አምላካችን በመስጠት ነፃ ነው ። ነገር ግን እርሱ የሚለውን አዳምጥ፣ ስማ። "በሰፈርክበት መስፈሪያ ይሰፈርልሃል" አንተ የምትሰጠው እስልተህና በትክክል ያችኑ ብቻ ከሆነ የሚያስፈልግህን እንዲሞሉብህ እግዚአብብሔር ወዳንተ የሚልካቸው ሰዎችም የሚሰጡህ በትክክል ያችኑ እስልተው ነው።

## ሁለት ተጓዳኝ ምስክርነቶች

### 1. የሚስተር ሙሌ ታሪክ

ሃንድሊ ሲ.ጄ ሙሌ የተባለ እንግሊዛዊ "የሕይወትና እምነት" መፅሔት አዘጋጅ ነበር ። ይህ ሰው በጌታ ፊት ስላደረጋቸው ነገሮች ብዙ ይባላል። አንዱ ጠንካራ ጎኑም የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀቱ ነው። በእምነት ይኖራል። ሁል ጊዜ በገንዘብ የጎደለ ነገር ሲገጥመው ሚስቱን በመስጠት አንድ ችግር እንዳለባቸው ይነግራታል። ምን ያህል እንደሰጡ አያተኩርም ችግሩ ምን ላይ እንደሆነ ይፈልጋል እንጂ ።

አንድ ወቅት ቀለባቸው አለቀ። የታወቀው የእንግሊዝ ምግብ ማለትም ዱቄታቸው ፈፅሞ ተሟጠጠ። አንድና ሁለት ቀን ቢጠብቁም ምንም የመጣ ነገር አልነበረም። ስለዚህ እርሱና ባለቤቱ ባንድ ላይ ፀለዩ። ኃጢአት ነው ብለው ያሰቡትን ነገር ሁሉ ተናዘዙ። በቤታቸውም በትርፍነት ብዙ ነገር ይኖር ይሆናል በማለት አሰሳ አደረጉ ። ይህ ሰው በመጀመሪያ እግዚአብሔር ዱቄት እንዲሰጠው አልፀለየም ። በዚህ ፋንታ ግን በቤታቸው ውስጥ ብዙ ነገር ያለጥቅም ሊኖር ስለሚችል ሚስቱን እንድትፈልግ ነገራት። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሊሰጣቸው እንዳልቻለ ገለፀላት። ስለሆነም እግዚአብሔር ይህን በብዛት ያላቸውን ነገር

እንዲያሳያቸው ተንበርክከው ካፀለዩ በኋላ ከጓዳ ጀምረው በብዛት ያላቸውን ነገር መፈለግ ጀመሩ። ጓዳ ጎድጓዳውን ካዳረሱ በኋላ የልጆች እንኳን ልብስ ሣይቀር ቢፈልጉ ምንም ነገር ሊያገኙ አልቻሉም። ሚስተር ሙሌም እንዲህ አለ "ጌታ ሆይ ያለ ጥቅም የተቀመጠ ነገር የለንም። ስለዚህ ባለመስጠት ያጣነው ነገር ያለ አይመስለኝም" አለ ። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር እንደማይሳሳት አሰበ። ስለሆነም ፍለጋቸውን ቀጠሉ። መጨረሻ ላይ ግን ምድር ቤት ከትንሽ ቀኖች ቀደም ብሎ የተሰጣቸው አንድ ገረ ወይና ቅቤ አገኙ። ሚስተር ሙሌም ይህን ቅቤ ሲያይ በጣም ተደሰተ። ምክንያቱም ጥያቄ የሆነው ነገር ይህ እንደሆነ አውቋል ።

እነዚህ ሰዎችም ለብዙ ዓመታት የመስጠትን ትምህርት የተማሩና መስጠትን የተለማመዱ ናቸው። " ስጡ ይሰጣችሁማል" የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ያውቃሉ። ስለሆነም ከቅቤው ከፍለው ከቅዱሳን መካከል ደሃ ለሆኑ ሰዎች ላኩላቸው። ቅቤውን ከሰጡም በኋላ ሚስተር ሙሌ ለሚስቱ "ሁሉ ነገር ተስተካክሏል" አላት። ተንበረከከናም "እግዚአብሔር ሆይ ስጡ ይሰጣችሁማል ያልከውን ብቻ ላስታውስህ እፈልጋለሁ፣ አሁን በቤታችን ምንም ዱቄት እንደሌለ አስብ "በማለት ፀለየ ።

ይህ ነገር የሆነው እሁድ ምሽት ነበር። ቅቤውን ከተቀበሉት መካከል አንዷ በጣም ድሀና የአልጋ ቁራኛ የሆነች አካለ ስንኩል እህት ነበረች። ለብዙ ቀናትም ያለ ቅቤ ዳቦ ትበላ ነበር። ስለሆነም "ጌታ ሆይ ፀጋህን አብዛልኝ ቅቤም ስጠኝ" ብላ ፀልያ ነበር። ሚስተር ሙሌ ቅቤ ይዞላት ሲመጣም ረጅም ጊዜ አልፈጀም። ፀሎቷ ስለተመለሰ ጌታን አመሰገነች። ቅቤዋን ከወሰደች በኋላም እንዲህ ብላ ፀለየች "ወንድማችን ምንም ነገር ባይጎለውም የጎደለ ነገር ኖሮት ሲፀልይ ግን እባክን ፀሎቱን ሰማው። ሚስተር ሙሌ የጎደለው ነገር እንዳለ ምንም እንድታውቅ ስላልፈቀደ የሚያስፈልገው ነገር እንዳለ ምንም አታውቅም ነበር። እንዲያውም በብዙዎች ዘንድ ሀብታም ወንድም እንደሆነ ይታሰባል ። ከዚህ የምንረዳው ይህ ወንድም ለሌሎች ቅቤውን ባይሰጥ ኖሮ ለሌሎች ሊከፋፈል የሚችል ቅቤ በቤቱ በከንቱ ይቀመጥ ነበር ። ነገር ግን ቅቤውን በመስጠቱ ይህች እህት ፀለየችለት ። በሁለትና በሶስት ሰአት ጊዜ ውስጥ ሁለት ጆንያ ዱቄት ተቀበለ፣ ችግሩም ተወገደለት ።

እዚህ ላይ ልናውቅ የሚገባ ነገር በማንኛውም ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ማመን ያለብን መሆኑን ነው ። ብዙዎቹ በእግዘአብሔር ቃል ላይ ችግር አለባቸው ፣ የእግዘአብሔርን ቃል ለማመን ይቸግራቸዋል። እንደ ሚስተር ሙሌ ያሉት ግን እግዚአብሔርን

የሚያውቁት በቃሉ ነው። ስጡ ይሰጣችሁማል። አማኞች ሁሉ መስጠትን መለማመድ አለባቸው። መስጠት የሚያደኸይ ወይም ያለንን የሚያራቁት አይደለም። የእኛ መስጠት እግዚአብሔርን እንዲሰጥ ያደርገዋል። መስጠት የክርስቲያኖች የገንዘብ የማስተዳደር መመሪያ ነው።

መስጠት ስህተት ከሆነ መቀበልም ስህተት ነው ። አንድ ሰው ከሌሎች ለመቀበል ቢፈልግ በዚህ መመሪያ መሠረት ጥቂት ቢያገኝ ብዙ መስጠት አለበት ። እንዲህ ቢያደርግ ብዙ ይቀበላል ። ብዙዎች በእጃቸው ያለውን ነገር ለመያዝ ይሞክራሉ። ስለሆነም እግዚአብሔር ያንኑ ብቻ ይፈቅድላቸዋል፣ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች መስጠት እንዴት እንደሆነ አልተማሩም። የመስጠት ፀጋ በአንተ ከሌለ የእግዚአብሔር የማብዛት ፀጋ ባንተ ላይ አይሆንም። በሌሎች ላይ ፀጋህን ካላሳየህ እግዚአብሔርም ፀጋውን በአንተ ላይ አያሳይም ።

## 2. ስለመስጠት የእኔ የመጀመሪያ ልምምድ

መስጠትን በተመለከተ ጉዳይ ብዙ ምስክርነቶች አሉኝ ። ነገር ግን በመጀመሪያው ልምምዴ ብቻ ራሴን እወስናለሁ ። ነገሩ የሆነው 1928 ነው ። በዚህ ወቅት ገና ተማሪ ነበርኩ። በአንድ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ አማካኝነትም ቸንኡ በተባለች ከተማ በተዘጋጀ አንድ የመነቃቃት ስብሰባ ላይ እንድሰብክ ተጋበዝኩ ። ቸንኡ ከምኖርባት ከፋቾ ከተማ 180 ማይል ትርቃለች ። እኔም ጓደኛዬን ለዚህ ጉዞ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ጠየቅሁት ። እርሱም ሰባ ወይንም ሰማንያ ዶላር እንደሚያስፈልግ ፣ ነገር ግን ለመመለስ ከዚህ ያነሰ እንደሚጠይቅ ነገረኝ ። እኔም ግብዣውን ከመቀበሌ በፊት ወደ ቸንኡ መሄድ እችል እንደሆነ እግዘአብሔርን ልጠይቅ አልሁት ። በዚሁ ተስማማንና ተለያየን። በዚያ ጊዜ በእጄ አንድ ሣንቲም እንኳ አልነበረኝም ። ከዚያም እግዚአብሔር ወደ ቸንኡ መሄዴን ይፈልግ ከሆነ ገንዘብ እንዲሠጠኝ ፀለይሁ ። ጌታም ገንዘብ ይስጠኝ ጀመር ። ገንዘብ ማግኘት ስለጀመርሁም ወደ ቸንኡ ለመሄዱ ወሰንሁ ። ነገር ግን ያገኘሁት ገንዘብ ጉዞው ከሚጠይቀው በሁለትና በሦስት እጥፍ የሚያንስ ነበር ። የተሰጠኝ ገንዘብ ሃያ ዶላርና ጥቂት ሣንቲሞች ብቻ ነበሩ ። ይሁን እንጂ በቀሩኝ ቀናት የሚያስፈልገኝን ያህል ይሟላል ብዬ አሰብሁ ። ጓደኛዬም ከቸንኡ ሆኖ ሁሉ ነገር የተጠናቀቀ መሆኑንና በተባለው ቀን የግድ መድረስ እንዳለብኝ ጻፈልኝ ። እኔም ከስብሰባው ቀን ቀደም ብዬ ጓርብ እንደምነሳ ቴሌግራም አደረግሁለት ።

ወደ ቸንኡ ለመንቀሳቀስ አንድ ቀን ሲቀረኝ ማለትም ሐሙስ ሌላ ነገር ተከሰተ ። "ስጡ ይሰጣችሁማል" የሚል ቃል ወደ ልቤ መጣ ፣ ትንሽ ተረበሽኩ ። እንድረበሽ ያደረገኝ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ሳይሆን በእጄ ያለው ገንዘብ ለጉዞዬ አለመብቃቱ እየታወቀና ተጨማሪ

የጉዞ ገንዘብ እያስፈለገኝ ባለሁበት ሰዓት በእጄ የገባውን ገንዘብ ስጥ መባሌ ነው ። ይህ ቃል በውስጤ እየተደጋገመ መጣ ፣ ጠንከር ያለም ነበር ። ከዚያም ለመስጠት ወሰንኩ ። በውስጤም የተሰማኝ ሃያውን ዶላር እንድሰጥና ሣንቲሟን ብቻ እንድይዝ ነው። ስለሆነም ለማን መስጠት እንዳለብኝ ጸለይሁ ። በዚህ ጊዜ አንድ ቤተሰብ ላለው ወንድም ስጥ አለኝ። ከዚህ በኋላ "እሺ ወይም እምቢ" አላልሁም ። ከተንበረከክሁበት ተነሳሁና በቀጥታ ወደዚህ ወንድም ቤት ጉዞ ጀመርኩ ። የሚገርማችሁ ነገር ይህን ወንድም ገና ግማሽ መንገድ ሳልሄድ አገኘሁት ። በእጄ ያለውን ገንዘብ መስጠት ግድ ሆነ ። ለዚያ ወንድም "ጌታ ይህንን ገንዘብ በእጁ ላይ አድርግለት ብሎኛል " አልኩትና እጁ ላይ አስቀምጬለት ተጨማሪ ቃል ሳልተነፍስ ከፊቱ ዘወር አልሁ ። ጠቂት እንደተራመድሁ የቸንእ ሰብሰባ ታሰበኝና እንባዬ በፊቴ መንጠባጠብ ጀመረ ። ምክንያቱም ቸንእ ላለው ጓደኛዬ በስብሰባው ላይ የምገኝ መሆኑን ቴሌግራም አድርጌ ነበርና ነው ። ከዚህ በተጨማሪ በቃሌም አለመገኘቴን ሳስበው አስለቀሰኝ ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር " ስጡ ይሰጣችሁማል" ያለውን የተስፋ ቃል ሳስብ ልቤ ሰላም አገኘ ።

እኔም እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝን የሚሞላብኝ ሰዓት ይህ ነው ብዬ አሰብኩ ። ነገር ግን ሐሙስም ሆነ ዐርብ ማታ ከያዝኩት ሣንቲም በስተቀር ያገኘሁት አንድ ዶላር እንኳ አልነበረም ። ዐርብ ማታ አንድ ወንድም ሊሸኘኝ መጣ ። ጉዞው የማታ ጉዞ ነበር ። ሻንጣዬንም ተሸክሞ ወደ ወደቡ ወሰደልኝ ። ወደ ሆንግ ሳንግ ብሪጅ መርከብ አስይዞኝ ተመለሰ ። እኔም ወደ ስዋይኮው የምትወስደኝ ርካሽ ጀልባ ፈለግሁና የሆንግሳንግ ብሪጅ ትኬት አስቆርጬ ተሳፈርኩ ። በጣም ፈራሁ ። በዚህ ላይ ከፋቸ ወጥቼ አላውቅም ። እርግጥ ነው ስዋይኮው ከፋቾ ቅርብ ስለሆነች የሚያስጠይቀው የጉዞ ገንዘብ በሣንቲም ቤት ነው ። ስለሆነም ስዋይኮው ለመድረስ የሚከፈል በቂ ሣንቲም ነበረኝ ። ከፍተኛ ዶላር የሚጠይቀው ግን ከዚያ በኋላ ያለው ጉዞ ነው። ያ ወንድም ሸኝቶኝ ከተመለሰ በኋላ እንቅልፍ እስኪ ወስደኝ ድረስ ጀልባዬ ውስጥ ሆኜ እንዲህ በማለት መፀለይ ጀመርኩ። "ጌታ ሆይ እንግዲህ ስጥ ባልከኝ መሠረት ያለኝን በሙሉ ሰጥቻለሁ፣ ከዚህ በኋላ ያለው ኃላፊነት የራስህ ነው።" ከተወሰነ ሰዓት በኋላ ሆንግ ሳንግ ብሪጅ ደረስኩ ። ሆንግ ሳንግ ብሪጅ እንደደረስሁም ሌላ ጀልባ ለወጥሁ ። ምክንያቱም ምናልባት በሌላ ጀልባ ላይ ቢያንስ የማውቀው ሰው አገኝ ይሆናል በማለትና እግዚአብሔርም የማውቀው ሰው ባገኝ የሚያስፈልገኝን ለመሙላት ቀላል ይሆንለታል ብዬ በማሰብ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ በለወጥኩት ጀልባም ቢሆን የማውቀው ሰው ላገኝ አልቻልኩም። ስለሆነም ለመጨረሻ ሙከራ እንዲያው የማውቀው ሰው አገኝ ይሆናል በሚል እምነት የጀልባዋ መንቀሳቀሻ ጊዜ እስኪደርስ ከጀልባዋ ወርጄ ወደቡ ላይ ጥቂት ተዘዋወርኩ ፣ በዚያም የማውቀው ማንም ሰው አልነበረም ። ወደ

ጀልባዬ ተመለስኩ ። በልቤም "ጌታ ባዘዘኝ መሠረት እስከስጠሁ ድረስ ስለ እኔ ራሱ ያስባል " በማለት ተጽናናሁ ።

በሚቀጥለው ቀን ጀልባዋ ሰዋይኮው ደረሰች ። ከዚያም ለመጨረሻ ጊዜ ሌላ የግል ጀልባ መያዝ ነበረብኝ። ብዙ ገንዘብ የሚጠይቀውም ይህ ጉዞ ነው ። እስካሁን የጠየቀኝ ጉዞ በሳንቲም ቤት ስለነበር አልተቸገርኩም ። ከዚህ በኋላ ግን ከሰማንያ ዶላር ያላነሰ ያስፈልገኛል ። በእጄ የቀረኝ ፍራንክ ደግሞ ሰባ ሣንቲም ብቻ ነው ። ሐሳቤ ሁሉ ተከፋፈለ ። እንዲህ ብዬም ጸለይኩ-

"ጌታ ሆይ አሁን ሰዋይኮው ደርሻለሁ ። ወደ ቸንኡ የምሄድበት ገንዘብ ግን የለኝም ። ስለዚህ ወደ ፋቾ እንድመለስ ባለችኝ ሣንቲም የመመለሻ ትኬት ልግዛን ?" አልኩት ። ወዲያውም እንዲህ ሲል ተናገረኝ ። "ለምን በርካሽ ዋጋ መሄድ የምትችልበት ምቹ የሆነ መርከብ እንዲዘጋጅልህ አትጸልይም ?" ፍጹም ግልጽ ንግግር ነበር ። ከሰው ጋር እንደምነጋገር ሆኖ ታወቀኝ ። እኔም "ጌታ ሆይ ከአሁን በኋላ ገንዘብ አልጠይቅህም ነገር ግን ባለኝ በዚህ ሣንቲም ቸንኡ እንድታደርሰኝ እለምንሃለሁ" አልኩና ጸለይሁ ። የሚገርመው ነገር በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ልቤ በሰላም ተሞልቶ ነበር ።

በዚህ በሰዋይኮው ወደብ ላይ ከአንዲት መርከብ ተጠግቼ ቆሜ ነበር ። መርከበኛውም ወደ እኔ መጣና ወደ ናፒንግ ወይም ወደ ቸንኡ እሄድ እንደሆን ጠየቀኝ ። ለመሄድም የተቻኮለ ነበር ። እኔም ወደ ቸንኡ እንደምሄድ ፣ ነገር ግን ሰባ ሣንቲም ብቻ እንዳለኝ ነገርኩት ። እርሱም ጥቂት ካሰበ በኋላ ሊወስደኝ እንደሚችል ነገረኝ ። እኔም ሊገባኝ ስላልቻለ ሣንቲም የሚለውን ቃል እንዲደግምልኝ መልሼ ጠየቅሁት። እርሱም መልሶ " ሰባ ሣ.ን.ቲ.ም " አለኝ ፡ብያዝኩት ሣንቲም ማለት ነው ። ስለገረመኝ ሰባና ሰማንያ ዶላር የሚጠይቀው ጉዞ ለምን ዋጋው እንዲህ ሊቀንስልኝ እንደቻለ ጠየቅሁት ። እርሱም ጀልባዋን አንድ የመንግሥት ባለስልጣን በመንግሥት ወጪ ኮንትራት ይዞ ወደ ቸንኡ ለመሄድ የተከራያት መሆኑንና ይህም ባለሥልጣን መርከበኛውን ለመርዳት ስለፈለገ በተወሰነ ገንዘብ በመርከቧ የኋላ ፋርጎ ሰዎችን ሊጭን እንደሚችል የፈቀደለት መሆኑን ነገረኝ ። ይህ ምስኪን መርከበኛ በዚህ አጋጣሚ ከኔ የሚያገኛትን ፍራንክ ማጣት አልፈለገም ። አነስተኛ ሣንቲምም ብትሆን ለእርሱ ወጪ የሌለባት ነፃ ገቢ ስለሆነች ሊጭነኝ ተስማማ። ይህችን መርከብ ጌታ እንዳዘጋጀልኝ በዚህ አወቅሁ ። ሻንጣዬን ወደ መርከቧ እንዲያስገባና እንዲጭን ሰጠሁት ። ከዚያም ወደ ቸንኡ ጉዟችንን ቀጠልን ። በዚህ ሁኔታ ቸንኡ ገባሁ ። የቸንኡም ጉዞ በዚህ ተጠናቀቀ ።

ይሁን እንጂ የመመለሻውም ነገር ቀላል አልነበረም ። በኪሴ ምንም ፍራንክ አልነበረኝም ። በዚህ ላይ ትምህርት ቤት ስለሚከፈት ስብሰባው እንዳለቀ ወዲያውኑ መመለስ ነበረብኝ ። ስለሆነም የመመለሻዬን ነገር እግዚአብሔር እንዲያዘጋጅ መጸለዬን ቀጠልሁ ። ወደ ፋቶ ለመሄድ አንድ ቀን ሲቀር ከአንድ ሚሲዮናዊ ቤት ራት ተጋበዝኩ ። ከራት በኋላም ወደ ማረፊያ ሥፍራዬ ለመሄድ ስነሳ ይህ ሚሲዮናዊ " ሚስተር ኒ የአንተ ጉብኝት በጣም ረድቶናል" አለኝና ቀጠል አድርጎ በለሆሳስ "እንዲያው ፈቃድህ ቢሆን እባክህን የመመለሻህን ወጪ እኔ ልሸፍን?" ሲል ጠየቀኝ ። ውስጤ በደስታ ዘለለ ። ነገር ግን ተግደረደርኩ፡ "ስለ እኔ ኃላፊነት ያለበት ሌላ አለ "አልኩት ። እርሱም የእኔን ወጪ ለመሸፈን በመጠየቁ እንደተሳሳተና ይቅርታ እንዳደርግለት በትህትና ጠየቀኝ ። ከዚያም ገንዘቡን ወደ ኪሱ መለሰና አሰናበተኝ ። ቤቴ ከተመለስኩ በኋላ ባደረግሁት ነገር ተጸጸትሁ ፣ ይሁን እንጂ በልቤ ትልቅ እረፍት ነበረኝ ።

በሚቀጥለው ቀን ለጉዞ ተነሳሁ ። ልብ አድርጉ ፣ በኪሴ ምንም ፍራንክ የለኝም ። የቻንኡ ጓደኛዬም ሻንጣዬን ቀደም አድርጎ ወደ ወደቡ ከላከ በኋላ ወደ ፋቶ የምሄድበትን መርከብ ለማስያዝ ወደ አረፍኩበት ሥፍራ መጣ ። አብረን ጉዞ ጀመርን ። በውስጤ ግን እጸልያለሁ ። "ጌታ ሆይ ወደ ቻንኡ እንዳመጣኸኝ ሁሉ ወደ ፋቶም ልትመልሰኝ ትችላለህ። ስለ እኔ ጉዳይ ኃላፊነት አለብህ ፣ ካንተ በቀር ስለ እኔ ጉዳይ ኃላፊ ሊሆን የሚችል የለም ፣ አይኖርምም " እያልኩ በጸሎት አሰላስል ነበር። ከዚህ ከሚሸኘኝ ጓደኛዬ ጋር ሆነን ወደ ወደቡ እያመራን ሳለ አንድ ሰው እየሮጠ ወደ እኛ መጣና ከሚሲዮናዊው የተላከ ደብዳቤ ሰጠኝ። ከፍቼ ሳየው ውስጤን በደስታ አዘለለው ። ደብዳቤ ብቻ አይደለም፣ ገንዘብም ይዟል። " ስለ አንተ ኃላፊነት ያለበት ሌላ እንዳለ አውቃለሁ፣ ነገር ግን የዚህን ጉዞ ወጪ እንድሸፍን ጌታ ተናግሮኛልና እባክህ እኔ ሽማግሌው ወንድምህ በዚህ እድል የወጪህ ተካፋይ እንድሆን ይህችን ትንሽ ስጦታ ተቀበለኝ " የሚል ነበር። እኔም መልዕክቱን ከተቀበልሁ በኋላ "ጌታ ሆይ ይህንን ገንዘብ በትክክለኛው ጊዜ የላክህልኝ አንተ ነህ " በማለት አምላኬን ደጋግሜ አመሰገንሁ። ይህን ገንዘብ ለመጨረሻ ብቻ ሳይሆን "መነቃቃት" የሚል አንድ በራሪ ጽሑፍም ለማሳተም ተጠቅሚበታለሁ ። ታሪኩ በዚህ ብቻ አላበቃም ።

ከቻንኡ ከተመለስኩ በኋላ ያንን ሃያ ዶላር የሰጠሁትን አገልጋይ ልጎበኝ ወደ ቤቱ ሄድኩ ። ስሄድ ሚስቱን አገኘኋት ። እርሷም እንደተገናኘን በመጀመሪያ ያቀረበችልኝ ጥያቄ፦ " ወደ ቻንኡ ከመሄድህ በፊት ሃያ ዶላር ለምን ልትሰጠን እንደወደድህ ብትነግረኝ ?" የሚል

ነበር ፡፡ እኔም"እግዚአብሔር እንድሰጣችሁ ስለተናገረኝ ነው" አልኳት ፡፡ እሷም እንዲህ በማለት በዚያ ወቅት የነበሩበትን ሁኔታ መሰከረችልኝ ፡፡ " በዚያ ምሽት የመጨረሻ ራት ብቻ ነው የነበረን ፡፡ ከዚያ በኋላ ምን እንደምንመገብ አናውቅም ነበር ፡፡ ስለሆነም እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን እንዲያዘጋጅልን ለሦስት ቀን በጌታ ፊት በጸሎት ቆየን ፡፡ እግዚአብሔርም አንተን ገንዘብ አስይዞ ላከልን ፡፡ በሰጠኸንም ገንዘብ እግዘአብሔር ሌላ እስኪያዘጋጅልን ድረስ የሚያቆይ ሩዝና የምግብ ማብሰያ ጋዝ ገዛንበት " አለችኝ ፡፡ የእኔን ታሪክ አልነገርኳትም ነገር ግን ቤቷን ለቅቄ ከሄድኩ በኋላ መንገድ ላይ እንዲህ እያልኩ አሰላሰልኩ፣ ያንን ሃያ ዶላር እኪሴ ውስጥ አስቀምጬው ቢሆን ኖሮ የሞተ ዋጋ ቢስ በሆነ ነበር ፡፡ ነገር ግን በተሰጠ ጊዜ ጠቃሚ ሆኗል፡፡ ስለሆነም ራሴን ወደ ላይ አቅንቼ ወደ ጌታ እንደገና ቀደስኩ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እሰጣለሁ፡፡ በኪሴ አገልግሎት የማይሰጥ ገንዘብ አላስቀምጥም ፡፡

የእኔ ምኞትም በእኔ መስጠት እግዚአብሔር ተአምር እንዲሠራ ነው፡፡ ገንዘቤን በመስጠቴ እግዚአብሔር ፀሎትን ይመልሣል፡፡ ማንኛውንም ገንዘብ በእጄ ላይ አስቀምጬ ለአስፈላጊው ጉዳይ በጊዜው እንዳይውል አላደርገውም፡፡ ይህን ስናገር ግን እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ያህል ልምምድ እንዳለኝ ለመፎከር ሳይሆን ምን አልባት ብዙ በመስጠት ከሌላው ንፉግ ሰው በተሻለ ብዙ የተቀበልኩ መሆኔን ለማሳሰብ ነው ፡፡ በመሆኑም ብዙ ገንዘብ በእጄ ተዘዋውሯል፡፡ እንደሞኝ እናገራለሁ እኔ ገንዘቤ እንዲወጣና ተአምር እንዲሠራ፣ ፀሎትንም እንዲመልስ እመርጣለሁ፡፡ ያለ ስራ እንዲቀመጥና ጥቅመ ቢስ እንዲሆን ግን አልፈልግም ፡፡

አማኞችም ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ገንዘባቸውን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባቸው ሊያውቁ ይገባል ፡፡ እኔ በግሌ ብዙ ነገር ለማለት አልፈልግም ነገር ግን እንዲሞከሩና ፊትነው እንዲያረጋግጡ እፈልጋለሁ፡፡ ከ1923 ጀምሮ ብዙ ጊዜ እስከ መጨረሻዋ ሣንቲም የወረድኩበት ጊዜ ነበር ፡፡ ምን አልባትም በቻይና ከሚገኙ ወንድሞች ከማናቸውም ይልቅ ይህ ነገር በእኔ ደርሷል፡፡ የራሴን ታሪክ አውቃለሁ፡፡ የመጨረሻዋ ሣንቲም ምን ማለት እንደሆነችም አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን በሚያስፈልገኝ ጊዜ የጌታ ቃል " ስጡ ይሰጣችሁማል" የሚለውን አስባለሁ፡፡ ዛሬ ይህን ተምሬአለሁ፡፡ ለሌሎች ስሰጥ እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝን ይሞላብኛል ፡፡ ከልምድ እንደማውቀው የሚቀበሉ የሚሰጡ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ሕይወት እንደሚያሳየኝ በነፃነት ስሰጥ እግዚአብሔርም በነፃነት ይሰጠኛል ፡፡ " ወንድም ኒ ባለፀጋ ነው" እባላለሁ፡፡ በእርግጥም ገንዘብ አለኝ፡፡ ይህም የሆነው ሁል ጊዜ ስለምሰጥ ነው፡፡ የሚገርመው ደግሞ ለሰጠሁት የማገኘው ምላሽ እጥፍ ነው ፡፡ የእኛ አምላክ ስስታም አይደለም ፡፡

## የክርስቲያን ገንዘብን የማስተዳደሪያ መንገድ

ክርስቲያኖች ገንዘብን የሚያስተዳድሩበት መንገድ በእጃቸው አጥብቀው በመያዝ አይደለም። አጥብቀው የሚይዙ ሰዎች ድህነት እያስጋቸው ይመጣል። እንደዚህ ዓይነቱ ገንዘብ ዋጋ ቢስ ነው ። እንደበረዶ ይቀልጣል። ገንዘብ የሚጨምረው በመስጠት ብቻ ነው ። የእግዚአብሔር ልጆች እንዴት እንደሚሰጡ ቢያውቁ እግዚአብሔር ታምራቱን በየትኛውም ቦታ ያደርጋል ። ገንዘብን ማከማቸት ግን የእግዚአብሔርን ልጆች ወደ ድህነት ያወርዳቸዋል። አዳዲስ አማኞች ይህን ትምህርት መማር አለባቸው። ለመቆጠብ ሲሉ ጥብቅ መሆን የለባቸውም። በመስጠት መባረክን መለማመድ አለባቸው ። ገንዘባቸውን በጥብቅ የሚይዙና የማይሠጡ ሰዎች እግዚአብሔር ሊታመንባቸው አይችልም። እነዚህ ሰዎች እምነት የማይጣልባቸው ናቸው ። አንድ ሰው ብዙ የሚሠጥ ከሆነ እግዚአብሔርም ብዙ ይሰጠዋል ።

### 1. ለእግዚአብሔር መዝራት

" ይህንም እላለሁ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል ። "/2ቆሮ 9፥6/ ይህ ጥቅስ ከክርስቲያኖች የገንዘብ መመሪያ ጋርም የሚገናኝ ነው። ክርስቲያን ገንዘቡን ይሰጣል እንጅ አይበትንም። ብዙ የሚቀበል የሚበትን ሰው አይደለም። ወይንም ጥቂት የሚቀበል ጥቂት የበተነም አይደለም። እግዚአብሔር ግን የሚለው በበረከት የዘራ በበረከት ያጭዳል በጥቂት የዘራም በጥቂት ደግሞ ያጭዳል ። ገንዘብህ እንዲበቅል ትፈልጋለህ ? ከፈለግህ ሂድና ዝራ፣ ብትዘራው ገንዘብህ ይበቅላል፣ አለበለዚያ ግን ያንኑ ሆኖ ይቀራል ።

ወንድሞችና እህቶች ካልዘራንበት ለማጨድ እንደሞኞች እናስባለን። ብዙ የበረከት ፀሎቶች የማይመለሱት አስቸጋሪ ሰዎች በመሆናችን ነው ። ምክንያቱም ካልዘራንበት ለማጨድና ለመሠብሰብ ስለምንፈልግ ነው። ታዲያ ለምን ጥቂት ገንዘብ ወስደን አንዘራና አናየውም ? ለምን ገንዘብህን በተቸገሩ ብዙ ወንድሞችና እህቶች ላይ አትዘራውም። እንዲያ ብታደርግ ታጭዳለህ። ገንዘቡን አጥብቆ የያዘ ሰው ምንም ነገር አያተርፍም። እዚህ ላይ መልካሙን ስዕል አያችሁ። ሐዋርያው ጳውሎስ ድሆችን ለመርዳት ገንዘባቸውን ስለላኩ ሰዎች ይናገራል። የፊሊጵስዩስ አማኞች በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ቅዱሳን የሚያስፈልጋቸውን ልከውላቸዋል። ይህንንም መዝራት እንጅ ማባከን እንዳልሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ተናግሮታል። አስተውሉ ገንዘብ እህል እንደሚዘራ ሊዘራ የሚችል ነው። የተቸገሩ ወንድሞና እህቶች ብታገኝ

የሚያስፈልጋቸውን ስጣቸው። ሰላሣ፣ ስድሣና መቶ እጥፍ እስከምታጭድ ገንዘብህን ያበዛልሃል ።

አማኞች መዝራትን መለማመድ አለባቸው። እንደዚህ ቢያደርጉ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ የዘሩትን ያጭዳሉ። ያልዘራሃውን ልታጭድ አትችልም። ብዙዎች ያላቸውን ሁሉ ስለሚበሉት ምንም ነገር አይቀራቸውም። እንበል አንተ 50 ኪሎ ግራም እህል ቢኖርህና ግማሹን ብትዘራው በሚቀጥለው ዓመት ምርት ይኖረዋል ። ሁል ጊዜ እንዲህ ብታደርግ ከዓመት እስከ ዓመት ምርት ይኖረዋል ። ያለህን ሁሉ አትብላው። ለምትዘራው ጥቂት አስቀር። ብዙ ክርስቲያኖች ምንም ሳያስቀሩ ይበሉታል። እንደዚህ ስለሚያደርጉ በሚያስፈልጋቸው ቀን ባይጨመርላቸውና ባያመርቱ አያስደንቅም። እግዚአብሔር ገንዘብህን እንድትዘራ ያድርግ ። አሜን !!

## 2. ወደ እግዚአብሔር አምጣ

የእግዚአብሔር ቃል የሚያስፈልገንን ነገር በተመለከተ በብሉይ ኪዳን በጣም ግልፅ ነው "በቤቱ ውስጥ መብል እንዲሆን አስራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ። " /ሚል 3÷10/ ይህን ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረው እግዚአብሔር ነው። ይህም ቀደም ሲል ላብራራነው አንድ ዓይነት መመሪያ ይሰጣል ።

እስራኤላውያን በድህነት አዘቅት ውስጥ ነበሩ። ሚል 3÷10 የታዘዘውን ተግባራዊ አድርጉ ሲባሉ ምን አልባት አሥር ኩንታል ሩዝ ካልበቃን ዘጠኝ ኩንታል ሩዝ እንዴት ይበቃናል ? አሥር ጆንያ ዱቄት ካልበቃ ዘጠኝ ጆንያ እንዴት ሊበቃ ይችላል? ይሉ ይሆናል ። እንደዚህ አይነቱ የሞኝነት አባባል የሚነገረው በፍጥረታዊ ሰው ነው። እግዚአብሔር ግን ለእስራኤል ሕዝብ "ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል ። " /ማቴ 19÷26/ ነው የሚላቸው" ... አስራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ በረከትንም አትረፍርፌባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ "... /ሚል 3 ÷10/ በማለት ይናገራል ።

አንድ ነገር ልንገራችሁ፣ አስር ኩንታል የድህነት ምክንያት ነው፣ ዘጠኝ ኩንታል ግን የበረከት ምክንያት ነው ። አንድ ሰው በእጁ ብዙ ካለው የገንዘብ ሁኔታው በጥሩ ላይ ያለ እንደሆነ አድርጎ ሊቆጥር ይችል ይሆናል፥ነገር ግን እንደዚያ አይነት ሁኔታ ለድህነቱ መሠረታዊ

ምክንያት እንደሆነ አላወቀም። ወደ እግዚአብሔር ብናመጣ ወደ በረከት እንገባለን። በእጃችን ብናስቀር ግን እንረገማለን። ተጨማሪ ስጦታ ወደ እግዚአብሔር ጎተራ ብናስገባ በረከታችን ይሆናል፣ ብናስቀር ግን መርገም ይሆንብናል። ሌላው ዘጠኙ እንኳ ሣይቀር ይዋጥብናል ። የእግዚአብሔር የሆነውን ብናስቀር ድህነትን እናያለን ።

### 3. ለእግዚአብሔር መበተን

"ያለውን የሚበትን ሰው አለ ይጨምርለታልም ። ያለቅጥ የሚነፍግ ሰውም አለ ይደኸያልም ። " /ምሳ 11፥24/ ብዙዎች አይበትኑም ስለዚህም ምንም አይኖራቸውም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት የሚበትኑ ሀብታም ይሆናሉ፥ ይህም በእግዚአብሔር ቃል ተገልጿልናል ።

### 4. ለእግዚአብሔር ማባከን

ሌላም ልናየው የሚገባአንድ አስደናቂ ትዕይንት አለ። ኤልያስ ለዝናብ በፀለየ ጊዜ ሕዝቡ በከፍተኛ ድርቅ ይሰቃይ ነበር ። ንጉሱና የቤቱ አለቆች / መኳንንቶች/ ሳይቀሩ ውሃ ፍለጋ ይንከራተቱ ነበር ። በዚህም የውሃ ችግር እንዳለ በቀላሉ ይታወቃል ። ነገር ግን ኤልያስ መስዋዕቱን በሚያሳርግበትና ለዝናብ በሚፀልይበት ጊዜ ሰዎችን በሚቃጠለው መስዋዕት ላይ ውሃ እንዲያፈሱ አዘዛቸው። በዚያን ወቅት ውሃ ምን ያህል ውድ እንደሆነ አስቡ። ነገር ግን ኤልያስ ውሃው በመሰዊያው ላይ እስኪፈስና ጉድጓዱ እስኪሞላ ድረስ በመስዋዕቱ ላይ ሦስት ጊዜ እንዲያፈሱ አደረጋቸው ። እውነታውን ስንመለከት ዝናብ ገና ከሰማይ አልመጣም ነበር። ታዲያ ብዙ ውሃ ማፍሰስ ማባከን አይደለምን ? ዝናቡ ባይመጣ ምን መሆን ይቻላል? ነገር ግን ኤልያስ ውሃውን እንዲያፈሱ አዘዛቸው። ከዚያም ተንበረከከና በመሰዊያው ላይ ያለውን መስዋዕት የሚበላ እሣት እግዚአብሔር እንዲልክ ፀለየ። እግዚአብሔርም ይህን ፀሎት ሰማ። ለዝናቡም የፀለየውን ሠማ፣ ታላቅ ዝናብም ላከ ። እንግዲህ ልንገራችሁ ሰማያት ከፍተኛ ዝናብን እንዲልክ ከፈለጋችሁ በመጀመሪያ የራሣችሁን ውሃ አፍስሱ። የራሣችሁን ውሃ ካላፈሠሣችሁ ከሰማይ ውሃ አታገኙም ።

እዚህ ላይ የብዙዎች ችግር የሚገለጽበት ሥፍራ ነው። ብዙዎች የራሣቸው የሆነውን አጥብቀው ይይዛሉ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ፀሎታቸውን እንዲሠማ ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር ድርቅን ለማባረር ዝግጁ ነው። ነገር ግን ሰዎች ውሃቸውን እስከሚያፈሱ ይጠብቃቸዋል ። የሰው ሐሳብ ሁል ጊዜ ከመንገዱ የራቀ ነው ። ዝናብ ባይዘንብ ቢያንስ እሥራ ሁለት እንስራ ይኖረናል ብለው ያስባሉ። ነገር

ግን በእጃቸው ያለውን የእንስራ ውሃ የሚቆጥቡ ሰዎች የሰማዩን ውሃ ሊያዩ አይችሉም። የሰማዩን ውሃ የሚመኙ ሰዎች ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ በእጃቸው ያለውን ውሃ ለማፍሰስ ፈቃደኛ መሆን አለባቸው። ሁሉ ነገር መስጠት አለበት። ከብቶችና በጎች ብቻ አይደለም በእጃችን ያለው ውሃ ጭምር እንጂ። የገንዘብን ጉዳይ በተመለከተም ይሄው መመሪያ ይሰራል ። አማኞች ከእንደዚህ አይነቱ የእስራት ኃይል ነፃ ካልወጡ የቤተ ክርስቲያን መንገድ ቀጥ ያለ ሊሆን አይችልም። ያለንን ሁሉ ለእግዘአብሔር በመሠዊያው ላይ ለማድረግ ሁላችንንም የተቀደስን ሕዝቦች ያድርገን።

## 5. ከእግዚአብሔር መሞላት

"አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል " /ፊል 4፥19/። ይህ በእርግጥ የሚያስደንቅ ጥቅስ ነው ። የቆሮንቶስ አማኞች ለመስጠት ጥብቆች ናቸው። የፊሊጵስዩስ አማኞች ግን ለጋሶች ናቸው። የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች በየጊዜው ወደ ሐዋርያው ጳውሎስ ገንዘብ ይልኩ ነበር። በምላሹም ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር አምላክ የሚያስፈልጋቸውን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚሞላባቸው ይነግራቸዋል። የዚህን ጥቅስ አስገራሚነት አያችሁ? " አምላኬ ይሞላባችኋል" የሚለው ቃል ሐዋርያው ጳውሎስን የረዱትን ሰዎች እግዚአብሔር አምላክ እንደሚሞላባቸው ያሳያል። የስጦታ ተቀባዩ አምላክ ለሰጭዎቹ የሚያስፈልጋቸውን ይሞላባቸዋል ።

ብዙዎቹ ዛሬ ፊሊጵ 4፥19ን አፍነው ይዘውታል። ነገር ግን በዚህ ጥቅስ እግዚአብሔር የሚለምኑትን ሣይሆን የሚሰጡትን ሰዎች እንደሚሞላባቸው አስተዋልህ ? ይህን ጥቅስ የመጠቀም መብት ያላቸው ሰጭዎች ብቻ ናቸው። የማይሰጡ ግን የዚህ ጥቅስ መብት የላቸውም። ለሌሎች ከሰጠህ በኋላ ግን እንዲህ ብለህ መጠየቅ ትችላለህ " እግዚአብሔር ሆይ እንደባለፀግነትህ በክርስቶስ ኢየሱስ ዛሬ የሚያስፈልገኝን ሙላብኝ "እግዘአብሔር የሚያስፈልጋቸውን የሚሞላባቸው የፊሊጵስዩስን ክርስቲያኖች ብቻ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚሞላው በመስጠት መመሪያ ነውና። እንግዲህ የማድጋህ ዱቄትና የማሰሮህ ዘይት ሊያልቅ ሲል ለእግዚአብሔር ነቢይ ለኤልያስ በመጀመሪያ ትንሽ እንጎቻ ማድረግን አትርሣ። በዚህ ጊዜ አንድ እፍኝ ዱቄትና ጥቂት የማሰሮ ዘይት ለሰስት ዓመት ከስድስት ወር ይበቃሃል ። ማነው ጥቂት የማሰሮ ዘይት ለሦስት ዓመት ተኩል ይቆያል ብሎ የሚያስብ ? ነገር ግን በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር ነቢይ ከጥቂቷ ዱቄትህና ከትንሿ ማሰሮ ዘይትህ ከፍለህ እንጎቻን ለማዘጋጀት

ብትጠቀም ለዓመታት ልትመገብ ትችላለህ። ያች እፍኝ ዱቄትና ጠብታ ዘይት ለአንድ ጊዜ ማዕድ እንኳን የምትበቃ አይደለችም። ነገር ግን በመጀሪያ ለእግዚአብሔር ከተሰጠ ለሕይወት ዘመንህ ይበቃል ።

እንግዲህ ይህ ክርስቲያኖች ገንዘባቸውን የሚያስተዳድሩበት መንገድ ነው ።

## የክርስቲያንኖች መንገድ በመስጠት ነው

ብሉይ ኪዳንም ሆነ አዲስ ኪዳን የሚያስተምሩት አንድ ዓይነት ነው ። እግዚአብሔር ድሃ እንድንሆን ወይም እንድንቸገር አይፈልግም። በመካከላችን ድህነት ወይም ችግር ቢከሠት የዚህ ምክንያት ምን አልባት ገንዘባችንን አጥብቀን ይዘን ይሆናል ። ራሣችንን በጣም የምናፈቅር ከሆነ በጣም እንራባለን ። የገንዘብ ጥያቄአችን መልስ ካላገኘ ሌላ ጉዳያችን መልስ አያገኝም ። ገንዘብ ትልቅ መስሎ ለሚታየው ሁሉ ድህነት እየቀረበው መሆኑን ይወቅ። ሌሎችን ነገሮች ላረጋግጥላችሁ ባልችልም እንኳ ይህን ግን በሙሉ ድፍረት ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። ገንዘቡን አጥብቆ የሚይዝ ይደኸያል። እግዚአብሔር ታምራትን እንዲሠራ ገንዘባችንን እንልቀቅ ፣ እንዲዘዋወርም እንፍቀድለት ።

በተራሮች ሁሉ ላይ ከብቶችና በጎች የእግዘአብሔር ናቸው። ሞኝ ካልሆነ በስተቀር ማነው እነዚህን አገኛለሁ ብሎ የሚያስብ ? እንግዲህ እኛ ሁላችን ማድረግ የሚገባን የእኛ የሆነውን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር በማምጣት ነው ። ገንዘብ ወደ እኛ እንዲመጣ ለሌሎች በመስጠት ወደ እግዚአብሔር ማግባት አለብን። ወንድሞችና እህቶችን በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ መንከባከብ አለብን። ይህም ለራሣችን ማከማቸት ነው ። የክርስቲያን መንገድ በመስጠት ውስጥ ነው ። በቤተክርስቲያን ያለ ገንዘብ ሁሉ ሕያው እንዲሆን እንፍቀድ ። እንደዚያ ብናደርግ በሚያስፈልገን ጊዜ እግዚአብሔር ታምራቱን ይሠራል። የሚያስፈልጉንን ሁሉ ይሞላብናል።

ራስህን በእግዚአብሔር ቃል ላይ አኑር ። እንዲያ ባታደርግ ግን እግዚአብሔር ቃሉን በአንተ ውስጥ ለመፈፀም መንገድ አይኖረውም። ከመጀመሪያ ራስህን ለእግዚአብሔር ስጥ። ከዚያም ገንዘብህን ስጥ። እግዚአብሔርም መልሶ ይሰጥሃል።

የዕብራውያን መልዕክት ፀሐፊ በዕብ. 11፡32-38 የጻፈው የዕምነት አርበኞች ታሪክ በዎችማን ኒ ሕይወት ተደግሟል ቢባል ማጋነን አይሆንም። በዚያች ክህደት እግዚአብሔር ነግሶበት በነበረ በትውልድ ሀገሩ በቻይና በክርስቶስ ኢየሱስ ህይወት ጸንቶ በመቆም የታየ ሰው ነው። ዎችማን ኒ በነበረበት ዘመን በሚያምኑትም በማያምኑትም ዘንድ ስለ ክርስቶስ ብዙ ስቃይ ደርሶበታል። በእርሱ ላይ ከነበረው የእግዚአብሔር ፀጋ የተነሳ ከጨለማው ግዛት በሚሰነዘር ጥቃት ከፍተኛ የሆነ ግልፅ ውጊያ ነበረበት። ከውጊያውም ኃይል የተነሳ እንዳይሰብክና እንዳያስተምር ለማድረግ የተለያዩ ኢሰብአዊ ድርጊቶች ተፈፅመውበታል። ከነዚህም አንዱ እንዳይሰብክ ለማድረግ ምላሱን ቆርጠውታል። ነገር ግን እግዚአብሔር በልዩ ልዩ አስደናቂ መንገድ በዚህ ሰው ተጠቅሟል።

እግዚአብሔር የሚታዘዝ ሰው ካገኘ ለመሥራት የሰው ሁኔታ አያግደውም። ስለሆነም የዚህ ሰው ምላስ ሲቆረጥ በእጁ እንዲሰብክ አድርጓል። ቅባቱ በዚህ ሰው እጅ ላይ ያልፍ ነበር። እንግዲህ ያ ቅባት ነው እጅግ በርካታ መጽሐፍት እንዲደርሱን ያደረገው። ዛሬ በዚህ ዘመን ላለነው የደረሰን በረከት በአንደበቱ የተናገረው ሳይሆን በእጁ የሰበከው ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ለበጎ ስለሚለውጥ ይህ ሰው በአንደበቱ ከሰበከው ይልቅ በእጁ የሰበከው፡ ዘመን ተሻግሯል። ስለሆነም ዛሬ በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች በዚህ ሰው መጻሕፍት ለመባረክ ችለናል።

የዎችማን ኒ መጻሕፍት በመላው ዓለም ባሉት ክርስቲያኖች ዘንድ የሚወደዱ ናቸው። በእኛ ሀገርም ከማንኛውም በውጭ ሀገር ዜጎች ከተጻፉ መጻሕፍት ብዙዎች የሚወዱት መጻሕፍት ነው። ብዙ አንባቢዎች የዎችማን ኒ መጻሕፍቶች ወደ አማርኛ ተተርጉመው እንዲቀርቡላቸው በተደጋጋሚ ስለሚጠይቁ አቶ አይሸሹም መኮንን ይህን መጽሐፍ ተርጉመው አሳትመው ነበር።

አቶ አይሸሹም ዎችማን ኒ ከጻፋቸው «ከወተት ወደ አጥንት፣ ፀጋና እውነት» የተባሉትንም መጻሕፍት ወደ አማርኛ መልሰው አስነብበውናል፣ በቅርቡም በድርጅታችን የሚታተም «መጻሕፍትን መርምሩ» የተሰኘ መጽሐፍም ይኖራል።

ይህ «ቅድስና» የተሰኘው መጽሐፍ ብዙ ጉዳዮችን የሚዳስስ ስለሆነ ሰው ሁሉ በጥንቃቄ ቢያነበው ታላቅ በረከት ያገኛል ብለን ስላመንን በድጋሚ አሳትመነዋል።

ራዕይ አሣታሚ